ገፀ-ባህሪያት

ማርክ አንቶኒ.....

ቤንቱዬሥ...../የጦር ጀነራል/

ዶላቤላ...../ንደኛው/

አክታቪያ...../ባለቤቱ/

አሽከሮች.....

ክሊዎፓትራ...../የግብፅ ንግስት/

አሌክሳስ...../ጃንደረባዋ/

ቻርሚዎን.....ገረድ

አይራ.....ገረድ

ሴራጲዮን...../የግብፅ ቄስ/

ማይረስ...../የግብፅ ቄስ/

ባለሟል.....

ቦታው

አሌክስ አንድሪያ /ግብፅ/

ጊዜው

የንግስት ክሊዮፓትራ ዘመነ መንግስት

ተላላኪ

ገቢር አንድ

/ቦታው የአይሲስ ቤተ መቅደስ ቁስ ሴራጲዮን እና ቁስ ማይሪስ ይታያሉ፡፡

ሴራጲዮን፡- ኧረ ያዳም ልጅ ምን ሆናል የዝሆን ጆሮ መሻቱ

ቁጣ ምፅ አት መምጣቱ

ሲኾርጎደጎድ ምልክቱ

የሚያየውን የሚሰማውን ፤ነገሬም አለማለቱ

ሴራጲዮን፡- ሌሊት ተገኝቼ በህልሜ-መቅደስ ውስጥ ይመስለኛል

በምሰሶዎቹ መሃል ከላይ ታች ሸር ሸር ስል

አውሎ ንፋስ ሲነሳ አየው፤ የመብረቅ እሳት የሚመስል

ጣራ ግድግዳው ተናጋ፤ መስኮት በሮች ተላተሙ

ማጠፊያዎቻቸው ጮሁ፤ተዘግተው እንደከረሙ

የቶለሚስ የዘር ሃረግ፤ነገስታት ሚቀበሩበት

መቃብር ቤት ብረት በሩ፤ብርግድ አለና በድንገት

ታየልህ መቃብራቸው፤የሃያላን ሞት ነገስታት፡፡

ስብሃት ለአብ እግዚኦ ምፅአት!

ከእያንዳንዱ ሃውልት ስር፤እየፈነቀለ ጡብ አጥሩን

ጣረ ሞቱ ብቅ ይል ጀመር፤እንደያዘ ጋሻ ጦሩን፡፡

ወዲያው-የጣእር የሰቆቃ፤ድምፅ ማሰማት ቀጠለ

ከዚያም አንድ የሚያስፈራ ድምፅ፤‹‹አከተመላት ግብፅ!››አለ፡፡

ማይረስ፡- አረ ባክህ ሴራጲዮን-ይህን ባትነግረኝ ምን አለ!

ሴራጲዮን፡- አንዳች ፍርሀት ወረረኝ-መቅኔዬ ረጋ ባጥንቴ

ሎሚው ሚሸሸ ጉልበቴ

የሰራ አካላቴ ላልቶ፤ወደቅሁና ከወለሉ

አሰቃቂውን ተርኢት፤አቋረጥኩት ከመሃሉ፡፡

ማይረስ፡- ምን ጉድ ሊያወርዱብን ይሆን፤የዶሉቱት አማልክቱ

ሰውረን ከማእቱ

አሌክሳስ፡- (<u>ብቅ እያለ</u>) እና ህልም አየሁ ነው የምትል-ወይ የፈጠርከው ታሪክ ነው

እንዲሰጉ የግብፅ ልጆች፤ጉድ ሊፈላብን ነው ብለው

ሴራጲዮን፡- ጌታዬ-አላየሁህም፡፡

የተናገርኩም ሆን ብዬ፤ላንተ እንዲደርስህ አይደለም

ግን አሁን ከአፌ ከወጣው፤አንድም የሃሰት ቃል የለም፡፡

አሌክሳስ፡- እንግዲያውስ ሰውዬ ስማኝ-ይህ አንተ ህልም የምትለው

ከቅንጦት ከድሎት ብዛት፤የመጣ የጅል ቅዠት ነው

ሽብር በቁስ አፍ አያምርም፤ብታውቅበት ነው ሚሻለው

ሴራጲዮን ሃላፊነቴን አውቄያለው ከንግዲህ አይቀጥልም፡፡

አሌክሳስ፡- ሊቀጥልም አይገባውም፡፡

ህልምህ እውነት እንኳ ቢሆን፤አሁን አንተ እንደምትለን

ለንዲህ ያለ እንቶፈንቶ፤የሚያዋላ ጊዜም የለም፡፡

ከኒያ ኮረብቶች ደቡብን፤እንደ ንብ ሰፍሮ ጉብ ያለው

ያፍንጫ ስር ስጋታችን፤የሮማውያን ጦር እኮ ነው፡፡

ሴራጲዮን፡- የደካሞቹ ግብፃውያን፤ፀሎት ለንቶኒ ቢሆንም

ፈሪ ሽቁጥቁጡ ልባቸው፤ውስጥ ውስጡን የአክታቢዮስ፤ባለ እዳ ሳይሆን አይቀርም፡፡

ማይሪስ፡- ታዲያ አንቶኒ ለምንድነው

ጊዜውን ከንቱ ከሚገድል፤እድሉን የማይሞክረው

ከቀናው እኮ-ማን ያውቃል

አክቲዮም ላይ ያጣውን ክብር፤ማስመለስ ይችል ይሆናል፡፡

አሌክሳስ፡- ምን ያደርጋል!-በሱ ግምት-በአክቲዮም ላይ የሆነው

ከንግዲህ የማይታፈስ፤መሬት የጠጣው ውሃ ነው።።

ሴራጲዮን፡- ለነገሩ-ጠላቶቹም፤ጫናቸውን አላበዙም

ከበቡ እንጂ ከቆሙበት፤ አንዲት ስንዝር አልተጓዙም።።

አሌክሳስ፡- እሱ አይደለ የሚገርመው

ማይቼናስ እና አግሪፓ፤ከቁሳር ግራ ቀኝ ቆመው

ለሱ ፈላጭ ቆራጮቹ፤ላንቶኒ ግን ጠላት ናቸው።።

ባለቤቱም አክታቪያ - ተቤቱ ተባራ ወጥታ

በቀሏን እያስታመመች፤ ቀን ነው ምትጠብቅ አድብታ።።

ጥንት ወዳጁ የነበረው፤ ዶላቤላም ሆኖት ጠላት

ቂም አርግዞ ርቆታል፤ የመገላገያው ሰአት።።

እንዲያም ሆኖ- ጦርነቱ

እዚም ሆነ ከዚያ በኩል፤ ይህን ያህል መተኛቱ

የሚገርም ነው በውነቱ።።

ሰራጲዮን፡- ግን አንቶኒስ -የሄን ሰሞን

የክሊዎፓትራን ፊት መሸሹ፤ምክንያቱ ከቶ ምን ይሆን

አሌክሳስ፡- የኛም ስጋት እኮ የሄው።።

የሰለሰለ ናላውን ፤ከፍቅሯ ካራ ሊያደነው

ከሷ መሸሹ እንዳይሆን፤ እንደ ዘዴ የመረጠው።።

ሴራጲዮን፡- በጠላቶቹ ቢሸነፍ፤ ወይም ሰግቶ ቢደራደር

ወዮ ለግብፅ- መሆኗ ነው፤ አንድ የሮማ ክፍለ ሀገር።።

ትርፍርፉ ምርታችንም፤የነሱን ድርቅ ያካክሳል

ይውል ያድር የሆናል ይሆናል እንጂ፤ መቼም የፈሩት የደርሳል።።

አሌክሳስ፡- እንደኔ እንደኔማ ቢሆን- እነዚህ ጨካኝ ገገርሶች

አንዱ አንዱን እየበላ፤ ቢያልቁ ነው ለሰው የሚመች።።

ሴራጲዮን፡- ንግስቲቱ. . .ስ- እንዴት ናት

ንደዚያው ነች ወይ ተሻላት

አሌክሳስ፡- አረ ተወው - የሷስ ነገር ፤ አይወራ ሴራጲዮን

አብዳለች ከንፋለች ጭራሽ፤ አታውቀውም ምትሰራውን

ያ መለኮታዊ ሀይሏ፤ ከላይዋ ላይ የለም አሁን፡፡

ባበቃለት በተረታ፤ በዚህ ባንቶኒዋ ፍቅር

የጀግና አላቂ አቅፋ፤ ከቶ እንዲህ ሆና ትቅር

እንጂማ- አውቃበት ቢሆን፣ የኸው ታዳኛችሁ ብላ

ለዳኞቹ ለነቄሳር፣ ብትሰጣቸው ነበር መላ

ሁላችንንም አድና፣ ትተርፍ ነበር ለሌላ፡፡

ምን ያደርጋል -ልቧ መሐል፣ተደላድሎ ተቀምጧላ!..

(<u>ቤንቲዬምስ በጥግ በኩል ከአንቶኒ ባለሟል ጋር እያወራ ይገባል</u>)

ስራጲዮን፡- እስቲ ቆይ- ላሁኑ ይብቃን፣ሮማውያኑ እንዳይሰሙን

ያኛው እንግዳ ይመስላል- ታውቀዋለህ ማንነቱን

አሌክሳስ፡- ኦ! -ቤንቲዬምስ ነው፡፡

ምስራቁን ቀጥ አርጎ የያዘ፣ የማርክ አንቶኒ ጀነራል !

ፓርቲያን የሚያህል አገር፣ ያስገበረስ ማን ይመስልሀል

አንቶኒ ባለፈው ሰሞን፣ከሲሪያ አገር ሲመለስ

አደራ ብሎት ቢመጣ፣ እዚያው ኑሯል አሁን ድረስ፡፡

ሴራጲዮን፡- በጣም ታውቀው ትመስላለህ፡፡

አሌክሳስ፡- እንዴታ! -ከሚገባው በላይ ማለት ትችላለህ፡፡

ቺሊቺሊያ ውስጥ ነበር፣ መጀመሪያ ቀን ያየሁት

ክሊዎፓትራና አንቶኒ፣እዚያ አደል የተገናኙት

ያኔ- ለኛም ሆነ ለግብፅ፣ ጠላት መሆኑን አወቅሁት፡፡

ግን ልመስክር ለማተቤ- ህሊናዬ እንኳን ባይወደው

የሰይፍ አበጋዝ በሮማ፣ አልተፈጠረም ሌላ ሰው፡፡

ያሁኑ ግን አመጣጡ- ምክንያቱ ባይታየኝም

ላቀድነው ሁሉ ሳንካ እንጂ፣ ቀና ነው የሚል ህልም የለኝም፡፡

አሁን ገለል በል ወደዛ - ከፈለክ ሳትታይ ልታይ

ወዲያውም አስረዳሃለው፣ አንተ ያስፈለከኝን ጉዳይ፡፡

(<u>ወደ መድረኩ ጥግ ይሄዳሉ፡፡ ቤንቲዬሞስና የአንቶኒ ባለሟል ወደ መድረኩ ፊት ለፊት ብቅ ይላሉ</u>)

ቤንቲዬሞስ፡- ልታየው አትችልም አልከኝ - ማየቴማ የግድ ነው!

ባለሟል፡- ይሄ የኔ ህግ አይደለም፣ ራሱ እኮ ነው ያዘዘው

ቤንቲዬሞስ፡- ልታየው አትችልም አልከኝ-ማየቴማ የግድ ነው!

ባለሟል፡- ይሄ የኔ ህግ አይደለም፤ራሱ እኮ ነው ያዘዘው!

ቤንቲዬሞ፡- ዜና ይገፍለት ነውና፤የመጣሁት እዚህ ድረስ

የሱም ቢሆን ትእዛዙ፤ግዴለም ላሁኑ ይፍረስ፡፡

ባለሟል፡- ሌላ ፍጡር ይቅርና፤ክሊዎፓትራን አያያትም፡፡

ቤንቲዬሞስ፡- አረ እሳንስ ቀድሞ ነገር፤ምነው ባላያት ከጥንትም!

ባለሟል፡- ወይ አይበላ፤ወይ አይጠጣ፤ወይ አይተኛ፤ካሳብ በቀር

ተናገር ቢባል እንኳ፤ከራስ ነው ሚነጋገር፡፡

አለም በቃኝ ብሎ ዘግቶ፤አለምን ካላለፍሽ ይላል

ከንፈሮቹን እያኘከ፤አክታቢዮስን ይረግማል፡፡

ቤንቲዬሞስ፡- በርግጥ-ይህ ነው ተፈጥሮውም፡፡ግን አንዳንዴ-ምን ያደርጋል

ለውቅያኖስ ነፍሱ ስፋት፤ይህ መንገዱ ይጠበዋል፡፡

ከሰው በላይ ሆኖ፤እንደሰው ስህተት መስራቱ

ይቅርታም የለው በሱ ዘንድ፤ያሰቃየዋል በብርቱ፡፡

የዋዛ ሰውም አልነበር፤እንዲህ የሚቀር በከንቱ

(አሌክሳስ እና ቄሶቹ ወደ መድረኩ ፊት ለፊት ብቅ ይላሉ)

አሌክሳስ፡- መመሪያችሁን አንድ በአንድ፤ተቀብላችሁ የል አሁን

በሉ-ቀጥሉበፍጥነት፤አውጁ ትእዛዛችሁን (ይወጣል)

ሴራጲዮን፡- አዋጅ! አዋጅ!-ሮማውያን! ግብፃውያን! በአሌክሳንድሪያ ያላችሁ!

የንግስቲቱ ትእዛዝ፤አድምጡ ልብ ብላችሁ!

‹‹ስራ ሁሉ ይቁምና፤የዛሬው ታላቅ ቅዱስ ቀን

አንቶኒን የሚያህል ጌታ፤ለአለማችን ለሰጡን

አማልክት መታሰቢያ፤ሞገስና ክብር ይሁን!ብላ አዛለች ንግስታችን

ማርክ አንቶኒ ለዘላለም ይኑር!

ክልዎፓትራ ለዘላለም ትኑር!

ቤንቲዬሞስ፡- /<u>ጉምጉምታ</u>/ አረ እንዴት ያለ ቀልድ ነው!

ይዜንንስ ባላየው ምነው

ሴራጵዮን፡- ወይን ይቀዳ፤በቁጠማም፤አሳምሩት ቀዬአችሁን!

ቢንቲዬሞስ፡- ይህንን ቀን የደስታ ይሁን፤ብሎ ያዘዘ ባንደበቱ

መአት በላ ይውረድበት! ህሊናም የለው ከጥንቱ!

አሌክሳስ፡- ለታላቁ ሰው ላንቶኒ፤ዕልቆ መሳፍርት ፍቅር

ሰማይ ካጥናፍ አጥናፍ በርቶ፤ነው ደስታ የሚያበስር፡፡

የራሷን ልደት ቀን እንኳ፤ንግስታችን ችላ ብላው

ያዘቦት ሰኞ ይመስል፤እንደዘበት ነው ያለፈው፡፡

ቤንቲዴዎስ፡- ምነው የሷስ ልደት ቀኗ፤መቶ አመታት በዘገየ!

አንቶኒ ተወልዶ እስኪሞት፤እዚያም ተዳፍኖ በቆየ!

አሌክሳስ፡- ንጉሳችሁ-ምንም እንኳ፤ እያደር ቢከፋ ልቡ

ማንኳሰስ፤ ማበሻቀጥ ነው፤የጨዋ ልጅ ወጉ ደንቡ

ቤንቲዴዎስ፡- ትሰማለህ ጃንደረባው

ሆድ ሲያውቀው ከንቱ ማስመሰል፤ላንተም አይነቱ አይረባ፡፡

የወንድነት መቅኒውን፤መጥጣው ቀፎው እስከሚቀር

እሱው መሆኑን ማን ወዳጅ፤ነው አፉን ሞልቶ ሚናገር

የዚች አለም ግማሽ ገጢ-ያ ሁሉ ቀረና አሁን

ከነ ሙሉ ስጋ አጥንቱ፤ የሴት አሻንጉሊት ይሁን

አወይ የኛ ማርክ አንቶኒ፤አንተ የባልንጀራ ቁንጮ! -አንተ የጀግኖች ሁሉ ጀግና!

የዋህ ቸር እንደፈጣሪ፤እንዳንተ ማን ነበረና!

ጃንደረባው- ፍጠንና፤ ሂድ ለንግስትህ ንገራት

የኔን የውድ ጓደኛውን፤የቤኒቲዴዎስን መምጣት፡፡

ውሃ እንደበላው ትወቀው፤ ከእንግዲህ የሳ ምትሃት!

(<u>አሌክሳስ እና ሴራጲዮን ይወጣሉ፡፡የአንቶኒ ባለማሎች ይገባሉ፡፡</u>)

ሁለተኛው ባለሟል፡- እየመጣ ነው ንጉሱ- አዛል ማንንም እንዳያይ

ልጠጋ ያለን ወደሱ፤ ነፍሱን ከስጋ ሊለያይ፡፡

አንደኛ ባለማል፡- ትዕዛዙን ልጥስ አልደፍርም- አሁኑኑ እወጣለሁ፡፡

/ <u>ከሁለተኛው ባለማል ጋር ይወጣሉ</u>/

ቤኒቲዴዎስ፡- ደህና- እኔ እደፍራለሁ!

ግን አስቀድሜ መንፈሱን፤ ሳያየኝ ማጤን አለብኝ

ከዚያ-‹‹ሚመጣው ይምጣብኝ!

/ወደ መድረኩ ጥግ ገለል ይላል፡፡አንቶኒ በተወለካከፈ፤በተረባበሸ አረማመድ ከገባ በሃላ ብቻውን ማውራት ይጀምራል፡፡)

አንቶኒ፡- የልደት ቀንህ ነው አሉኝ - እስቲ ይሁና ምናለ

ለኔ እስትንፋስ የሰጠ ቀን ፤ እውን ቀን ነው ከተባለ፡፡

ለምን ነው ሽቅብ ማደጌ፤እስከምንሳፈፍ ሰማይ ላይ

እንደ አብሪ ኮከብ ፏ ብዬ፤ ከአጥናፍ አጥናፍ እስከምታይ

ከዚያስ ፋናዬ መውደሙ፤ መሸቆልቆሌ ወደ ምድር

ጭላንጭሌ ወርዶ እንዲከስም፤ ተረግጦ በቁሳር እግር

ቤንቲዬምስ፡- /ጉምጉምታ/ በሞትኩት! -የሚያሳዝን ነው፡፡

አንቶኒ፡- ምን ይሆን የተጠቀምከው

አይ ገሞራው ማርክ አንቶኒ! ለዚህ ይሆን የተፈጠርከው

አንት ዕድል በሊታ ሆዳም፤ ማትጠረቃ እድል በልተህ

በጧት አንክተህ ፈጅተሀው፤እድል አሁን ጠኔ ሆነህ፡፡

ቤንቲዬምስ፡- /<u>ጉምጉምታ</u>/ እግዚኦ! -አሁን አለ ነው ሚባለው

አንቶኒ፡- **/<u>በመደናገጥ አይነት ፈንጠር ብሎ እየተነሳና ሰይፉን እንደመምዘዝ እያለ</u> /**

ማነህ ደፋር የሳትራት፤ -ቀንህ ያለቀ ሙት ያለህ

ሃ! - ቤንቲዬዮስ ነህ

ቤንቲዬምስ፡- ይልቅ አንተ አንቶኒ ነህ

የኔማ መልክ ምን ለውጥ አለው

ያው የጥንቱ ምታውቀው ነው

ያንተን ግን ዐይኔን አያምነው፡፡

አንቶኒ፡- ከፊቴ ገለል በሉልኝ - ስሜቴ ቀና አይደለም፡፡

ቤኒቲዶሞስ፡- እኔን ካንተ ፊት እንዳልቆም፤የሚያደርገኝ አንዳች የለም!

ጌታዬ - አንድ አፍትም ቢሆን፤ ቀልብህን ስጠኝ ግዴለም፡፡

አንቶኒ፡- ተወኝ እኮ ነው የምልህ! - ብቸኝነት ፈልጌያለው -የሰው ስሜት አይገባህም

ቤንቲዶሞስ፡- እወድሃለው ጌታዬ - ስለዚህም አልተውህም፡፡

አንቶኒ፡- ‹‹ አልተውህም››

ኬት ተማርከው በል እሱን መልስ - ማን መሰልኩህ ማነኝ እኔ

ቤንቲዶሞስ፡- ንጉሴ - ጓዴ - ወገኔ!

መንግስተ ሰማይን ብቻ ነው

ያንተን ያህል የምወደው፡፡

ከዚያም በላይ ነው ብዬ ብል፤ ሃጥያት አይሆንብኝም

በዚች ምድር ላይ እንዳንተ፤ ከ ሀ እስከ ፐ ጥሩ አይገኝም፡፡

አንቶኒ፡- በዚች ምድር ላይ እንደኔ፤ ከ እስከ ፐ ጥሩ አይገኝም

እና - አሁን አትተወኝም

ቤንቲዶሞስ፡- ‹‹አልተውሁም››

አንተም ቢሆን ደግ አይደለም፤ካሁኑ እኔን ፊት መንሳትህ

የብስ ባህር አቃርጬ፤ላይህ መምጣቴን እያወቅህ፡፡

አንቶኒ፡- ታዲያ እኮ ይሀው አየኸኝ! - ደስ ብሎሃል ረክተሃል

የወዳጅነት ከሆነም፤በቂህን ያህል አይተሃል

የጠላትነት ከሆነ፤ይኸውም ይበዛብሃል፡፡

ቤንቲዶሞስ፡- **/<u>እያነባ</u>/**

ተመልከት ውድ ንጉስ ሆይ - ይሄ ተራራ ጤዛ አይደለም፤ጨሌ ሳር የሚያግተው ጧት

አንድ እንባ ጠብ አላለኝም፤ላለፉት አመታት፡፡

አሁን ግን የእናቴ አንጀት፤አንጀቴ ገብቴ ቢያስተኝ

እንደሳው ሴት ሆንኩኝና፤እንባዬን ማቀብ አቃተኝ፡፡

አንቶኒ፡- ኧረ የፈጣሪ ያለህ! - ያነባል እንዴ ሰውዬው

ምስኪኑ የዋህ ደግ ሰው

እንባውን እኮ አፈሰሰው!

ቤንቲዬሞስ - በቃ ተው

ተወው ይበቃል - አለዚያ፤ ሃፍረቱ ነው የሚገለኝ

ለዚህ ሁሉ ሃዘንህ እና፤እንባህ ምክኒያቱ እኔ ነኝ፡፡

ባክህ በቃኝ - ተለመነኝ፡፡

ቤንቲዬሞስ፡- እጥራለሁ በተቻለኝ፡፡

አንቶኒ፡- ተላላፊ ነው ይባላል፤የወዳጅ ዕንባ - በርግጥም

ጉድ አየህልኝ ተስቦውን፤የኔውም መጥቶ ሲል ግጥም

ቤኒቲዬሞስ፡- ንጉስ ሆይ!

አንቶኒ፡- ‹‹ንጉስ ሆይ››! . ‹‹ንጉስ ሆይ››! . ‹‹ንጉስ ሆይ››!

ይህ የድል ሰሞን ፈሊጥ ነው! - ዘይቤ ነው ሙሉ በሙሉ!

ቤንቲዬዮስ፡- ስለማምንብህ እኮ ነው፡፡

አንቶኒ፡- በምኔ ነው ‹‹ምታብንብኝ›› -ኦክቲዩምን ረሳኸው

ምንለ ሽንፈት ሃፍረቴን፤ደርሰህ ባትሸነግለው! - ወይኔ ሰውዬው!

ቤንቲዬሞስ፡- እጅግ ቆጥቁጦሃል በእውነት፡፡

አንቶኒ፡- መቆጥቆጥ አንድና ሁለት

ምነው በሞትኩ ያንን ዕላት!

ሌት የቅዠት እንደርቢ፤ቀን ልቤን እያሳከከኝ

ዓያስቀምጥ፤አያስተኛ፤የግር እሳት ነው የሆነብኝ፡፡

ቤንቲዬሞስ፡- አውጣው እስቲ - ተናገረው!

አይታመቅ - ንፋስ ስጠው፡፡

አንቶኒ፡- ተው ቅሌቱን አትጎትጉተው፡፡

ከቶም ሆኖ ማያውቀውን፤በጦር ሜዳ ድል ተነሳሁ!

ቤንቲዴሞስ፡- ዩሊዮስ ቄሳርም እንደዛው፡፡

እንደውም የሱን ካየሀው፤ሽንፈቱ እኮ ነው ‹‹ሚበዛው፡፡

አንቶኒ፡- ስለምታዳላ ለኔ፤የልብህን አታወራም፡፡

እንጂ ዩሊዮስ ከኔ ጋር፤ስሙ በአንድ አይጠራም፡፡

እሱኮ የአቅሙን ተፋልሞ፤ታግሎ ነው ድል የተነሳ

መች እንደኔ - አረ ባክህ አይነሳ!

ቤንቲዴሞስ፡- አታቋርጠው ጨርሰው!

አንቶኒ፡- መች እንደኔ - ጥሎ ሸሸው

የኔማኮ ቤንቲዴሞስ፤ለቅሌቱ ቃል አነሰው

ወታደሮቹ ሲዋጉ፤ጥርስ ለጥርስ ተነካክሰው

ጥያቸው ሸሸሁኝ እኮ፤እንደወኔ ቢስ ፈሪ ሰው!.....

ቸኩለሃል ልትረግመኝ፤እኔም ፈቅጄልሃለው

ለወቀሳም ተዘጋጅተህ፡እንደው የመጣው አውቃለሁ፡፡

ቤንቲዴሞስ፡- ነገሩማ ነበር

አንቶኒ፡- በል እኔም አግዝሃለው - ወንድ ነበርኩ ቤንቲዴሞስ!

ቤንቲዴሞስ፡- ከወንድም ወንድ ነበርክ እሱስ - ግን አሁን

አንቶኒ፡- ተወው- እኔው ልበልልህ!ለማለት የፈለከውን፡፡

ግን አሁን ውቃቢ የራቀኝ

ጀግና አሰዳቢ ከንቱ ነኝ፡፡

የክብሬና ዝናዬ ምርት፤በላይ በላይ ሲከመር

ቁንጣን ተጭኖኝቁጭ ብዬ፤አየሁ በሌላ ሲደፈር

አይደል ማለት የፈለከው

ቤንቲዴሞስ፡- ጨርሰዋ እንደጀመርከው፡፡

አንቶኒ፡- ደስተኛና ትልቅ ነበርኩ!

ዳር እስከዳር የተወደድኩ፡፡

ባላበሻቀጥካትና፤ባላስጨረስካት ትግስቷን

እድል ባልከዳችኝ ነበር ባላዞረችብኝ ፊታን፡፡

ከማሰሪያዋ ፈትቼ፤ሰደድኳት ወጣች ከቤቴ

ግን አልቆረጠችም ኑራ፤መጣች ካንድም ሁለት ሶስቴ፡፡

ንዝህላል ውሎዎቼና፤በቅንጦት ያገኮ አዳሮቼ

ቢያቅለሸልሻትበረረች፤ጥርሳን ትንከስ እስከ መቼ

ይበቃው ያህል ከገፋት፤የማይታክት መልአክ የለም

አሁን ጥላቸው ኩብልላለች፤ላትመለስ ለዘላለም፡፡

እባክህ እርገመኝ ጋደ - ለኔስ ሲያንሰኝ ነው መረገም፡፡

ቤንቲዴዎስ፡- መች ልረግምህ መጣውና

አንቶኒ፡- እንግዲያው ድካምህ ሁሉ፤ ይመስለኛል ከንቱ መና

ቤንቲዴዎስ፡- አቅምህ ከሚችለው በላይ ራስህን ረግመሃል

የውድቀትህም ጥልቀቱ፤ከማንም በላይ ታይቶሃል፡፡

እንደተተነኮሰ ጊንጥ፤ቀድመህ በቁጣ ገንፍለህ

መረዝከውና አረፍከው፤ራስህን በራስ ነድፈህ፡፡

የመርዝ ማርከሻ አምጥቼ፤ነሳንሼ ከቁስልህ ላይ

እገላግልህስ ነበር፤ከዚህ ካለህበት ስቃይ፡፡

አንቶኒ፡- ታደርገው ነበር - አውቃለው፡፡

ቤንቲዴዎስ፡- አደርገዋለሁ!

አንቶኒ፡- ሃ ሃ ሃ ሃ!

ቤንቲዴዎስ፡- ሳቅ ግዴለም!

አንቶኒ፡- ወድጀ እኮ አይደለም - ሃ ሃ ሃ!

ልሳቅ እንጂ - ታዲያ ላልቅስ

የዋህ የወዳጁን ቡድን፤እያየሁ ሲያንቆለጳጵስ

ቤንቲዬሞስ፡- እንግዲያውማ ጌታዬ - ሊያበቃልህ ይመስለኛል፡፡

አንቶኒ፡- አብቅቶልኛል

ቤንቲዬሞስ፡- አላበቃልህም ባይ ነኝ! ይልቅ ሞክር እድልህን፡፡

አንቶኒ፡- አትሰማም እኮ እምልህን

ሞክሬያለሁ ምችለውን፡፡

አብቅቶልኛል የምልህ

ምኑንም ሳላይ መሰለህ?

ላይመለስ፣ ላይፈታስ፣ ሁሉም መጥፋቱን አይቼ ነው

እራሴን ከአለም ደብቄ፣ አለምን የምኮንነው፡፡

አለም ሚሉት ከን ነገር፣ አሁን ልብ ብዬ ሳየው

የሚጠይቀው ክፍያ፣ ከዋጋው እጥፍ ድርብ ነው፡፡

እና ታዲያ- ለምኑ ነው?

ቤንቲዬሞስ፡- ቁሳር እንዲህ አያስብም፡፡

‹‹እነሆ››ብለህ አለምን፣ በሙሉ ልብ ብትሰጠውም

ካቅም ማጣት፣ ሽንፈት እንጂ፣ ከስጦታ አይቆጥረውም ::

እንደ ቺቺሮ ተቀልተህ፣ ባደባይ ትሞታለህ?

እውን ለቁሳር አንገትህን፣ በፈቃድህ ትሰጣለህ?

አንቶኒ፡- ህልመኛ ነህ ልበል እንዴ? - ቤንቲዬሞስ ጤናም የለህ?

ቤንቲዬሞስ፡- ህልመኛውስ እኔ ሳልሆን፣ ይታያል በግልፅ አንተው ነህ!

ሰአቶችህን በዋዛ፣ የፈጀህ እያንጎላጀህ፡፡

አለ ቦታው ፍልስፍና

ድሮስ ለማን ይበጅና?

ስለክብር አምላክ ብለህ -አንቶኒ ነቃ በል ባክህ!

አስራ ሁለት ጋንታ ጦር ነው፣ እንድትመራው የሚጠብቅህ፡፡

ባሳር አስቆጣሪ ጉዞ፣ በኔ መሪነት መጥተዋል

ለራብ ንዳድ ሳይበገሩ፣ ተጉዘው እዚህ ደርሰዋል፡፡

ሐሩር ያንቃቃው ፊታቸው

መጅ ያወጣው መዳፋቸው

የደነደነ ጡንቻቸው- ስታያቸው ጠጋ ብለህ

የጦር አባዜህ ይነሳል፣ ስል ሰይፍህን ትመዛለህ፡፡

ከአካል ብቃታቸው በላይ ፅናቱ የመንፈሳቸው

እኒያ ከበው ሚጠብቁህ፣ ቁሳራውያን ወዮላቸው!

አንቶኒ፡- አሁን የት ነው የተውካቸው?

ቤንቲዴሞስ፡- ከሲሪያ በታች ናቸው፡፡

አንቶኒ፡- ሂድና ወዲህ አምጣቸው፡፡

እነዚህስ በውስጣቸው ፣ ትንሽ ተስፋ ቢጤ አያጡም፡፡

ቤንቲዴሞስ፡- እዚህ ድረስስ አይመጡም፡፡

አንቶኒ፡- ‹‹ እዚህ ድረስስ አይመጡም››?

ታዲያ ምነው ማላገጥህ፣ እየሰጠህ አጉል ተስፋ?

ምሬት፣ ሀዘን፣ሆድ ብሶቴ፣ ነው ይብሱን እንዲከፋ፣

እንግዲያውስ -ጦር ያልካቸው

ዱር አዳሪ አመፀኞች፣ የማይታዘዙ ናቸው!

ቤንቲዴሞስ፡- እሱስ እጅግ ታማኝና፣ ታዛጉቹ ናቸው በፍፁም፡፡

አንቶኒ፡- ሃሃሃ! -ግን እዚህድረስ አይመጡም፡፡

በል ይሄን ፈዝህን አቁም!

ቤንቲዴሞስ፡- የነሱኮ ጥያቄአቸው- ፈጥኖ ይምጣና ይምራን ነው፡፡

አንቶኒ፡- ይሄ ሰው አይምሮም የለው? መከበቤን ረሳኸው?

ቤንቲዴሞስ፡- አታስብ ስለ ከበባው - አንድ መውጫ መንገድ አለው፡፡

አንቶኒ፡- እኔ እንግዲያው ፈቅም አልል፣ ከዚች አሁን ካለሁበት፡፡

ቤንቲዴሞስ፡- ከዚህ የተሸለ ምክንያት ፣ ሳይሹ አይቀርም ምናልባት፡፡

አንቶኒ፡- ‹‹ምክኒያት ››? - ምክኒያትም መስጠት አለብኝ?

እንዲህ አይነት መሪነትስ፣ ባፍንጫዬ ይውጣ ቢቀርብኝ፡፡

እዚህ ድረስ የማይመጡት፣ ለምንድነው? ምን ሆነዋል?

ቤንቲዴሞስ፡- ለክሊዋፓትራ ከሆነ፣ አንፋለምም ብለዋል፡፡

አንቶኒ፡- ምን? - ምን ብለዋል?

ለክሊዎፓትራ ከሆነ፣ ላይዋጉለት ወስነዋል፡፡

በርግጥም እውነት አላቸው፣ ለምንድነው ሚዋጉላት?

ድል በድል ሆና ስታይል፣ይብሱን እንድትሰግድላት?

ይብሱን ባሪያ እንድትሆናት

ላንተ ሲሉ ገድለው ሞተው፣ ሚያስገብሩልህን ግዛት

ቀን ስትዳራትም ሆነ፣ ስታድር ሌሊት አቅፈሃት

አንዴ በሳመችህ ቁጥር፣ አንድ ግዛት ለምትከፍላት?

አንቶኒ፡- ስማኝማ፣ ላስጠንቅቅህ አንድ ነገር

ለሌሎች ድክመቶቼ፣ ያሻህን ሁሉ ተናገር

ግን ከእንግዴህ- ክሊዎፓትራን፣ ብታነሳ ስሟን እንኳን

ገሃነም ነው የምልክህ፣ የዘህ ጦሷን ጥንቡሳሷን!

አንተ እሷን አታውቃትም-

ስለዚህ ካፍህ ጠንቀቅ በል፣ ገደብ አለው ለትዕግስትም፡፡

ቤንቲዴሞስ፡-- አማልክት እስቲ ጉድ እዩ፣ እዚህ ወርዳችሁ አንዳፍታ

ለማን አደራ እንዳላችሁ ፣ የሰውን ልጅ እጣፈንታ፡፡

እዩ፣ አውሮፓን፣ አፍሪካን፣ እሲያን ባንድነት ሆነው

ሲመዘኑ ካንዲት ሴት ጋር፣ መበለጣቸው ደንብ ነው?

አንቶኒ፡- እንግዲህ አታብዛው! ተወኝ!

ቤንቲዬሞስ፡- ገደብ የለሽ ፍቅርኮ ነው፣ እንደዚህ የሚያናግረኝ፡፡

አንቶኒ፡- ‹‹ገደብ የለሽ ፍቅር›› - ገደብ የል ንቀት!

ገደብ የለሽ ድፍረት

ሰዎችህ ብኩኖች ናቸው1 አንተም መልቲ ከዳተኛ!

አሳቢ መስለህ የመጣህ፣ ቅናት ቢልህ አላስተኛ፡፡

እኩያዬ ብትሆን ኖሮ፣ በውጊያው ጥበብ በደረጀህ

ክብሬም በደምህ ሳይጎድፍ፣ዛሬ ነበር መታረጃህ!

ቤንቲዬሞስ፡- ቀጥላ ታዲያ!. .እረደኝ!

ሚብሰውን አርገኸዋል፣ ከዳተኛ አይደል ያልከኝ?

አንቶኒ፡- አዎ ከዳተኛ አልኩህ!

ቤንቲዬሞስ፡ -እኮ ራስህን ባሳየሁህ?

ሁሉ በሆዱ ሚልህን፣እኔ ባፌ በነገርኩህ?

አንተ እንዳልከው ብሆንማ፣ቀናተኛ፣ከዳተኛ

እዚህ ምን ላደርግ መጣሁኝ?- ለሽርሽር ነው በለኛ?

ያንተንስ መራራ ፅዋ፣ማን አስገደደኝ ልቀምሰው?

እኒህን ጀግና ንስሮች፣እየመራሁ ብወስድለት

ያቺን ያልኩህን ማምለጫ፣ቀዳዳ ብሸፍንለት

አክታቢዎስ ያነግሰኛል፣ ሳይውል ሳያድር ያን እለት

ያኔ ነው ከዳሁህ ማለት፡፡

አንቶኒ፡- [ከፋታ በኋላ] ጎበዝ- በቃ ይቅር በለኝ!

ሆድ ብሶት ነው ያሳሳተኝ፡፡

ቤንቲዬምስ፡- አንዴ ተጠራጥረኸኛል፣ ከዚህም ወዲያ አታምነኝም

ስለዚህ -ባክህ ግደለኝ፡፡

ምዘዝ ሰይፍህን! ገላግለኝ!

ለነገሩ- ምን ያደርጋል -ካፍህ የወጣው መርዝ ቃል

የሰይፉን ስራ ሰርቶታል

አንቶኒ፡- ጓዴ ብትረዳኝ ምናለ?

የጭፍን ደም ፍላት እንጂ፣ የመጠራጠር አይደለም

ለዚህ ነው ማረኝም ያልኩህ፣ሰው ሆኖ የማይስት የለም፡፡

አንተስ ቢሆን ከቁስሌ ላይ፣መጎጥህ ምን ይባላል?

ከእሳት ሊያወጣ የመጣ፣ደርሶ በእሳት ይጫወታል?

ቤንቲዬምስ፡-ከልክ ያለፈን ግልፅነት፣ማንም ገገር አይወደውም

ከልቤም ባልፍ ባንተው እንጂ፣በሌላስ አላደርገውም፡፡

ንቀት ይመስልሃል ብዬ

መች ገመትኩና ጌታዬ?

ግንኮ አንተ -የዛሬን አያድርገውና -እንዲህ በፍቅር ሳትታወር

ኩልል ያልክ እንደ ምንጭ ውሃ፣ ነበርክ ቁንጮው የሰው ልጅ ዘር፡፡

አማልክቱም በኪናቸው፣ተጠብበው ሰርተውህ ነበር

አቦ ሰጥ እስኪመስላቸው፣የእንከን አልባነትህ ነገር፡፡

ቅናት የሚሉት እኩይ ዚቅ፣ከአማልክቱም ዘንድ አይጠፋ

እንጂማ ህያው ባረጉህ፣እንደሰው ፈርሶ የማይጠፋ፡፡

ዘላለማዊ አድርገው፣ መለኪያ ባረጉህ ነበር

የትዬለሌ እንዲሆን፣ የሰው ልጅ የብቃት ድንበር፡፡

አንቶኒ፡- ግና ታዲያ -ክሊዎፓትራ

አዬ ጉድ! አዬ መከራ!

እሺ ቀጥል ውድ ወዳጄ -

መቼስ ማጨድ ግዴም አይደል፣ የዘራሁን በገዛ እጄ?

ቀጥል ቀጥል ቤንቲዴሞስ -እየገሰፅከኝ አይደለም?

ማለት ያሻኸውን ሁሉ፣ ቀጥል ንገረኝ ገዴለም።።

ቤንቲዴሞስ፡- በቃ -ምንም ምቀጥለው የለም።።

አንቶኒ፡- ይህ ግልፍተኛ ሜቴ ሳያሰጋህ ለህይወትህ

ጥሞታል መሮታል ሳትል፣ የሆድህን ደፍረህ ማውራትህ

ምስክሩ ነው ለፍቅርህ።።

ሐቀኛ ፍቅር ህንዲህ ነው!

የሌሎቹን ሁሉ ሳየው

የቅቤ አንጓች ሽንገላ ነው።።

ቤንቲዴሞስ፡- ኧረ የፈጣሪ ያለህ! -ምንድነው ምሰማው ያለው?ለዚህ አሁን ለተናገርከው

አምላክ ልብህን ይባርከው!

እንግዲያውማ ጌታዬ -በሙሉ ልቤ እንደገና

እንደምትወደኝ ልመና?

[ፋታ] በላ ጌታዬ - ንገረኛ!

አንቶኒ፡- ጥንትም -ዛሬም -ወደፊትም፣ እወድሃለው እመነኝ! [እያቀፈው]

አድርግ ምትለኝን ሁሉ፣ለመፈፀም ዝግጁ ነኝ

በል እንግዲህ የኔ አንበሳ -የድሉን መንገድ ጠቁመኝ

እስከዛሬም አንተው ነበርክ፣ ለንግዲሁም አንተው ሁነኝ።።

ቤንቲዴሞስ፡- ትተዋታለሃ ጌታዬ? -ማለቴ የቺን -ይቺን. . .

አንቶኒ፡- እንዳትዘልፋት አደራህን!እንግዲህ መቼም ቃል ቃል ነው -እቀጣዋለው ክስህን።።

ምንም እንኳ የማፈቅራት፣ ከህይወት በላይ ቢሆንም

ከድል በላይ፣ -ከግዛት በላይ፣ -ከሃገር በላይ ቢሆንም

ከውዱ ክብሬ እንኳ ሳይቀር -ከሁሉ በላይ ቢሆንም

ተዋታለሁ እንደምንም።።

ቤንቲዴዎስ፡- ኅ. . .ሽ! -አሁን ገና አስደሰትከኝ!

ጌታዬን ጌታዬን ሸተትከኝ።።

እንዋጋለን ማለት ነው?

አንቶኒ፡- ጠርጠሩስ ለምንድነው?

መሰንበትን የመሰለ፣ ደግ ነገር መቼም የለም

ዳግም ጥሩሬን ለብሼ፣መጣሁለት ይሄን አለም!

ቤንቲዴዎስ፡- የሄ ነው ክጥንት የማውቀው

ድምፁ መንፈሱ የጀግና።።

ፈጣሪ ምስጋና ይግባው -ከተኛበት ቀና ብሏል

አጉል አጥጦ የቆየው፣ አክታቢዎስ ጉዱ ይፈላል!

አማልክት ሆይ -ተለመኑኝ!

ያቺን ቀን ለማየት አብቁኝ!

ከዚያ በኋላ የምኖረው፣ መቶ አመት እንኳ ቢኖረኝ

ሰርዙት አልፈልገውም፣ ለለውጡ ፍቃደኛ ነኝ።።

አንቶኒ፡- አወይ ክሊዎፓትራ! —

ቤንቲዴዎስ፡- እ -የ -ፈጨ ጥሬ. . .!

ኧረ ምን ተሸለ ዛሬ? -አሁንም እዛው ነህንዴ?

አንቶኒ፡- ሙግት ይገፍ ነው ከሆዴ. . .

እፎ. . .ይ! -ይኸው ወጣችልኝ በቃ፣ በረረች ለቃ አንጀቴን!

አያምጡ ምጥ አምጬ፣ ተገላገልኳት ሞት ሞቴን።።[ፋታ]

የወደደን ሰው ማስገደድ -እንዲርቅ ውዴ ከሚለው

ወንድ አይደለሁም አንቶኒ፣ቄሳር በቁምህ ባታየው!

ቤንቲዬሞስ፡- ተመስገ . . .ን! ነቃ መንፈስህ፣ ሞቶ ቀዝቅዞ የነበረ

አይኖችህ ትንታግ ረጩ! -ትንፋሽህ ይፋጅ ጀመረ!

አንቶኒ፡- ለኮስከኝኮ ነው ምልህ! በደም የገር ሰይፍ ሸተተኝ

የጠላት ብልቱ ራሳው፣ ዙረያዬን ተዘርቶ ታየኝ፡፡

ዳግም ታድሶ አባዜዬ እየናጠኝ ነው በብርቱ

የ ከውጊያ አውድማ ገብቶ፣ የመፋለም ፍላጎቱ

ነፍስን ከስጋ በጦር መንሸ፣የማበራየት ስሜቱ

ቤንቲዬሞስ - ሸረ ስንቱ!

ትዝ አይልህም ያን ጊዜ፣ ወደቃሲዮ ቶር ሰፈር

እንደ ሰደድ እሳት ሽቅብ፣ ስምዘገዘግ ስወረወር

ፈረስ ሆኝ የጋለብኩት፣ እንዲህ አይነቱን ዛር ነበር፡፡

የዝንጆሮ አሳር ሚሉት፣ የኮረብታው አቀበቱ

ሊያዘገየኝ እንኳ አልቻለም፣ለመድረስ ካሰብኩበት፡፡

ጦራቸው ባናቱ ዙሪያ፣እየዘፈነ ቢጠጋኝ

እንደ ጃርት እሾህ ጋሻዬን፣ ምሽጋቸውን ሳምሰው

ሜዳውን አልፎ የመጣ፣ አንድም አልነበር የኔ ሰው፡፡

ቤንቲዬሞስ፡- አቤቱ ኃያል ፈጣሪ! ለዚች ሰአት ያበቃኸኝ !

የልን አርገህልኛል-ከእንግዴህ ሌላም አልመኝ

አንቶኒ፡- አይዞህ እንግዲህ ገሞራው!

ሰይፍና ልባችን እንደሁ፣ ያው እንደቀድሞው አንድ ነው

ዳግም ከጠላት ለመግጠም፣ችኮላየየ ልክም የለውኝ

እኔና አንተ ጦራችንን፣ እንደ ጊዜና ሞት መርተን

መራውን የእድል ዕዋ ፣ ሳይወዱ እንግታቸዋለን!

ይታጨዳል! ይከመራል! ማን ብሎን ለጦር ግብርናው!

ምርታችን ዝቅም ብሎ አያውቅም፣የዘንድሮው ከአምናው።።

በል ና ተከተለኝ ጀግናው!
[እየወጡ ሳሉ መብራት ይጠፋል]

ገቢር 2

[ክሊዎፓትራ፣ አይራ፣ አሌክሳስ። በክሊዎፓትራ ቤተመንግስት]

ክሊዎፓትራ፡- ምንድነው ሚውጠኝ አሁን? -ወዴት ነው ፊቴን ማዞረው?

ቤንቲዩዎስ ጉድ አርጎኛል፣ በቃ አንቶኒ መሐዱ ነው!

አሌክሳስ፡- ቢሐዱስ? -ሚዋጋው እኮ ላንቺው ነው።

ክሊዎፓትራ፡- እንዲያ ቢሆንማ ሲሄድ፣ በተሰናበተኝ ነበር።

አሌክሳስ፡- እውን -ይሐ ደካማ ልብ ነው

ኃያሏን ንግስት የሆነው?

ክሊዎፓትራ፡- ኤዲያ! እኔ ብሎ ንግስት! -እንዲህ ነው እንዴ ንግስትነት?

በኒህ አንጓጣጭ ሮማውያን፣ዙሪያ ተከበቦ መጎለት?

እስኪጠፈሩ መጠበቅ፣ በድል አድራጊው ሰንሰለት?

እኮ እንዲህ ነው መንገስ ማለት?

ለነገሩ -ይሄ ሁሉ፣ ቅንጣት አያስጨንቀኝም!

ማርክ አንቶኒን ካጣሁ ወዲያ፣ ሌላው ሌላው አይገርመኝም።

ስለዚህ - ና አክታቢዮስ! የማጣው የለም ከእንግዲህ!

የምርኮኛ ሰንሰለቱን አዘጋጅና ና ወዲህ!

የጥንቸል ያህል እንኳ ምታስፈራኝ እንዳይመስልህ!

አይራ፡- ግራና ቀኙን ብታይው፣ ትንሽ ይረዳሻል ባይ ነኝ።

ክሊዎፓትራ፡- የማየውም ነገር የለኝ!

የምን ደግሞ ግራና ቀኝ? -እኔኮ አሁን እብድ ነኝ!

እብደቴ ግን የመደዴ፣ ሳይሆን የተራ ተትንሽ ሰው

የሰማይ ኮከብ ወዳጄ፣ የምድሩን መተዋ ነው።

ምጥን ሀዘን የሚገጥመው

ከመደዴ አፍቃሪና ከተራ ተፈቃሪ ነው።

አየሽ -ምናልባት ያኔ ነው፣ግራ ቀኝ ማየት ሚቻለው፡፡

የኔ ፍቅር ግን ምድራውዊ፣ ሳይሆን በዋዛ ሚታረቅ

ከሰማይ ሰማይ የሚናኝ፣ ጡዘት ነው የማይታወቅ፡፡

ምናለ አሁን እዚህ መጥቶ፣ እንዴት ሂኜ እንዳለሁ ቢያየኝ፡፡

ሁኔታዬን ቢመለከት፣ ይመስለኛል የሚያዝን?

አአ! - መሄዱ እንኳን ግድ ቢሆን

የሚጨክን ሆድ የለውም፣ ልቡ ገር ነው እንደ ህፃን

አውቀዋለሁ አንቶኒዬን፡፡

አያይ. . . አላውቀውም ኧረ!

እርግጥ ነው -አውቀው ነበር፣ ያ ግን ድሮ ቀረ፡፡

አይራ፡- አንቺስ አንዴ ጨክን ብለሽ፣ ብትተይው ምናለበት?

እርሺው ባክሽ የኔመቤት፡፡

ክሊዎፓትራ፡- የማይሆን ነው የኔ አደራ፣በፍፁም የማይሞከር

የዛሬን አያርገውና፣ ይህ ሰው እኮ የኔ ነበር፡፡

ታዲያ አሁንም -ትንሽ ትንሽ -የኔው የኔው ይመስለኛል

ምን አንጀት ይቆርጥልኛል?

አሌክሳስ፡- እንደ ጨካኝ -ተለዋዋጭ -ምስጋና ቢስ ግዴለሽ ሰው

ብትቆጥሪው ነው የሚሻለው፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ይህንስ ከቶም አልችለው!

ብችለውም ትርጉም የለው፡፡

ተለዋዋጭ፣ ጨካኝና፣ ምስጋና ቢስ እንኳ ሲሆን

መጥላት አልችልም አንቶኒን፡፡

(<u>ቻርሚዮን ትገባለች</u>)

እ. . . ሺ የኔዋ ቻርሚዎን- ምን ዜና ይዘሽልኛል?

ቻርሚዎን፡- ገና ከመድርሴ ነበር፤ ያገኘሁት የኔ እመቤት

ክሊዎፓትራ፡- እያዘጋጀሽው ነው ገና፣ ሰፊ ንግግር አንቺ ሴት?

በጎ ቃል አምጥተሽ እንደሁ፣ ወዲህ በይ ስጪኝ በፍጥነት!

አይራ፡- እንደሚያፈቅርሽ ግልፅ ነው

መልክቱን እስክትሰሚ፣ መታገሱ ነው የሚሻለው፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ራርቶልኝ ቢሆን ኖሮ፣ ገና አፏን ሳትከፍተው፣ ዐይኗ በነገረኝ ነበር

ቻርሚዮን፡- ልንግርሽ ነውኮ ያለሁት

እንዳልኩሽም እንደረስኩ አገኘሁት የብረት ሀውልቶች ከበውት፡፡

እመቤቱ የብረት ሐውልቶች እንጂ በጭራሽ ሰውች አይመስሉም

እንደ ድንጋይ ግኡዝ መስለው ከበው ቆመው ነበር ሁሉም፡፡

ማለቴ ባለሟሎቹም፣ ወታደሮቹም፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ኧረ ምነው ቻርሚዎን ነገርሽ ማጠር አይችልም?

ቻርሚዎን፡- ልነግርሽ ፈልጌ እኮ ነው፤ ከሥር ዘርዝሬ ሁሉንም፡፡

እናም- ሁኔታውን ሳየው መቁረጡን ሳይቆርጥ አይቀርም

ግን በውሳኔው የረካ፣ የተደሰተ አይመስልም፡፡

ለማለፍ እየተጋፋሁ፣ ከሰዎች መሃል ሲያየኝ

እንዴት ፊቱ ከመቀፅበት፣ እንደቀላ አትጠይቂኝ

ወዲያው ነበር ያዘዛቸው መንገዱን እንዲለቁልኝ፡፡

አሌክሳስ፡- ይሄም ጥሩ ምልክት ነው ንግስት ሆይ ልብ በይልኝ፡፡

ቻርሚዎን፡- ቤንቲዬሶስ ሆዬ ታዲያ ቆሞ መሐል መንገድ ላይ

እንዴት ግንባሩን ከስክሶ እንደሚገላምጠኝ ሳይ

ልመለስ ምንም አልቀረኝም፣ ፊርቼ ክፉ እንዳይቃጣው

ግን እሱም ሳይወድ መንገዱን ለቆልኝ ዞር አለ ወዲያው

እኔም መልክቱን ወዲያው አንድ ባንድ፣ ሳልቀንስ ወይም ሳልጨምር

ከአፍሽ የወጡትን ቃላት፣ አነበንባቸው ጀመር፡፡

በመጨረሻም ሳነሳው፣ አሳዛኙን ጥያቄሽን

‹‹ከመሄዴ በፊት አንዴ፣ ዐይንህን ልየው›› ማለትሽን

ወደ ውስጡ አቃሰተ፣ የሰማ ይመስል መርዶሽን፡፡

ምነው ባየሽው ሐዘኑን፣ በጠራሁ ቁጥር ስምሽን፡፡

ያ አንቶኒ እንዳይመስልሽ፣ ሲያዩት የሚያንቀጠቀጠው

በፊቱ ወላፈን ብቻ፣ አንድ አገር ጦር የሚንጠው

በሙሉ ዐይን እንኳን ሳያየኝ፣ አቀርቅሮ ነው የቆየው፡፡

እንደዘበት አስመስሎ፣ ዐይኑን በጣቱ ቢነካው

በመዳፍ ተከልሎ፣ ጠብ ሲል አየሁት ዕንባውን፡፡

እንዳይታይበት ነው መሰል- አድበሰበሰው በጫማው፡፡

ክሊዎፓትራ፡- አለቀሰ ነው ምትይኝ ዕንባውን አፈሰሰልኝ?

እንዲህ የሚያስደስት ሌላ ከሌለሽ ምታወሪልኝ

በፈጠረሽ ቻርሚዎኔ እዚሁ ላይ አቁሚልኝ፡፡

እና ደስ እንዳለኝ ልሙት!

የእቅፌንስ አስለቀቁኝ- የልቤን ግን ምን ሊያደርጉት?

ቻርሚዎን፡- በመጨረሻም ያሳዘዘኝ፣ ለእመቤቱ እንድነግርሽ

አቅሙን እንዳያምነው ነው- እናም ከቆመ ከፊትሽ

ጥያቄሽ ምን ከባድ ቢሆን፣ አንደማይችል እምቢ ሊልሽ፡፡

ስለዚህ. . .

ክሊዎፓትራ፡- አያይሽም ልትይኝ ነው

ቻርሚዎን፡- ስለዚህ ልቋቋመው፣ የማይችለውን ሀይለሽን

ላትጠቀሚ በዕኑ፣ ለምኖሻል አደራሽን

በተረፈ ላንቺ ያለው፣ ታላቅ ግምት እና አክብሮት

እንድገልፅልሽ አዞኛል፣ ሁሌም እንደሚኖር አብሮት፡፡

ክሊዎፓትራ፡- እውን አንቶኒ ይህንን፣ ለክሊዎፓትራ ይላታል

‹‹አክብሮት››- አለ? ይገርማል!

ውሃ ውሃ ሚል ባዶ ቃል!- ኧረ እንደምን ያፀይፋል!

ያለመልኩ ያለቦታው ደርሶ ከሚሰነቅረው

ምን አለ ቃሉ ለሚገባት፤ ለአክታቪያ ቢያኖረው!

አሌክሳስ፡- ፍርድ እያዛባሽ እኮ ነው፡፡

የፍቅር መነፅር አርገሽ፣ ሁሉን በዚያ ውስጥ ካየሽው

በጎው ክፉ- ክፉው በጎ፣ እንደሚመስልሽ አትርሺው፡፡

ውሃ ውስጥ ገብቶ ስናየው

ቀጥተኛው ነገር እንኮን፣ ውልግድግድ ያለ ሚመስለው- ለዚሁ ነው፡፡

እና ለኔ ፍንትው ብሎ ያለእክል እንደሚታየኝ

ከእመቤቱ ፊት ለመቆም፣ የፈራ ባሪያ ነው ባይ ነኝ፡፡

በቀላሉ ተስፋ ቆርጠሽ፣ ካለቀቅሽው አያመልጥም፡፡

ገና በጥሶ ያለጣለው፣ የፍቅር ሰንሰለትሽም

እርቆሽ እንዲሄድ ፍፁም፣ የሚያስችለው አይመስለኝም፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ምነው ባመንኩ ደስ ባለኝ!

አሌክሳስ፡- እኔ ግን እርግጠኛ ነኝ - ይህ ሠው በፅኑ ማፍቀሩን፡፡

ምንም ከሁለት ቢወጠር፣ ፍቅሩን ይደግፍ ወይ ክብሩን

ከራሱ ጋር ሸንጎ ይዞ፣ መስጠት ቸግሮታል ፍርዱን፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ፊቴ ቁሞ አይኔን ማየት፣ እንደሚያሰጋው ላከብኝ፡፡

አሌክሳስ፡- ከዚህ በላይ ምን ፍንጭ አለ? ምን ነው ንግስት- ምን ሆንሽብኝ?

ፍልሚያውን ይቅርብኝ የሚል፣ ደካማነቱን ቢያምን ነው

ስለዚህም አንቺም ያለብሽ፣ እድልሽን መጠቀም ነው፡፡

የላከብሽ መልክት እኮ፣ ምንም እንቆቅልሽ የለው

‹‹ነይ ባክሽ ገላግይኝ- ክሊዎፓትራ ድረሽልኝ- ከቤንቲዬዎስ አስጥዱኝ-

ብቅ ብለሽ እይኝ እና፣ እንድተወው ሠበብ ሁኚኝ›› ማለቱ እኮ ነው- እመኚኝ!

[የጥሩንባ ድምፅ ይሠማል]

ይሄ ጡሩንባ የሱ ነው- በዚህ ማለፉ አይቀርም-

ይቅርታ አድርጊልኝ እና፣ አንዴ ገለል በይ ግዴለም፡፡

ኋላ እንዳያስቸግርሽ-

መጀመሪያ እኔ አግኝቼው፣ መንፈሱን ላስተካክልልሽ

ክሊዎፓትራ፡- እንደሚመስልህ እንድተርመራኝ፣ ስልጣኑ በእጅህ ይገኛል

ግን እንጃ- ነገሩ ሁሉ፣ ከንቱ ድካም ይመስለኛል፡፡

[ቻርሜዎንን እና አይራን አስከትላ ትወጣለች]

አሌክሳስ፡- እሱስ እኔም አስግቶኛል፡፡

ባረጋጋሽ ብዬ ነው እንጂ፣ ጨለማው ለኔም ታይቶኛል፡፡

ግን ያለን መንገድ ይሄው ነው፡፡

የእድል ፋንታ ነው የቀረው፡፡

[ይወጣል፡፡ የሮማውያን መጥረቢያ አርማ የያዙ አጃቢዎች ይገባሉ፡፡ አንቶኒ እና ቤንቲዲዎስ ሌሎች ባለሟሎች አስከትለው ይገባሉ፡፡]

አንቶኒ፡- አክታቢዮስ እኔ ሳውቀው- ይህ ነው የሚባል መዓም የለው

በደፈናው- የእድል እና፣ የአቦሰጡኝ ጎተራ ነው፡፡

አንቶኒ፡- እኔ ምለው- ማስታወሻም የለኝ?

አሌክሳስ፡- እንዴት አይኖርህ ጌታዬ- ይኸው እኮ ልሰጥህ ነኝ፡፡

ውድህ ባሪያህ ንግስቲጡ-

አንቶኒ፡- እመቤቴ!

አሌክሳሰስ፡- ደህና- እመቤትህ ንግስቲቱ- እንደፍላጎቷ ቢሆን፣ ቢሞላላት የፍቃዷ

በላከችልህ ነበር፣ ልቧን አውጥታ ከሆዷዷ፡፡

ይህን ማድረግ ባይቻላት- የራስዋ አርማ የሆነውን

የሚደሙ ልቦች ቅርፅ፣ የተለበጠ ዙሪያውን

እንቁ አንባር ነው የላከችው፣ እነሁ ተቀበለኝ አሁን፡፡

[አንባሩን ይሠጠዋል]

ቤንቲዬሶስ፡- እረባክህን ጌታዬ- በክብር ስም ይሁንብህ

እሱ ነገር ያጠፈሃል፣ እንዳትነካው ይቅርብህ!

እልቆ መሳፍርት ሰቆቃ በውስጡ እንደየዘ እወቅ

ዋ ከጫፉ ትደርስና፣ መዳኛም የለህ ተጠንቀቅ!

ይሄ አንተ በበግ ልብህ፣ ‹‹ማስታወሻ›› የምትለው

በላኪው የተቀመመ፣ መዳኒት አልባ መርዝ ነው፡፡

አንቶኒ፡- ኤዲያ- ቤንቲዬሶስ ደግሞ፣ አንዳንዴ ታበዛዋለህ

የጨዋ ሴት ልጅ ስጦታ፣ ክብር እንደሁ ማን በነገረ!

ቀድሞ ነገር ከሷ መጥቶ፣ እኔ አልቀበልም ልል?

ምነው እዚህ ሲጥ የማልል!

ሌሊቱ መጫኛ ሲሆን፣ ደዳግም ማይነጋ እስኪመስኪመስለኝ

ለያንዳዷ ሚጢጢ ፈርጥ፣ በአምባሩ ላይ ለምትገኝ፣ የምነግራት ታሪክ አለኝ፡፡

የኔና ክሊዎፓትራ- አይደለም ለሰው ሚወራ

እነግራቸዋለሁ ለእኒህ፣ አዕላፍ ፈርጦች በተራ፡፡

ታዲያ- ይሄን ብቀበለው

ክብር እንጂ ጉዳት አለው

አሌክሳስ፡- በጭራሽ- ጌታያ ምነው ፍቅርኮ ጡሩ ብዙ ነው፡፡

አንቶኒ፡- [አምባሩን እጁ ላይ ለማሰር እየሞከረ] ገርማል!

የጦር ሰዎች ስንባል፣ ብዙ ነገር ይጎድለናል

ጥቃቅኖቹ ነገሮች፣ ይብሱን ያስቸግሩናል፡፡

እስቲ ባክህ አስተሳስረኝ- [ለአሌክሳስ]

አሌክሳስ፡- በሆነልኝ ምን ቸገረኝ!

እነዚህ ረቂቅ ነገሮች

መች በጅ ይላሉ ለወንዶች

እኔ እንኳን ወንድ የማልሞላው

እንዲህ አይነቱ ነገር ላይ፣ ጥፍት ነው ሚለኝ መላው፡፡

ይልቅስ- አንድ ሃሳብ አለኝ!

ጌታዬ ደፈርክ ባትለኝ

አንቶኒ፡- ምንድነው እሱ ንገረኝ፡፡

አሌክሳስ፡- እንግዲያውስ- ጌታዬ ሆይ፣ ይህን ማድረግ የማይሳናት

መላቅጡን የምታውቀው፣ የላከችው ሰው ብቻ ናት፡፡

እግዚኦ ሞት! አለቀልህ!

ይህ ሾተላይ ጃንደረባ፣ ጉድጓድህን ነው የማሰልህ1

ምነው ጌታዬ፣ ምን ነካህ ምኔ ምኔ ዘነጋኸው

በጭራሽ አይኗን እንዳታይ፣ አልነበር የተስማማነው

[አሌክሳስ ለተላላኪው ሹክ ይለዋል፡፡ ተላላኪው ይወጣል]

አንቶኒ፡- ለስንብት ብቻ እኮ ነው፡፡

ቤንተዬሞስ፡- እንግዲያውስ ውሃ ስወቅጥ፣ ነበራ የሰነበትኩት

ከምኔው ያልኩህን ሁሉ፣ አፈር ከተትከው በሞትኩት

አይ አንቶኒ! -በቃ ተያዝክ፣

እግር ተወርች ተተበተብክ!

ከእንግዲህ አንተን ለመጣል፣ አያሻም የቄሳር ጦሩ

አይ ዐይኖቿ ወንድነትህን ፣ ነቅለው ሲጥሉት ከስሩ!

አንቶኒ፡- በክንቱ ነው የምትሰጋው - እኔ አቅሜን መች አጣሁት

ውሳኔዬ ውሳኔ ነው፣ አይቀየርም አንዴ ያልኩት፡፡

ልመስላትም አልፈልግም፣ ጋጠወጥ ያልሰለጠነ

አሳዳጊ የበደለው፣ እድገቱ አግድም የሆነ፡፡

ሮማዊ እንደመሆኔ፣ ስርአቱም የሮማዊ ነው

መልካም የእንግድነት ጊዜው፣ አልቆ ሊሄድ ሲል አንድ ሰው

አመስግኖ መሰናበት፣ በጨዋ ደንብ ተገቢ ነው፡፡

ቤንቲዴዎስ፡- ‹‹አቅሜን መች አጣሁት›› አልከኝ - እሱን ነው ያልተራደኸው

ማርክ አንቶኒ- ያንተ አቅም፣ ለሷ ሳይሆን ለሌላ ነው፡፡

አንቶኒ፡- የቺው መጣች!- ይታይሀል

ምን ያህል እንደተሳሳትክ፣ አሁኑኑ ይገባሃለል፡፡

ተመስገ. . . .ን ፈጣሪዬ ሆይ! - በጣም እንዳልፈራሁ ሁሉ

አሁን ሰአቷ ስትደርስ፣ ስጋቴ ሁሉ መቅለሉ፡፡

ቤንቲዴዎስ- እንዲሁ ነው፣ አደጋውን ያጋነንነው፡፡

ቤንቲዴዎስ፡- አይ ምነ. . .ው! - ማለቂያውን መች አየነው

[ክሊዎፓትራ ቻርሚዎንን እና አይራን አስከትላ ትገባለች]

አንቶኒ፡- እ. . .ሺ ማዳም! - ይኸው እንግዲህ ተገናኘን፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ‹‹ተገናኘን››?- ይህን ቃል ምን አመጣው?

ምንለያይ ነን ማለት ነው?

አንቶኒ፡- እሱ አይቀርም- የግድ ነው፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ማነው የግድ ነው ያለው?

አንቶኒ፡- እጣ ፈንታ ሚባለው፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ታዲያ- እጣፈንታችንን፣ የሰው ልጅ ዋና ተግባሩ

የአለም ህዝብ፣ ሳር ቅጠሉ፣ ምነው በኛ ተሰማሩ?

አንተ ራስህ እንኳንሳትቀር፣ ከቀሩት ጋር አብረህ

በኔው ላይ ነው የተነሳህ፣ እንዲህ ሽንጥህን ገትረህ!

አንቶኒ፡- እንደማያስወቅሰኝስ፣ የማደርገው ነገር ሁሉ

ሚመጡት ትውልዶችና፣ አሁንም ከኛ ጋር ያሉ

ምክኒያቴን ይረዳሉ፡፡

ስለዚህ- አሁን አድምጪኝ

አንዲት ሀሰት ከሃቁ ጋር፣ ከቀላቀልኩኝ አቋርጪኝ

አሊያ ግን- ፀጥ ረጭ ብለሽ

ምነግርሽን ትሰሚያለሽ፡፡- ገባሽ?

ክሊዎፓትራ፡- አዎ ጌታዬ- ታዛኜ ነኝ

ትንፍሽ ካልኩኝ ትንፋሽ ይንሳኝ

ቤንቲዴዎስ፡- [ጉምጉምታ] ጎሽ ይዜን ነው የምወደው

ስልጣኑን እያሳየ ነው፡፡

አንቶኒ፡- ውድቀቴ፣ ጥፋቴ የመጣው፣ ፣ካንቺ ብቻ ለመሆኑ፣ በቂ ምክንያት ስላለኝ

ክሊዎፓትራ፡- ጉዴ ፈላ ፈጣሪዬ!- አጥፊዬ ነሽ ነው የምትለኝ?

አንቶኒ፡- አሁን ቃል ገብተሽ አልነበር፣ ፀጥ ብለሽ ልታዳምጭ?

ገና ጫፉን እንኳን ሳልይዝ፣ ለምንድነው ምትበጠብጭ?

ክሊዎፓትራ፡- እሺ ጌታዬ- ይቅርታ

አላስችል ቢለኝ እኮ ነው- በሆንክ በኔ ቦታ፡፡

አንቶኒ፡- ገና ግብፅ ውስጥ ያየሁሽ ለት፣ ነበር የወደቅሁ በፍቅርሽ

ግን አንቺ ልብ አላልሽው፣ የዛኔ ልጅ ስለነበርሽ፡፡

ይህ የሆነው- ቁሳር ባይኑ፣ አይንሽን ሳያይ በፊት ነው፡፡

አባትሽንም ከዙፋኑ፣እንዲመለስ ያደርግኩት

ላንቺው ስል እንደነበረ፣ በራስሽ ጊዜ እንዲገባሽ፣ ነበር ሳልነግርሽ የተውኩት፡፡

በዚህ መሃል -ቁሳር መጥቶ፣ በስስት እጆች ቀጠፈሽ

ቀንበጥሽ ከማጎንቆሉ፣ ለጋ፣ እንጭጭ፣ ጮርቃ ሳለሽ፡፡

ታዲያ አዛኜም ከመሆኑ፣ ባለጊዜ ነበረና፣ ልቀናቀነው አልቻልኩም፡፡

የኔ ልትሆኚ ሲገባሽ፣ የሱ ለምን ሆንሽ አላልኩም፡፡

ይሄ ሁሉ ሆኖ እያለ- የሮም ጠላት በሆነችው፣ ቺሊቺያ ውስተጥ ባይሽ

ከሮም አንቺ ትብሽ ብዬ፣ የቅርታ አደረግሁልሽ

ክሊዎፓትራ፡- [በማቋረጥ] ለዚህ አሳማኝ ምክኒያት፣ በዚያውም አለት በዚያውም ሰአት

አቅርቤ መስሎኝ ምናልባት

አንቶኒ፡- እንደገና ቃል አፈረስሽ፣ ምላስሽ አልያዝ አለሽ!

‹‹ትንፋሽ ይንሳኝ›› ብለሽ ምለሽ ?. . .

አመት አይደለም ማወራው፣ እና ስሚኝ ፀጥ ብለሽ

የሆነው ሆኖ- እንዳልኩሽ፣የማይመስል ምክንያትሽን፣ ከመቀበልም አልፌ

በቁሳር እንደተበከልሽ፣ አስገባሁሽ በእቅፌ፡፡

ከዚያማ ምኑ ይወራል- አብሬሽ ወደ ግብፅ ወረድኩ

ራሴን ከአለም ደበቅኩ

ከእንግዲህ ቀሪ እድሜዬን፣ አለሜ አንቺ እንደሆንሽ፣ለሰማዩም ለምድሩም ማልኩ፡፡

ቤንተዴዎስ፡- አዎ! - አንድ ሰው ግፉን ከስሩ

ሲያፍረጠርጠው ነው ጥሩ፡፡

አንቶኒ፡- የመውደዴንማ ልኩን- እኒያ ጊዜያት ይመስክሩ!

ቀኑና ሌቱ ያን ጊዜ፣ በተራ ሚቀይሩ

ይመስል ነበር፣ የኔን ፍቅር፣ ለማየት ሲፎካከሩ፡፡

ቀን ፀሃይቱ፣ ሌት ኮከቦች

ሆነው የኛ ተመልካቾች

ላንዲት አፍታ ያህል እንኳ፣ ጋብ ሳይል ፍቅሬ ኃይሉ

ስጋዬ ስጋሽን ሳይሆን፣ ነፍሴ ነፍስሽን ማፍቀሩን፣ ምስክሬ ይሆናሉ፡፡

ከተገናኘን ጀምሮ፣አንዷንም ቀን ሳላሰልስ፣ ነግቶ፣ መሽቶ፣ እስኪነጋ

በጋው አልፎ ሲሆን ክረምት፣ ክረምት አልፎ ሲሆን በጋ

ቀናት በነንዱ ቁጥር፣ ፍቅሬ ጭራሽ እያየለ

ነፍሴ ነፍሰሽን ባይጠግበው- ያኔ አወኩ ካንቺ ካልፎ፣ ሌላ አለም እንደ ሌለ፡፡

ቤንቲዬሞስ፡- ክፉና ደጉን መለያ፣መስሪያ ቢኖር ምን አለ!

አንቶኒ፡- ይሂን ጊዜ- የበፊትዋ ባለቤቴ፣ ፋልቪያ ቅናቷ አየለ

ባል ተብየው ሌላ ሲወድ፣ የማይቀና ሴት ማን አለ?

የሮማ ምድር አውካ፣ አቆመችው ባንድ እግሩ

ካልተመለሰልኝ ብላ፣ ባለቤቴ ወደ አገሩ፡፡

ቤንቲዬሞስ፡- [ጉምጉምታ] ቢሆንም- ንቅንቅ አላልክም፡፡

አንቶኒ፡- ተኝቼ ሳለው ከእቅፍሽ ውስጥ፣ አለም አንድ ሁለት እያለች

እንደ አጃ ሊጥ ከጭብጤ፣ ወጣች እያፈተለከች፡፡

ብቻ- ባጭሩ ብነግርሽ

የያዝኩት ሁሉ ያጣሁት፣ ስንከባለል ነው ከስርሽ!

እድሜ ላንቺ እና ለፍቅርሽ!

ቤንቲዬሞስ፡- [ጉምጉምታ] ጎሽ - እስቲ እንዲህ ንገራት

እንደው ምን አልባት ቢገባት፡፡

ክሊዎፓትራ፡- አሁንስ እኔ ብናገር?

አንቶኒ፡-	ትቺያለሽ- ከደባለኩህ ሐሰት ነገር፡፡

አሊያ ገና ይቀረኛል. . .

ጥሩ- እንግዲያውስ ዝምታሽ፣ ቀጥል ማለት ይመስለኛል፡፡

ፋልቪያ በኔው ምክኒያት፣ በግና ጤሳ ነዳ ስትሞት

ለአለም ሠላም ይበጅ ብዬ፣ የኦክታቢዎስን እህት፣ ኦክታቢያን አገባኋት፡፡

በወጣትነት ኩራትዋ፣ ገና በሚያብብ ውበትዋ

ወቅት ነበር ለዛች ልጅ፣ ሆንኩ የህግ ባለቤትዋ፡፡

ብዙም አልቆየ- ጠራሽኝ

ፍቅሬ ታገዘሽ- ኦክታቪያ፣ ጥያት ወዳንቺ መጣሁኝ፡፡

ይህ ቢያስቆጣ ሮማውያኑን- አብሶም ቄሳራቸውን

አድነው የእጄን ለሰጡኝ፣ አነሱብኝ ጦራቸውን፡፡

አህ! ክሊዎፓትራ- ምን ያላደረክሽኝ አለ?

ልፋለማቸው ያቀድኩት፣ የተሸለ ሀይል ባለኝ፣ በየብስ ውጊያ ሆኖ ሳለ

በባህር ካልሆነ አልሸኝ

በባህር ስገጥም ደግሞ፣ ማሃል ውጊያላይ እያለው፣ ኤሁ ስትሸሺ ጥለሺኝ፡፡

ያቺ ሠዓት ናት ቁስሌ! ቅሌት የተከናነኩበት!

አንቶኒ ነቴ ከላዬ፣ እንደ ጤዛ የተነነባት!- አምላክ የረገማት ሠዓት!

ሸሸው!. እኔ ማርክ አንቶኒ ሸሸው!- እግዚዎ ውርደት! እግዚዎ መአት!

እንዴት እንደሆ አላውቅም- እንዴት እንደተከተልኩሽ

ጦሬን አውላላ ባህር ላይ፣ ያላዛኘ አጋኘ በትኜ፣‹‹መጣሁልሽ ቆይኝ›› አልኩሽ፡፡

ቤንቴዲዎስ፡-	ምኔ ምኔ እንደተዘረጋች፣ የመርከቦን ንፋስ ሸራ!

እሱስ ይቅር- አይወራ፡፡ ጥላን መሸሸዋ ሳያንሳት፣ ወጉስ ለምን ይቅርባት?

ከሀይላችን ላይ ግማሹን፣ ይዛ ሔደች እንዲያጅባት፡፡

ኧረ ንገራት- ንገራት!

አንቶኒ፡- አየሽ ውዷ ክሊዎፓትራ- ይህን ሁሉ አደረክሽኝ

ሳልሞት በቁሜ ቀበርሽኝ!

አሁን ምንቀረሽ እንግዲህ፣ ከዚህ ወዲያ ምንታረጊኝ?

ዳግመኛ ፈጥረሽ ትገይኝ?. . .

ቀረኝ ምለው ጓደኛዬ፣ ይህ ታማኝና ደግ ሠው

ነው የእድሌን ስብርባሪ፣ ከየተበታተነበት፣ እየለቀመ ያደሠው፡፡

አስራ ሁለት ጋንታ ጦር ነው፣ ከዚያ ሁሉ ሀይል የቀረኝ!

ከሞት ማንሠራራት ታህል፣ እንኳን እድል እንዳይኖረኝ

መጣሽ አይኖችሽን ይዘሽ፣ ዳግም ልታደነዝዥኝ

ከነሱው ጭምር ልትይገርኝ. . .

ለተናገርኳው ሁሉ፣ መልስ የሚሆን ነገር ካለሽ

አሁን ቀጥዩ ትቺያለሽ

አሌክስስ፡- [ጉምጉምታ] ምትናገረው ጠፍቷታል- ይሄስ ለወሬም አይመች

ክው ብላ እኮ ነው የቆመች

ቤንቴናስ፡- [ጉምጉምታ] በያ ደርድሪ ቃላትሽን- ጠብጠብ አርጊዋ እንባሽን

የማጥመጃ መረብሽን፡፡

‹‹የለመደች ጦጣ›› አሉ

አሁን አለፈ ያ ሁሉ- ማባበሉ፣ ማታለሉ፡፡

ክሊዎፓትራ፡- እንዴት ብዬ ይሁን ወንጀሌን፣ መከላከል የሚቻለኝ

ከሳሼም ዳኛዬም አንተው፣ ሆነህ አንዴ ከፈረድከኝ?

ለኔ የነበረ ፍቅር፣ መጥቶ ጠበቃ እንዳይሆነኝ

ዛሬ ጭራሽ ጠላት ሆኖኝ፣ እያጠፋኝ ነው የሚገኝ፡፡

ፍቅር ካበቃለት፣ ቢቻል ቢረሳ ያዋጣል፡፡

ባብዛኛው ግን ውሎ አድሮ፣ እርሾ ይቆመጥጥ እና፣ ወደ ጥላቻ ይለወጣል፡፡

ስለፈቀድከው ነውና፣ የኔ ክፉን እጣ ጌታዬ፣ እንዲህ መዘርዘርህ ጉዴን

በቃ ጥፋተኛ ሁኜ፣ ብቀበል ይሻላል ፍርዴን፡፡

ግን ለአንዲት ደቂቃ እንኳ- አንተ በኔ ላይ አትኩረህ

ጉድፌን አንድ ሁለት እያልክ፣ በረቂቅ ወረንጦ ለቅመህ

እስክትመራመረኝ፣ ለአንተ ጠላት እሆናለሁ፣ ብዬ ላስብ እችላለሁ?

ተናገር እስቲ ጌታዬ- እኔስ በቃኝ ጨርሻለሁ፡፡

የሚገባኝ ቢሆን እንኳን፣ ይህ አይነቱ ቅጣት ለኔ

አንተ ከት አመጣኸው፣ እንዲህ ያለውን ጭካኔ?

አንቶኔ፡- ኦ. . . ! መለያየቱን ፈልጌው፣ ከመሰለሽ ተሳስተሻል

የሆዴን በሆዴ ብይዝ፣ ላንቺስ ቢሆን ደስ ይልሻል?

በደልሽን መዘርዘሬም

እራሴን ለማንባት እንጂ፣ ሀጢያትሽን ላበዛ አይደለም፡፡

ለመቆራረጣችንም፣ አግባብነት ምክኒያቱ

ግልፅ እንዲሆን ፈልጌ ነው፣ ለሌላ አይደለም በእውነቱ፡፡

ክሊዎፓትራ፡- በጣም አመሠግናለሁ- ነገር ግን ለንፅህናዬ፣ በአንድ ነፍሴ እምላለው!

የስራዬ በምድር ባይሆን፣ በሠማይ አገኘዋለው፡፡

ቤንቲዴዎስ፡- [ጉምጉምታ] ይሄ ፍንክች ያላረጋት- ሳጥናዬልም ቢቀቅላት

በጅ ማለትዋን እንጃላት፡፡ ኧረ ምን ጨካኒቷ ናት!

ክሊዎፓትራ፡- የመጀመሪያ ወዳጄ፣ አንተ ልትሆን ሲገባ

ቂሳር ቀድሞ ስላቀፈኝ፣ እጅግ ያዘንክ ትመስላለህ፡፡

እኔም ካንተ በላይ ነበር፣ በዚህ ቅጥል ያልኩ ያን ሠሞን

መቼ ጫፌ ይደርስ ነበር፣ ቀድመህ ያንተ አርገኸኝ ቢሆን?

ግን እንድታውቀው ምፈልገው- ከቂሳር አልጋ ብወድቅም

እኔ የእሱ ሆኜ አላውቅም፡፡

ቁሳር በቅድሚያ ፍቅርሽን፣ ወሰደ አይደል ያልከው

እዚህ ላይ ነው የተሳሳትከው

እሱ ገላዬን ሲወስድ፣ ፍቅሬን አንተ ነው የወሰድከው።

ቁሳር እኔን ቢያፈቅረኝም፣ እኔ አንቶኒን ነው ያፈቀርኩት

የስልጣኑን ልክ ባውቅ ግን፣ እንደምንም ብዬ ቻልኩት።

ለእብሪት ምን ይሳነዋል? በፍቃዴ አልሠጥ ብለው፣ ፣በጉልበቱ ይወስደዋል።

ቤንቲዴሞስ፡- አቤት ሔዋን፣ አቤት ሔዋን

እዩልኝ ብቻ ዘዴዋን!

ይሄ ብዙ ያወራችለት፣ ፍቅሯ ዐውነት ነው እንበል

በሷ ምክንያት አይደለም፣ የሆነብህ ሜዳው ገደል?

ሌላውን ሁሉ ተውና፣ ይህን ብቻ አስበው በል!

ክሊዎፓትራ፡- የሆነው ሁሉ የሆነው፣ መሆን ስለነበረበት

እንጂ እንዳይደል በኔ ስህተት

ጠምዶ የያዘኝ ጓደኛህ፣ ቢገነዘብ ምናለበት

እርግጥ ነው- አፍቅሬሃለሁ

ከባለቤትህ ፋልቪያም፣እንድትርቅህ አድርጌሃለው

ይህንን በደንብ አምናለሁ።

ባልጀራህ ግን የሚለው- አየከሰሰኝም ያለው

አክታቪያን ለኔ ብለህ፣ ትተሃት ስለመጣህ ነው።

ያን ሁሉ ክብር ዝናህን፣ በኔ በአንዲት በማልረባ

ለውጠህ፣ እርግፍ አድርገህ፣ መጥተህ ከቤቱ ስትገባ

ብቀበልህ እልል ብዬ

ያስወቅሰኛል ጌታዬ?

ቤንቲዴሞስ፡- ወሬ ነው! ወሬ ብቻ ነው!

ባክህ አክቲዩምን አስታውሰው!

አክቲዩም ላይ የሆነውን ለዚህ ሁሉ ያበቃህን

እንዳትረሳው አደራህን!

ክሊዎፓትራ፡- የጓደኛህ ክፋቱና፣ ምክኒያት የለሽ ጥላቻው

አያስጨንቀኝም እኔን፣ አይደለሁም እና አቻው፡፡

እንጂማ እኔ እሱን ብሆን፣ ዛሬ ነበር መሞቻው!

ግን ካነሳው አክቲዩምን

በእርግጥም እኔ ነኝ ያቀድሁ፣ ውጊያው በባህር እንዲሆን

ነገር ግን ቢመስ፤ኝ እንጂ፣ የሚያዋጣ የሚረዳ

ቀድሞስ ለምን ዘመትኩና፣ ኧላስ ለምን ነው የመከዳህ?

‹‹መሀል ውጊያ ላይ እያለው፣ ጥለሽኝ ሸሸሽ›› ብልሃል

ብሸሸም ወደ ሀገሬ እንጂ፣ ወደ ጠላት አንዳልነ ነበር፣ ልትርዳኝ ይገባል፡፡

መቼም ጦር ሜዳ ነውና፣ ልቡ የፈራ የሸሻል

ለዚህ ምን ምክኒያት ያሻል?

አንቶኒ፡- ያም ሆነ ይህ ክሊዎፓትራ- እኔ እና አንቺ አልታደልንም

ሌላ ምክኒያት አንኳ ባይኖር፣ የእህል ውሃ ነገር ሆኖ፣ ከመለያየት አንድም፡፡

እነስቲ አንቺው ተናገሪው

እዚህ ቆይቼ ቢያልቅልኝ፣ ከነአካቴው ቢያከትምልኝ፣ ይሻላል ነው የምትይው?

ክሊዎፓትራ፡- እንደ ባልንጀራህ ሆኜ፣ ፍርድ እንደድሠጥ ከጠየከኝ

ሂድ ብልህ ነው ሚቀለኝ

እንዳፍቃሪህ ፍረጅ ካልከኝ፣ ብትቀር ነው ደስ የሚለኝ

ግን ጌታዬ ይቅር በለኝ፡፡

ክብርራችን ቢያልፍ፣ ቢያከትምልን፣ እኔ አንዳችም ግድ የለኝ

አንድም ቀን ትሁን ሁለት ቀን፣ ቀሪዎን እድሚያችንን፣ ባንለያይ ነው የምመኝ፡፡

ባክህ ባክህ ማርክ አንቶኒህ፣ ስለ ፍቅር ተለመነኝ!

ቤንቴዲዎስ፡- አይህ አይደል - ፍቅር ፍቅር፣ እያለች የምትደሰኩረው

ከማየቀው መቃብሯ፣ አስከትላህ ልትገባ ነው።

እንጂ ያላንተ ብቻዋን፣ ማምለጥ ትችል ቢሆን ኖሮ

ዞር ብላ እንኳን ሳታይህ፣ ጥላህ ትሮጥ ነበር ድሮ

ክሊዎፓትራ፡- [የተፃፈበት ወረቀት ለአንቶኒ እየሰጠችው] እንግዲያውስ -አይተህ

ፍቅሬን ትመዝነዋለህ።

ካንተ ተለይቶ ኑሮ፣ ሞትም ይሁን፣ ደስታም ይሁን

ላደርገው ብፈቅድ ኖሮ፣ አግኝቼው ነበር እድሉን።

አንቶኒ፡- [ወረቀቱን እያየ] ኧረ የፈጣሪ ያለህ!

ቤንቲዬስ -ጉድ ታያለህ?

እንደ እጅ መዳፍ የማውቀው

የአክታቢዎስ ጽሁፍ ነው!

ከኔ ጋር ያላትን ሁሉ ግንኙነት ካቋረጠች

ጦሯን ከጦሯ ነጥላ፣ ከሱ ጦር ከቀላቀለች

በገፀ በረከትነት፣ ሲሪያን ቃል ገብቶላታል

ግብፅም ባለበት ሁኔታ፣ የሷ እንደሚሆን ነግሯታል።

ክሊዎፓትራ፡- ምንም አይደል -ሂድ ትተኸኝ! -ግን ምንጊዜም አፍቃሪህ ነኝ።

አንተን በሌላ ብለውጥ፣ አንድ አምላኬ አይለመነኝ!

ንብረት፣ሀገር፣ ግዛት፣ ሕይወት

ከምንላቸው ነገሮች፣ ምንም አይከብደኝ መለየት

ካጣሁ ልኖር የማልችለው

አንቶኒ - አንተን ብቻ ነው።

እባክህ አብሬህ ልሙት!

ወይስ አግባብ የጎደለው፣ ጥያቄ ይሆን ያቀረብኩት?

አንቶኒ፡- አብረን ልንኖር ካልተቻለን

አብረን በሞትን በተሸለን፡፡

አሌክሳስ፡- [ጉምጉምታ] በጣም ጥሩ -ሰይጣን ሽው ካላለው በቀር፣

ድል የኛ ሳይሆንም አይቀር፡፡

ክሊዎፓትራ፡- በፍፁም! መሄድ አለብህ

አዎ -እጅግ ብርቱ በመሆኑ፣ ስበቱ የውድ ክብርህ

[እጆቹን በእጆቿ ትይዛለች]

ሂድ ግዴለም ጦረኛዬ -ጭንቀት ላያስቀር ከመንገድ

ፍቅርህ ካለቀ በኋላ፣ ለምንድነው ምትገደድ፡፡

ግን እወቀው ከወዲሁ -መንገድህን እንደጀመርክ፣ ብዙም ሳትጓዝ በመሐል

የሆነ ሰው ተከትሎህ፣ከኋላ ይደርስብሀል

‹‹ክሊዎፓትራ ሞተች›› ብሎም የምስራች ያረዳሀል፡፡

የዛኔ -ወታደሮችህ፣ ሐሴታቸው ወሰን ያጣል

አንተ ግን ኬት መጣ ሳትል፣ ይወርህና ወናነት፣ ምናልባት ታዝን ይሆናል፡፡

በል ሂድ የኔው ማርክ አንቶኒ -ነገር ቢያበዙት ይበዛል

በፍቅር አልሆን ያለ ልብ፣ በሌላ በምን ይገዛል?

አንቶኒ፡- እናንት አማልክት! ይህ ነገር፣ እጅግ በጣም ነው ሚከብደው!

ወንድ ልጅም ሊሸከመው፣ ከሚችለው ያለፈ ነው፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ያፈቀረችውን ላጣች፣ አንዲት ደካማ ሴትማ፣ ምንኛ እንደሚከብድ እየው፡፡

እስቲ አትመቅኘኝና፣ በዚች ደቂቃና ሰአት

የመጨረሻዋን ትንፋሼን፣ በእቅፍህ ውስጥ ልተንፍስላት፡፡

በተቻለኝ ፍጥነት ሁሉ፣ በቶሎ እሞትልሃለሁ

ያንተንም ጣጣ ከስሩ፣ ነቅዬ እጥልልሃለሁ፡፡

አንቶኒ፡-	ኧረ እኔኑ ፍግም ያርገኝ!

አንቺ ሞትሽ ምን ሊውጠኝ?

ሰማዩን ደግፎ የያዘው፣ ምሰሶው ለምን አይፈርስም!

ለምን አንዳች መአት ወርዶ፣ ያለም መጨረሻ አይሆንም!

የኔ ብርሃን፣ የኔ ህይወት! ነይ የኔ አለም!

[ያቅፋታል]

ቤንቲዬሞስ፡-	አወይ ሐኤዋን! የአዳም ቅጣት!

ከድልህ፣ ክብርና ዝናህ፣ አንዣርአርገህ ብትመዝናት

አሁን ይቺ አሻንጉሊት፣ ኧረ በኔ ሞት ምንድናት?

አንቶኒ፡-	ተው በቃ! -ቤንቲዬሞስ ተው

የትና የት ተገናኝተው?

እኔ አሁን ስለንግስቴ፣ ቀድሞም ነገር መጠርጠሬ፣ የበደል ሁሉ በደል ነው!

የቺ -ይቺ -ይቺ ናት እንግዲህ እየው

‹‹ከማይቀረው መቃብሯ፣ አስከትላኝ ልትገባ፣ፍቅርን ምትደሰኩረው››

‹‹ያለኔ ብቻዋን ማምለጥ፣ የሚቻላት ቢሆን ኖሮ

ዞር ብላ እንኳን ሳታየኝ፣ ጥላኝ የምትሮጥ ዱሮ››!. . .ሃሃሃ!

ይቅርታዋን ተማፀናት፣ ከፊቷ ተንበርከክና

ንፅህናዋን በክለህ፣ ስሟን አጥፍተሃልና፡፡

ቤንቲዬሞስ፡-	ለምን አሁን ድብን አልል!

እሷን ይቅር በይኝ ከምል፡፡

ይልቅ አሁን ትሄዳለህ?

አንቶኒ፡-	‹‹ ትሄዳለህ››?. . .አንተ ሰው ትቀልዳለህ?

ይቺን መሳይ ፀጋ ትቼ፣ የት አባቴ ነው ምሄደው?

ይህን አምላክም አይወደው!

እምነት -ክብር -ጨዋ ምግባር፣ ሁሉም አይፈቅዱም እንድርቅ

ፍቅሬን ካስበለጠችው ሴት፣ ከግዛቶች ዋጋ ይልቅ፡፡

አማልክት ሆይ -እባካችሁ!ይቺን ተረት ተረት አለም

ስጡት ለቄሳር ልጃችሁ፣ አልፈልጋትም ግዴለም!

እኔ ከክሊዎፓትራሌላ፣ ምፈልገው አንዳች የለም!

ክሊዎፓትራ፡- ያንተው ናት እስከዘላለም!

ለፈጣሪ ምን ይሳነው. . .

በዓለም ያለ ሐሴት ሁሉ፣ ገብቶ ልቤን ስለሞላው

ልጓም አልባ፣ ገደብ ዘለልፍቅር፣ ግብ በአደባባይ፣ መከወኜ የማይ ቀር ነው፡፡

ያኔ- የመውደደድ ሚስጥሩ፣ የማይቀው ይህ ጅል አለም

እብድ ቢለኝም ግድ የለም!

ቤንቲዲዎስ፡- እግዚኦ ሴቶች! እግዚኦ ሴቶች!

አማልክት ሁሉ በአንድነት፣ ለወንድ ልጅ ደግ ደጉ፣ ለመስራት ያለው አቅም

እናተ ክፉን ክፉን፣ ልትሠሩበት አላችሁን፣ ሀይል እና ስልት አያክልም!

[ይወጣል]

አንቶኒ፡- ወታደሮቻችን ከትተው፣ በተጠቀቅ ነው የቆሙት

ወደ ቄሳር የጦር ሠፈር፣ የሚያስወጣውን ከተን በር፣ ወለል አድርጋችው ክፈቱ!

ከጀርባዬ ላሴረብኝ፣ ለዚህ ክፉ መሰሪ ሠው

የበቀል ክንዴን ላቅምሰው!

ለጥቂት ወቅት የተላየኝ፣ ገናታዊ ፍስሃ፣ መመለሱ ሲታወቀኝ

ገና ከመሄዴ በፊት፣ መመለሻዬ ናፈቀኝ፡፡

አይ ቄሳር- አንተን አያርገኝ!

[እየወጣ ሳለ ማብራት ይጠፋል]

ገቢር ሦስት

[በአንደኛው መግቢያ በር ክሊዎፓትራ፣ ቻርሚዮን፣ አይራና አሌክሳስ ግብፃውያን አጃቢዎቻቸውን አስከትለው ይገባሉ። በሌላኛው መግቢያ ደግሞ አንቶኒና ሮማውያን አጃቢዎቻቸው ይገባሉ። በሁለቱም በሮች በኩል ሙዚቃ ተዘጋጅቷል። መጀመሪያ ከአንቶኒ በር አቅጣጫ የትራፔቶች ደምፅ ይሠማል። ከዚያም ከነ ኪሎ ፓትራ አቅጣጫ የትብሬሎች ድምፅ ያስተጋባል ቻርሜዎን እና አይራ በመካከላቸው የአበባ ጉንጉን አክሊል ይዘው ቁመዋል። የግብፃውያን ዳንስ፣ ወዘተ ይታያል። በመጨረሻም ክሊዎፓትራ አክሊሉን በአንቶኒ እራስ ላይ ትደፋለች።]

አንቶኒ፡- እነዚህ አረግ ክንዶችሽ፣ አቅፈው ከጉያሽ ሲከቱኝ

ከደረትሽ ላይ ለጥፈው፣ አቅለጠው ፍቅር ሲያደጉኝ

በሀሳቤ እየታየኝ

አሁን- አሁን- አሁን ሲለኝ

ለያንዳንዱ ስንዘራዬ፣ ተጨማሪ ጉልበት ሆነኝ።

ክሊዎፓትራ፡- ናልኝ እስቲ ሳተናዬ ግባ ከክንዶቼ ማሀል

ከቅፌ ከተለየህ፣ ከራቀኝ ሰነባብትሃል።

አንቶኒ፡- የኔ ፀዳል፣ የኔ ብርሃን- ሠማይ ሙሉ ኮከብ በርቶ፣ ያነስቺ ያህል አያደምቅም

ክሊዎፓትራ፡- ግን አንተን ከፊቴ ሳታህ፣ ውድም እንደምል አታውቅም?

አንቶኒ፡- እኔ ከቅፍሽ ውስጥ ሲያዩኝ

ምድሪቱም ሆነ ሠማዩ

ሚስጥሩ ምን ይሁን እንዲህ፣ በቀናት ዛር የሚሠቃዩ?

በከንቱ ነው ሚደክሙት፣ ለማየት ስንነጣጠል!

[ቤንቴዲዎስ ይገባና ነጠል ብሎ ይቆማል]

አሌክሳስ፡- ተመስገን. . . ን!- አደጋው አልፉዋል

ጄነራልህ ተመልሱዋል።

ግን ደስታህን ከቁብ ሳይቆጥር ድልህን ችላ ብሎ

ማገማጨጩን ቀጥሉዋል፣ ግንባሩን ኮሶ አስመስሎ።

አንቶኒ፡- ማ? የኔው ቤንቴዲዎስ?- ለዚህስ አንገቴን እሠጣለው!

ከገዛ ሂወቱ በላይ፣ እንደሚወደኝ አውቃለው፡፡

አንድ ቀን እንኳ ያላግባብ፣ ለወግ ሸንግሎኝ አያውቅም

ለዚህ ነው እጅግ ማከብረው፣ ጨዋነቱ የሚያስፈራኝ

ወደ ቤተመቅደስ እንሂድ፣ ምን አልባት አይኑ ቢርቀኝ

አይኑን በአይኔ ስጋፈጠው፣ በብርቱ ነው ሚፈትነኝ

[የተቀሩት ሁሉ ይወጣሉ፡፡ አንቶኒን ግን ቤንቴሊዎስ ልብሱን ያዝ አድርጎ ያስቀረዋል]

ቤንቲዲዎስ፡- ንጉስ ሆይ

አንቶኒ፡- **/ወደ ጎኗ መለስ ብሎ እያየው/**

ደሞ መጣህ ልታደርቀኝ?

እባክህን፣ በቃ ተወኝ!

ቤንቴዲዎስ፡- ንጉስ ሆይ- አንድ እድል ስጠኝ

አንቶኒ፡- እኮ ሸማዬን ልቀቀኝ!- በኋላ ጦስ እዳትሆነኝ

ቤንቴዲዎስ ግድ የለም አንዴ ታገሰኝ

ማወቅ ምትሻውን ነገር፣ ነው ይገፍልህ የመጣሁኝ፡፡

አንቶኒ፡- አይንህ ያያል ነፃ እነዳሎንኩ

እዚህ ቆየኝ፣ እመጣለው የያዝኩትን እንደጨረስኩ

/ይወጣል/

ቤንቴዲዎስ፡- ለሱስል ፍዳዬን አየው!- ቢሆንም እችለዋለው

የራሱን ግባተ መሬት፣ ለማየት የሚጣደፈውን፣ ይህን ሠው አፈቅረዋለው

/አንቶኒ ይገባል/

አንቶኒ፡- አየህ አይደል እንደምንችል፣ማሸነፍ ያላንተ ርዳታ?

እንደፈንዲሻ ቆሎ ነው፣የበተናቸው ባንዳፍታ!

አምስት ሺህ ሮማውያን፣እስትንፋሳቸውን አጥተው

ተንጋለው ሜዳ ሞልተዋል፣ፊታቸውን ለፀሃይ ሰጥተው።።

ቤንቲዬሞስ፡- እሱስ ጥሩ ነው- ቢሆንም- አምስት ሺውን የላከው ሰው

ሌላ አስር ሺህ መጨመር፣እንዳይመስልህ የሚሳነው።።

አሁን ግን ጥሩ እድል አለህ፣ከቁሳር ለመደራደር

ባሁኗ ሽንፈት ምክንያት የጦርነትን አማራጭ፣ትንሽ ስለሚጠራጠር

አንተን በሚመስልህ መልኩ፣ይቻልሃል እርቅ መፍጠር።።

አንቶኒ፡- እሱንማ- ቤንቲዬሞስ፣አታስበው፣የማይሆን ነው

ያልጅ ከኔ እርቅ ሳይሆን፣ውድቀቴን ነው ሚፈልገው።።

ቤንቲዬሞስ፡- በሱ ተሰሚነት ያለው፣አንድም ባልንጀራ የለህ፣ከወታደሮቹ መሃል?

ማይቼናስ ወይም አግሪፓ፣ቢሆኑስ ምን ይመስልሃል?

አንቶኒ፡- ቀኝ እጆቹ ናቸውና፣ሁለቱንም አናስብም፣ለኛ ያደላሉ ብለን

ስለዚህ- በሰይፍ እንደጀመርን፣በሰይፍ እንጨርሰዋለን

አሊያም ደግሞ- እናልቃለን።።

ቤንቲዬሞስ፡- አንድ ሌላ ሰው አግኝቼ፣ምነው ልቤ በረጋልኝ።።

አንቶኒ፡ ስለቅን አስተሳሰብህ፣አምላክ የጅህን ይስጥልኝ።።

አራት አምስቱን ከደገምን፣የዚህ ያሁኑን ድል አይነት

ተገላገልክ ማለት ነው እኮ፣እንዲህ ከወጠረህ ጭንቀት።።

ቤንቲዬሞስ፡- ከንግዲህስ ሌላ አትጠብቅ

በርግጥ አውቃለሁ ጌታዬ፣ድልህ መሆኑን ሚያስደንቅ።።

ግን ያም ሆኖ- እንድታውቀው ምፈልገው

የሰው ሃይልህንም ሆነ፣ስንቅ እና ትጥቅ ምታገኘው

ከንዲት ደሃ ከተማና፣ከግብፃውያኑ ብቻ ነው።።

የቁሳርን ግን ካየሀው

አለም ሁሉ ደጀን ሆኖት፣ከጀርባው ይጠብቀዋል

ምትፈጥርበትንም ክፍተት፣ከስር ከስረ ይሞላዋል፡፡

እና አስብ እባክህን

አንተን በሚወግን ዘዴ፣ከዚህ ሰው ጋር ሚያስማማህን፡፡

አንቶኒ፡- ለምንነው የባእድ ድጋፍ፣እንድሻ ምታስጨንቀኝ?

የጥንት ወዳጅ ለማስታወስ፣ጠፉን እና ባድማውን፣ካላካለልክ የምትለኝ?

አንዴ አምላክ የበደለው

ምንም አይነት ወዳጅ የለው!.....

አሃ..ወዳጅ መኖሩን ነበረኝ- አንድ ጀግና የሮም ወጣት

ቁሳር ለሱ ያለውን ፍቅር፣ወንድ እንኳ የለውም ለሴት፡፡

ቤንቲዴሞስ፡- ልክ የዚህን አይነት ሰው ነው፣አሁን እኛ ምንፈልገው!

አንቶኒ፡- በጣምም ይወደኝ ነበር

ነፍሱም እኔ ነበርኩና፣ከኔም ውጪ እሱ አልነበር፡፡

እኔ በሱ፣እሱ በኔ፣መንፈስ ከማደራችን ላይ

ተሰፍተን አንድ የሆንበት፣ክሩ ሚመውቶ ስለጠፋ፣ምልክቱ እንኳ አይታይ፡፡

ቤንቲዴሞስ፡- [ጉምጉምታ] አሁን እየሄደ ያለው

በማልፈልገው መንገድ ነው፡፡

አንቶኒ፡- እንግዲህ- ከዚህ በኋላ- ማን እንደሆን ያልኩህ ሰው

የተረዳህ ይመስለኛል- ታላቁ ዶላቤላ ነው፡፡

ቤንቲዴሞስ፡- አሁን እኮ ታዲያ እሱ- ቁሳር ጦር ሰፈር ነው ሚገኝ፡፡

አንቶኒ፡- እዛም ቢገኝ፣ እዚህም ቢገኝ ከእንድዚህ ምንም አይጠቅመኝ

የኔነቱ ድሮ ቀርቱዋል፣ አሁን ከምንም አይቆጥረኝ፡፡

ክሊዎፓትራን በማፍቀሩ፣ ትንሽ ስጋት ገባኝና

ከለከልኩት ዝር እንዳይል፣ ከአጠገቧ እንደገና፡፡

በዞረችበት እንዳይዞር፣ አዘዝኩ- እሱም ተቀበለኝ

ከዚሃን ወዲህ ግን፣ ሆዱ እንደተቀኘመኝ፡፡

ለኔ ሲል አምቆ የያዘው

ልዩ ሰሜት ለእሷ እንዳለው

ሀሜታ ሰምቼ ሳይሆን፣ የነገረኝ እራሱ ነው፡፡

በእርግጥም እኔና ይህ ሠው፣ የዚያን ያክል ተመሳስለን

ሁለታችንም አንዷን ሴት፣ ላንወድ እንዴት እንችላለን?

ታዲያ ሆዱ መቀየሙን፣ በበለጠ ግልፅ ያደረገው

ላይመለስ ጥሎን ሲሄድ፣ አለመሰናበቱ ነው፡፡

ቤንቲዲዎስ፡- እሷን ከወደዳት በላይ፣ ቢወድህ ነው እንጂ አንተን

ከመሄዱ መቆየቱ፣ ሊመርጥ እንደ ነበር እመን፡፡

ግን መቅናትህ ስለገባው፣ ሊያሳዝንህ አልፈለገም

ስለእውነቱ እንፍረድ ካልን፣ ከዚህ በላይ ወዳጅ የለም፡፡

አንቶኒ፡- ያኔም ማወቅ ነበረብኝ!

አሁን ሲያስቸግረኝ ሳይሆን፣ ዙሪያው ገደል ሲሆንብኝ፡፡

ቤንቴዲዎስ፡- ይወድህ እንደ ነበረ፣ ልብህ በትክክል ያምናል?. . .

መልስህ ‹‹አዎ›› እንደሆነ፣ ከአይኖችህ ይነበባል

በቃ ላሳጥረው እና፣ የድብበቆሹ ነገር

የሱን ደብዳቤ የያዘ፣ መልክተኛ መጥቶ ቁሟል፣ ከዚያው ከቁሳር ጦር ሠፈር፡፡

አንቶኒ፡- ብቅ በል በለዋ ታዲያ- እስከማየው ቸኩያለው፡፡

ቤንቴዲዎስ፡- አሁኑኑ አስገባዋለሁ፡፡

[ቤንቴዲዎስ ይወጣና ወዲያውኑ ከዶላቤላ ጋር ይገባል]

አንቶኒ፡- ኧረ የፈጣሪ ያለ!- ዶላቤላ እራሱ ነው!

ይህንንስ አይኔ አያምነው! /ሊያቅፈው ወደሱ ይሮጣል/

እስቲ ወዲህ ናልኝ እና፣ ቀሪህ ግማሽ ነፍሴን ስጠኝ፡፡

የናፈቀ መሽራ እንኳን፣ የጫውግላው እለት ፍቅሩን ሲያገኝ

በደስታው ቢስተካከለኝ-

አምላክ ዛሬውን ይግደለኝ! /ይተቃቀፋሉ/

ዶላቤላ፡- አሁን ምንም ማለት አልችል፣ አንደበቴ ጥሎኝ በሯል

ቀልቤን ለከውን ባሰብኩት፣ ታላቅ ምግባር ተወጥሯል፡፡

ነፍሴም ቀሪህ ግማሽ ጎኗን፣ ስለተገናኘችው አሁን

በስስት እየቃየች ነው፣ ያው እንደ ጥንቱ መሆኑ፡፡

አንቶኒ፡- የጥንቱማ አይደለሁም!- ወርጃለሁ!- ዘቅጫለሁ!

ቢኖር እንኳ ቀረኝ ምለው

አሁን ካንተ ጋር ያለው ነው፡፡

እንደ በጋ ወንዝ ጎድዬ፣ ምድር ለምድር ነው ምሳበው!

ገባር ሆነው ያገዘፉኝ፣ወንዞቼ ሁሉ ደርቀዋል

ወይ አቅጣጫ ቀይረዋል፡፡

እንዲያም ሆኖ ግን- ይህ ልቤ፣ ለእጣፈንታ ላለው ንቀት

እንዳቁመ ቁስል አብጦ፣ ዝቅ ብዬ ካለሁበት፣ ብድግ ያደርገኛል ድንገት፡፡

ዶላቤላ፡- የሆነው ሆኖ- እኔ የማመነው

አሁንም የመላው አለም፣ ገዢ አንተ መሆንህን ነው፡፡

አንቶኒ፡- ባንድ በኩል ትችላለህ- ሃሃሃ! ትችላለህ!

‹‹መላው አለም›› የሚባለው፣ምንድን ነው?አንተም አይደለህ?

አይ የኔ ዶላቤላ!

ታውቀኛለህ- እንዳሁኑ፣ የሰው ውራጅ ሳልሆን በፊት

ስንት ንጉስ ዘብ እንደሚያድር፣በዙሪያዬ ቀን ከለሊት፡፡

ዶላቤላ፡- እኮ- የእድልህ ሎሌያት፡፡

አንቶኒ፡- አሁን ግን እድል የቄሳር ናት!

እኔማ ያለው ከጥልቁ፣ካርባ ክንድ ጉርጋድ ውስጥ ነው፡፡

ቤንቲዬሞስ፡- አርባ ክንድም መቶ ክንድም አልከው

እራስህ ነህ የቆፈርከው!

አንቶኒ፡- በርግጥ በቅን ልቦና ነው፣ይህንን የተናገርከው?

ዶላቤላ፡- መጠየቁስ ለምንድነው?

የወዳጅነቱን እንጂ፣አሊያማ ምን አናገረው?

ያለው ትክክል ነውና፣እኔም ስለምደግፈው

ልትቆጣን አይገባህም፣ጋደኝነት ለመቼ ነው?

አንቶኒ፡- አረ ልብ አርግ ዶላቤላ-

አንተስ ምንም አያምርብህ፣የኔን ማፍቀር ብታጥላላ፡፡

የዚችን ንግስት ጉድ አይኖች፣መለኮታዊ ምትሃት

ያንተም ነፍስ የምታውቀው ናት፡፡

ትዝ አይልህም ያን ጊዜ- ለወንድምህ ሞት ምክኒያት

ነች ብለህ እንዲያ ጠልተሃት

ግን እንዴት እነዴት እንደሆንክ፣መጀመሪያ ቀን ስታያት?

ዶላቤላ፡- አረ እሱንስ አታስታውሰኝ!

የዚያ ቀን ሃፍረት ፀፀቱ እስከዛሬም አለቀቀኝ፡፡

አንቶኒ፡- ለወንድምህ ረዳት ጦር፣ለምን እንዳላከችለት

ምክኒያታን ልታስረዳህ፣ወደኛ ሃገር የመጣች ለት

ቁልቁል በብርማው ባህር፣መርከባ ወደኛ ሲሳብ

የመለያ ባንዲራዋ፣ወርቃማው ሃር ሲውለበለብ

እንደወላንዶ ተገፍቶ፣በነፋሻው የባህር አየር

ሃምራዊው የንፋስ ሽራ፣እንዳጋተ ጡት ሲወጠር

ባህር ጣአት የሚመስሉት፣አያሌ ውብ ገረዶችዋ

ያልማዝ ፈርጥ ሆነው ሲያደምቃት፣ተኮልኩለው በዙሪያዋ

እሳ እንደ እንቁ መሃላቸው፣ከመከዳው ጋደም ብላ

ትዝም አትልህ ባህሩ ላይ፣ሌላኛዋን ቬኑስ መስላ!

ዶላቤላ፡- በቃ! በቃ!- ባልሰማው ነው የሚሻለኝ!

አንቶኒ፡- መስማትማ ይገባሃል፣አላግባብ ከምትፈርጀኝ፡፡...

አልማዝ አይኖቻ ፈንጥቀው፣እንደ እሩቅ መንታ ክዋክብት

በሚያማልል ከፈት ከደን፣ዙሪያዋን ፀዳል ሲያለብሱት

ኮበሌ አሽከሮች ከፊቷ፣ግራና ቀኝ ቆመውላት

በተዋቡ መሸረፊቶች፤አየሩን ሲያራግቡላት

መለኮታዊ ሞገሳ፣መልአክ ነበር ያስመሰላት፡፡

ፈገግ ባለችማ ጊዜ-

ይታይ ነበር በዙሪያዋ፣ሚወረወር፣ሚፈናጠቅ ምትሃታዊ አባዜ፡፡

የአዳም ልጅ በጉጉ አይኑ፣ሲያየው ቢኖር የማይጠግበው

የሚፈካ አበባን ሚስጥር፣የተካነ ፈገግታ ነው፡፡...

በዚያች ሰአት ዶላቤላ -የት ነበረች ያንተስ ነፍስህ?

ባድናቆት ስሜት ተውጠው -ቁጣ ጥላቻህ እልህህ፣ጥሎህ አልጠፋም ከላይህ?

እኒያን አይኖቿንስ ሸሽተህ፣ በኔ ጆርባ ተከልለህ፣በጆሮዬ ሹክ አላክም?

‹‹ለወንድሜ ሞት ምክንያት፣ እሷን እንደምትጠረጥራት

አደራህን እንዳትነግራት›› ብለሃል ወይስ አላልክም?

ዶላቤላ፡- ታዲያ የኔ ድክመት ላንተ፣ ምክኒያት ሊሆንህ ይችላል?

እኔኮ -ዕድሜዬም ሲታይ፣ አይፈረድብኝ ይሆናል፡፡

በፍላጎቱ ስለነበር፣ አደግሁ አደግሁ በምልበት

የኔው ብቻ ጥፋት ሳይሆን፣ የተፈጥሮም እጅ አለበት፡፡

ያንተ ግን -

ቤንቲዬሶስ፡- ምንም ሳትፈራ ንገረው!

አየህ -ሊልህ የፈለገው -ያንተው ግን በማያምርብህ፣በስተርጅና መሆኑ ነው፡፡

በግድ ከምታመነጪው፣ በቀር ሌላ አንዳች መውቀት

በአካልህ ውስጥ በሌለበት፡፡

በእድሜ ምክንያት ዝቅ እያለ፣የመጣውን ፍላጎትህ

ከተፈጥሯችን ሕግ ውጪ፣ በግድ አቅጣጫ አስተህ

ከቶም የማይመስል ነገር፣ ልታስረዳን ትጥራለህ!

እኔ ውነቴን ነው ምልህ፣ እንዳው ደፈርከኝ ባትለኝ

በስተርጅና የመጣብህ፣ መጃጃል ነው የሚመስለኝ!

አንቶኒ፡- አሃ. . .! ‹‹መጃጃል ነው›› አልከኝ?

ዶላቤላ፡- ይህም ትንሽ በዛ ባይ ነኝ፡፡

እና -እኔ ከስሬ እንኳን ቢሆን፣ ኪሳራዬ ወሰን አለው

ምን የማጣው ነገር አለኝ? ካጣሁም ራሴኑ ነው፡፡

የጦር ሃይሎቼን አላጣሁ -

ዓለምን ከእጄ አላወጣሁ -ወይ በህዝቤ አልተጣለሁ!

አንቶኒ፡- አለኝ ከምለው ወዳጄ፣ ይህን አይነቱን ቃል ልሰማ?

ዶላቤላ፡- አዎ ጓደኤ ማርክ አንቶኒ -ከልብ ወዳጅህ ብቻ ነው፣ እንዲህ ግልፁን የምትሰማ!

ካንጀቴም ስለምወድህ -ቃላቱ ካፌ ሲወጡ

ከጆሮህ ሳይደርሱ በፊት፣ የኔን ልብ ነው ሚበጡ፡፡

ያም ሆነ ይህ - ጭቅጭቅ አብዝቼም እንደሁ፣ ወይ ቃላት ቆርፍደውብኝ

ከክፋት እንዳትቆጥርብኝ፡፡

በተረፈ -በቁሳር ስም፣ ቢኖር ልልህ የምችለው

ምህረቱን ልኮልሃል -ውሳኔው ግን የራስህ ነው።።

አንቶኒ፡- አቤ. . .ት እናንት አማልክት! ምን ይሆን የበደልከኳችሁ?

ቁሳር መሃሪዬ ሲሆን፣ እንደዘበት ማየታችሁ?

ይሄን ጉድ ልታሰሳዩኝ ነው፣ እስከዛሬ ያስቆያችሁኝ?

ምነው እናንተም እንደሰው፣ ቀን አይታችሁ ከዳችሁኝ?

ዶላቤላ፡- አንደበታቹ እኮ ሳይሆን፣ እንደኩያው ነው የጠየቀህ።።

አንቶኒ፡- እኩያው መሆኔንማ ከቶስ ምን አጠራጠረህ!

እሄንን ታጥቄ ሳለሁ፣ ሊበልጠኝ ይችል መሰለህ?

ዶላቤላ፡- እርቀ ሰላሙ እንዲወርድ፣ እንድታገኝ ምህረትህን

ቁሳር በዝርዝር ነግሮኛል፣ ካንተ ሚጠብቁብህን።።

አንቶኒ፡- ጨዋ ጥያቄዎች ናቸው?

ቢሆኑ እንጂ -አንተም ደፍረህ፣ ከኔ ዘንድ አታመጣቸው።።

ሆኖም -ቁሳርህ ነውና፣ የተዋጣለት አስመሳይ

ተንኮሉ እንኳንስ ለቀን፣ ለሚያተኩርም አይታይ።።

ቤንቲዬሶስ፡- ታዲያ -እንዲህ ዓይነቱን ሰው

አስተሳሰቡን በማረቅ፣ ወዳንተ መንገድ መልሰው

ለርቀ ሰላም ያደረሱት፣ እንደዬት ታላቅ ሰዎች ናቸው!

አንቶኒ፡- ያው የኔው ዶላቤላ ነው!

ካምላክ በታች ማን ሰው አለ፣ ይህን ማድረግ የሚቻለው

ዶላቤላ፡- መስሎህ በኔ እንዳትኮራ -

ወይ እንዳይመስልህ የአግሪፓ፣ ወይም የማይቼናስ ሥራ።።

ማይቼናስና አግሪፓ፣ የሱ እንጂ ያንተ አይደሉም።።

እኔ ወዳጅህ ብሆንም -

ብቻዬን ማድረግ ምችለው፣ አንዳች ነገር አልነበረም።።

ያም ሆነ ይህ -ይህን ጉዳይ፣ ላንተ ቆሞ የከወነው

ሮማዊ ወዳጅህ ነው -ይገባም ዘንድ ፍቃድህን እየጠበቀ ነው ያለው።።

አንቶኒ፡- ሮማዊነቱንማ፣ እኔም አልጠራጠረው።።

እስቲአሳዩኝ ይህን ሰው!

ሕይወቴን -ፍቅርና ክብሬን፣ ከእንጦሮንጦስ የመለሰው።።

እስቲ ፊቴን ብቻ ልየው!

ቤንቲዴሞስ፡- አሁኑኑ ማሳይህ ነኝ!

[እየወጣ] ትደሰታለህ እመነኝ።።

ዶላቤላ፡- ቀሪውን እድሜህን ሙሉ፣ በህይወት ቆመህ እስካለህ

የዚህን ታላቅ ሮማዊ፣ ውለታውን ትረሳለህ?

አንቶኒ፡- ብረሳው አማልክት ይርሱኝ! -እንጂ ሌላ ምን እላለሁ?

ንግስቴም ለዚህ ምግባሩ፣ እጥፍ ድርብ ምስጋናዋን፣ እንደማትነፍገው አምናለሁ።።

ዶላቤላ፡- እሷስ እንጃ -ምታደርገው አይመስለኝም።።

አንቶኒ፡- ታደርገዋለች እመነኝ፣ እኔ ምልህ ዶላቤላ

ትኩሳቷ በልብህ ውስጥ፣ እርሾ ብጤ እንኳን አልተወም፣ ውሎ ቢያድር የሚብላላ?

ዶላቤላ፡- ማርክ አንቶኒ -አልዋሽህም

ክፉዋን ላይ አልፈልግም።።

አንቶኒ፡- ከረቂቅ ውበቷ በላይ፣ ያላት ንፁህ ሀቀኝነት

ሰማይ በላዬ ይደፋ፣ እሷን ጥዬ የሄድኩ እለት!

ቄሳር ያልሞከረው የለም፣ እኔን እንድትከዳላት

ከግዛቶጩ ባላነሰ፣ ክፍያ ቢፈታተናት

ከኔ ፍቀር ባይበልጥባት፣ ሁሉን ንቃ የተወች ናት!

ታዲያ ለዚህች ንፅህት ሰው -የኔ መውደድ በዝቶባት ነው

ይህን ያህል ምንኮነነው? አንተስ እንዲህ የምትሆነው?

ዶላቤላ፡- አዎ -ምክኒያቱም ይህ ነው!

[ቤንቲዴዎስ ተመልሶ ይገባል፡፡ አብራውም ኦክታቪያ ትገባለች፡፡ አንቶኒ ይደናገጣል፡፡]

አንቶኒ፡- [ወደኋላው እንደማፈግፈግ እያለ] እንዴ -ኦክታቪያ ናት!

ቤንቲዴዎስ፡- ምነው? -ለምንድነው ዬምትሸሻት?

አውሬ መስላ ታየችህ? -ወይስ ክፉ ደዌ አረካት?

እስቲ በደንብ ተተመልከታት -ውዲ ባለቤትህ እኮ ናት

ዶላቤላ፡- ስለፍቅር እንኳ ባይሆን፣ ስለፍርሃት አምላክ ብለህ

እባክህን ተቀበላት ግንባርህን ፈታ አርገህ፡፡

አንቶኒ:- እንዴት ወዲህ እንገመጣች ግራ ቢገባኝ እኮ ነው፡፡

ቤኒቲዴዎስ፡- እኔ በሰው ልኬባት ነው

እንድትገባም ያደረኩት ዘበኞቹ ሳያውቁ ነው

ዶላቤላ፡- ኧረ ባክህ ጌታዬ እንኳን ደህና መጣሽ በላት

ለምንድነው ፊት ምትነሳ?

ኦክታቪያ፡- እንግዲህ- የዚህን ያህል፣ጠብቃለሂ ሰለምታ

በእንኳን ደህና መጣሽ ፋንታ፣ ኮሶ ካስመሰልክ ፊትህን

ወይ አላውቅሽም በልና፣ አሰናብተኝ እንግዳህን፡፡

ማነኝ ከፊትህ የቆምኩት?

አንቶኒ፡- የቁሳር እህት

ኦክታቭያ፡- ውይ- በሞትኩት!

በቁሳር እህትነቴ፣ ብቻ ነው እኔን ምታውቀን?

የቁሳር እህት ከመሆን፣ ያለፈ ጉዳይ ከሌለኝ

ከቁሳር የጣር ሰፍር፣ ምን ይሁን ወዲህ ያመጣኝ?

የቁሳር እህት ነው ያልከኝ?- ሃሃሃ!- አምላክ የስራህን ይስጥ!

ግን ያንተዋ ኦክታቪያ- ስቃይ የበዛብኝ ሚስትህ

ምንም አልጋህን ብታገድ፣ ወይም ብባረር ከቤትህ

ምን የቄሳር እህት ብሆን- አሁንም ነኝ ባለቤትህ!

በኔ ላይ መቀዝቀዝህን፣እንደተጠየፈው ልቤ፣እርግጥ ነው ይታወቀኛል

እናም ያንተን በጎ ፍቃድ፣ በልምምጥ መቀበሉን፣ ለኔ በጣም ይከብደኛል፡፡

ይሁንና፣ የሚስትነት፣ ሃላፊነቱ ሚገኘው

ከእንዲህ ያለው ግብዝነት- እና ኩራት ባሻገር ነው፡፡

ስለዚህ መጥቻለው- የኔ እንደሆንክ ላስታውስህ

ሃላፊነቱ ነውና- ፈቃድህን ልጠይቅህ- መለቱ ልማዕንህ፡፡

ጌታዬ እጅህ የኔ ነዋ!

ስለዚህ- ስጠኝ ልውሰደው፡፡

(እጁን እየያዘችው)

ቤኒቲዬሞስ፡- ኧረ ውሰጂው!- ይገባሻል፡፡

ዶላቤላ፡- ይገባታል!- ባንዲት ነፍስህ እንወራረድ- ማን ሴት ይስተካከላታል?

ጨዋነት ከሚሻው በላይ-እራሷን ዝቅ ካላረገች

ወይ ግብዝነቷ ገኖ- አላግባብ ያልተኮፈሰች

እጅግ የተመጣጣነች- ሮማዊም ሚስት ነች!

አንቶኒ፡- እኔ ምልሽ ኦክረታቪያ- ያን ወንድምሽን ቄሳርን

ህይወቱን እንዲምርልሽ- ለምነሽልኝ እንዳይሆን፡፡

ኦክታቪያ፡- ለምነሽልን አልክ ጌታዬ?

አንቶኒ፡- አሞ የኔይቱ አምበሳደር! ለምነሽልኝ ነው ያልኩት

አልባሌ እና አስነዋሪ፣ ውለታ ጠይቀሽልኝ፣ እንደይሆን ነው የሰጋሁት፡፡

ኦክታቪያ፡- አልባሌና አስነዋሪ ውለታ እኔም አልለምን

ወንድሜም ቢሆን አይከውን

አንቶኒ፡- ያንበረከኩትን ንጉስ፣ ተነስ እነደገና ንገስ፣ እያልኩ የኖርኩት ሰውዬ

ተንበርክኬ ልለምንህ ነው፣ ባክህን ቁሳር ማረኝ ብዬ?

አላደርገውም! ማረኝ ሚሉት ቃል ያንቀኛል!

ባፌ ከመውጣቱ በፊት፣ ምላሴ ላይ ይሞትብኛል፡፡

ዶላቤላ፡- ማረኝ ማለቱም ኣያሻህ፣ ሁሉም ተስተካክሎልሃል

አንቶኒ፡- **(በፌዝ አንደበት)** ሃሃሃ!- ሁሉም ተስተካክሎልኛል!

አንተም ጓኛዬ ሳትቀር፣ አሳልፈህ ሰጥተኸኛል

በጸሎት በዕንባ ተማፅና፣ ሚስቴ ያመጣችልኝን፣ ጥቂት ፀያፍ ድርድሮች

ገዝታቻኛለች ማለት እኮ፣ ከወንድሟ ላይ በዕንባዋ

አንዳሻት የምታገበኝ፣ ሆንኩኝ ማለት ነው ባሪዋ!

ደስ ሲላት እየቦረቅኩ፣ ቅር ሲላትም እያዘንኩ

ለሷ መስዬ ካላደርኩ

አንድ ቀን እንኳ ስሜቷ፣ ችላ ያልኩ መስሎ ከታያት

"ለወንድሜ እንዳልነግርልህ"፣ ብላ "ምታስፈራራኝ" ናት!

ኦክታቭያ፡- አውቀዋለሁ ሌላ -ሳይሆን፣ የራሴው መጥፎ ዕድል ነው

ቅንነት ከጎደላቸው፣ አግባብ የለሽ ግምቶችህ፣ ጋር የሚዳረገኝ ያለው፡፡

ትሰማኛለህ አንቶኒ? - ሚጠብቁህ ነገሮች ፣ የተደራደርኩባቸው

ክብርህ ጫፉ ሳይነካ፣ ምትስማማባቸው ናቸው፡፡

ያንተ ክብር ክብሬ እኮ ነው፣ ለምንድ ነው የማታምነኝ?

የኦክታቭያ ባለቤት፣ የወንድሟ ባርያ ነበር፣ እንዲባል ምፈልግ ነኝ?

ጌታዬ - በቃ ነፃ ነህ! - ነፃ ነህ ከሁላችንም

ከቁሣርም አይኗን ማየት ከማትሻው ከሚስትህም!

በርግጥ ወንድሜ ውሳኔው

በአንተና በሱ መካከል፣ እርቅ ሊወርድ የሚችለው

ለኔ ለህግ ባለቤትህ አክባሪ እና አፍቃሪዬ፣ ሆነህ ስትገኝ ብቻ

ይሁንና- የኔዋም ነፍስ፣ ስለሆነች ያንተው አይነት

ለመቀበል አልፈልግም፣ ፍቅርን በምዕዋትነት

ወይም መለመን አልሻም፣ ሚገባኝን በሚስትነት።

ለወንድሜ እነግረውና ፣ እርቅ ያወረድን መሆኑን

ከቦህ ከሚጠብቅበት፣ ለቆ እንዲሄድ ያዛል ጦሩን

ያኔ ተንቀሳቀሰና፣ ሄደህ አስተዳድር።

እኔ - አቴና ላይ ወይም ፣ የሆነ ቦታ ብትተወኝ

እንዲ ሆንኩ የሚል ወቀሳ፣ አንድም ቀን ካፊ ሳይወጣኝ - ትቼ መኖር ምችል ነኝ

ቤንቲዬዎስ፡- **(ጉምጉምታ)** የራስ ክብር ንትርክ ውስጥ፣ ገባን እኮ እንደገና!

የውለታህን ዕዳ ሸክም፣ ሁለቱም ጠሉት።

ዶላቤላ፡- **(ለቤንቲዬዎስ)** አየህ ዐይኑ ሲርገበገብ! አየሕ ሲጠርገው ዕንባውን

ጠብ ሲል የነበረውን።

አንቶኒ፡- ኦክታቭያ - በደንብ አዳምጩሻሁ

የነፍስሽን ትልቅነት፣ በዕውነት አደንቅልሻሁ።

ያቀረብሽልኝ ሃሳብ ግን -የምቀበለው አይደለም!

እኔን ከፍቅር በስተቀር፣ የሚረታኝ ነገር የለም።

ከኃላፊነት አንፃር ነው፣ ሁሉን ማድረግ የወሰንሺው

"ነጻ ካወጣሁህ ወዲያ፣ አቴና ላይ ትተኸኝ ሂድ" አይደለም እያልሽኝ ያልሽው?

ኦክታቪያ፡- አዎ ጌታዬ እንደሱ ነው።

አንቶኒ፡- እንግዲያውማ ያላግባብ፣ ያንዲት የማትወደኝን ሴት፣ ውለታዋን ልትቀበል ነው!

ይሄን ከቶም አልሞክረው! ሸክሙንም አልቋቋመው።

ቤንቲዬዎስ፡- **(ጉምጉምታ)** ጎሽ! ደስ ይለኛል እንዲህ ሲያመው።

ኦክታቪያ፡- ምስኪን ባለቤትህን፣ በጎ ሃሳብ ተገን አርገህ

ያቀድከውን ብታሳካ፣ አይሻልህም ወጉን ትተህ?

አንድ ነገር ላስገንዝብህ - ኩራቴ ብቻ ነው የቀረኝ

እንዳልወድቅ ደግፎ የያዘኝ፡፡

ወደ ፊት አንድ አንድ ጊዜ፣ ምናልባት ትዝ እንኳ ቢልህ

ነፃ አውጪ እኔ መሆኔ፣ የዘላለም ባለውለታህ

ያኔ አይቀርም ማስታወስህ ፣ ለዚህ ግብሬ ምክንያቱን

ሃላፊነቴን ብዬ እንጂ፣ ፍቅርን ብዬ አለመሆኑን ::

ልልህ የፈለኩት ነገር፣ እንደማይጠፋህ አምናለሁ

በጽኑ ተበድያለሁ!

ሆኖም ይቺ ኩሩ ነፍሴ፣ ሁሉን የምትቋቋም ናት

ግን አልጋዬን ለናቀ ወንድ - ይቺን ታህልም ቁብ የላትም!

አንቶኒ፡- ይህ ማለት - አትወጂኝም፡፡

ኦክታቪያ፡- ይህ ማለት - ልወድህም አይገባኝም!

አንቶኒ፡- ስለዚህ - ትሄጃለሻ ትተሺኝ ?

ኦክታቪያ፡- ስለዚህ - ትቼህ መሄድ ነው ያለብኝ - ከታቸለኝ፡፡

ዶላቤላ፡- ይህን ሁሉ ጉዳት ይዛ፣ እውድሃለሁ እንድትል

ይመስልሃል የምትችል ?

ቃሉን ባፏ ባትለውም፣ ሁኔታዋ ይመሰክራል

እርጋታዋ፣ ዝምታዋ፣ አፏ ሊለው ያልቻለውን፣ የልቧን በግልፅ ያወራል

አንቶኒ ፡- ኧረ ባክህ ዶላ ቤላ - ፊቴን ወዴት ነው ’ማዞረው?

ምን ባደርግስ ነው ’ሚሻለው?

ልቤ ውስጥ ውስጡን ሲረታ፣ እየታወቀኝ ነው ያለው፡፡

ብሞት እንኳ አብራኝ ልትሞት ፣ በራሷ ላይ የወሰነች

ከሁሉ በላይ ፍቅር ያለች ክሊዎፓትራስ ’ምተዋት ነች?

ቤንቱዲዎስ፡- ክሊዎፓትራ - አብሬህ ልሙት ብትልም፣ መጀመሪያ አጥፍታሃለች

ኦክታቪያ አንተ ያጠፋሃት ቢሆንም፣ ልታድንህ ትጥራለች

ከመቼ ወዲህ ነው ደግሞ እኩይ ምግባርና ጥሩ

መወዳደር የጀመሩ?

አንቶኒ ፡- (በተጨነቀ አንደበት) አወይ የተረገመች ነፍስ!

ኦክታቪያ፡- ምንም የማይነሳው አምላክ፣ ይባርክል ነፍስህንስ!

ጌታዬ - ና ግድየለህም፣ እኔ ከቻልኩ ይቅር ልልህ

እጄን መቀበል እጄን አለብህ፡፡

ቤንቱዲዎስ፡- እንዲህ አንጀት የሚበላ፣ ነገር ታይቶም አይታወቅ!

ጌታዬ፡- ሙተር ብትገፋት አምላክ እንዳይምርህ እወቅ!

ዶላቤላ፡- የምድሩስ የምድር ነው፣ ከማሰይ ቁጣ ተጠንቀቅ!

ኦክታቪያ፡- አደራህን ባለቤቴ፣ ቢያንስ አንድ አምላክህን ፍራ፡፡

አንቶኒ፡- **(በደቀቀ ስሜት)** አዬ ጉድ! አዬ መከራ!

ይበቃል ተረትቻለሁ! - ኦክታቪያ ነይ ውሰጂኝ!

ከልብሽ ይቅር በይና ዳግም የራስሽ አድርጊኝ፡፡ (እያቀፋት)

ሳልቆጥበው እንደዘበት፣ ነው ፍቅርሽን ያባከንኩት

እድሜውን ብቻ በሰጠኝ፣ እና ሁሉንም በካስኩት!

ኦክታቪያ፡- ይህን የተባረከ ቀን እንዴት ብዬ ላመስግነው?

ዶላቤላ፡- ዳግም የመወለድ ያህል ነው!

አንቶኒ፡- (ለኦክታቪያ) ይህስ ድል ያነቺ ነውና፣ ወደ ምትፈልጊው ምሪኝ፡፡

ከወንድምሽ ሰፈር እንኳ፣ ብትወስጂ የምሄድ ነኝ!

ኦክታቪያ፡- እዚያ የሚገኙት ሁሉ፣ ያንተው ሆነዋል እመነኝ፡፡

አሌክሳስ፡- ንግስቲቱ - እመቤቴ - ጌታዬ ያንተም እመቤት

አንቶኒ፡- ያማ ቀርቶ? ወዴት ወዴት? — (ነገሬም ሳይለው ወደ ኦክታቪያ ይዞራል)

ኦክታቪያ - ላስቸግርሽ፣ ከዚህ ቆዩ የዛሬን ሌት

ነገ ጠዋት ከቁሳር ጋር ፣ አንድ ስንሆን ታየዋለሽ ፣ የጥረትሽን ሁሉ ስኬት፡፡

(አንቶኒ ኦክታቪያን አስከትሎ ይወጣል፡፡ ዶላቤላም ተከትሎ ይወጣል)

ቤንቴዲዎስ፡- (ለአሌክሳስ) አቃጣሪው ጀንደረባ! - 'ምታወራው ዜና አለህ!

ምን እዚህ ይገትርሃል? - ይልቅዬስ ፈጠን ብለህ

ሌላ አቃጣሪ ሳይቀድምህ ሹክ አትልም ለእመቤትህ?

ፍጠን እንጂ ጃንደረባው! - ሩጥ - ሩጥ - ጊዜም የለህ

(ይሁን ብሎ ቤንቴዲዎስ ይወጣል)

አሌክሳስ፡- ይህ ገሪባ! ጅል ጦረኛ!

የራስ ቅሉ የደደረ፣ ሃሳብ የራቀው አርበኛ

በጅላጅል ቅን ልቦናው፣ የተበተብኩትን ድባቅ ከቶታል በሉኛ!

ወይኔ ሰውዬው!.... የዚህ ሁሉ ምክንያቱ...

አዎ ... የዚህ ችግር ስር መሰረት፣ የዚህ ሁሉ ምክንያቱ

ወንድ እሆናት የማይቻለኝ ፣ ዱልዱም የሰው መክት ሆኜ፣ መቅረቴ

ነው በእውነቱ!

እንጂ እንኳንስ ሲላገዲት፣ ፊቷ ዝር የማለት ዕድል፣ ማን ነበር ያገኘው

ከጥንቱ?

ምድረ ግብዝ ምድረ ከንቱ!.....

ገና ጨቅላ ሳለሁ ነበር፣ በፍጥረት የተቸረኝን ፣ የወንድነት ፀጋ ያጣሁ

ለሌሎች ቅንጦት ዘብ ላድርመ፣ ቃጭሌ በግፍ ተወስዶ ፣ ከተፈጥሮ ፈር

የወጣሁ፡፡

እንዲያም ሆኖ.... ያለብኝን ፣ ይህን ስጋ ስንኩልነት

እውቀት ምግባሬ ሸፍኖት፣ ጠብቆኝ ነበር ከንቀት፡፡

ምን ዋጋ አለው ? ዛሬ ሁሉም ፣ ጥሎኝ በረረ በድንገት!

ኧረ እንዴት ያለው ውንጅብጅብ፣ ቧልት አምባ ነው ዓለም ማለት?

መቋጠሪያ መፍቻ የሌለው፣ ትርጉም አልባ የጅል ቅዠት !

አንዳንዴ ደግሞ ሳስበው....

ለአንዲት ቁራጭ ሰከንድ እንኳ፣ ከወንድ ቆጥራኝ በነበረ

የሷ ግዛት የሷ ክብር ፣ ዳዋ ሰልቅጦት በቀረ !

በደሌን ለማወራረድ ፣ ማደርገውን አውቅ ነበር ። .....

(ክሊዎፓትራ ቻርሚዎን ፣ አይራና አጃቢዎች ይገባሉ።)

እ.... የኔ እመቤት - የማይታመን ነገር ነው ያጋጠመን በዚች ሰዓት

ኦክታቪያ መጥታ እዚህ ናት !

ክሊዎፓትራ፡- አትጨህ ሰምቻለሁ። እኔ አሁን የምገኘው

በሞት ቀስፈት አምባ ላይ ነው

አሌክሳስ፡- ይቅርታሽን እመቤቴ - ንግስትነትሽ አብቅቷል

ግብፅም ምፅኣቷ ለይቷል።

ክሊዎፓትራ፡- ስለ ግብፅ ነው 'ምትነግረኝ ?

ህይወትስ፣ ነፍስስ የታለኝ - ኦክታቪያ ጋ ነው 'ሚገኝ!

እንግዲህማ ምን ቀረኝ! ከእጄ ወጣም አይደል ጀግናው?

ኧረ ጉድ በሉ እናንተዬ - የት ጉድጓድ ነው የምገባው?

ግን እንደው - ንገረኝ እስቲ፣ ባላንጣዬን ስላየኋት

ይህ ፀጋ 'ሚገባት ናት? - ማለቴ

እንደ እንስት አምላክ ብሩህ፣ እዚህ ቀረሽ የማይሏት

የፈጣሪ ታላቅ ጥበብ፣ የታየባት ፍፁም ሴት ናት?

አሌክሳስ፡- እንደውነቱስ - ተዓምር ናት።

ክሊዎፓትራ፡- በቃ የቀረችኝ ተስፋ፣ ከነአካቴው ውሃ በላት! - ‹‹ተዓምር ናት››

አሌክሳስ፡- (በይቅርታ መልክ ለጥ ብሎ እጅ እየነሳት)

ተአምር ናት ስልሽኮ፣ በፀባይዋ ማለቴ ነው።

በውበትማ - እመቤቴ፣ ማነው ጫፍሽ የሚደርሰው!

ክሊዎፓትራ፡- (በእፎይታ) ተጣድፌ አቋረጥኩህ፡፡

ለዚህ መልካም ንግግርህ፣ እንካ ይሄን ልሸልምህ፡፡

(ቀለበቷን አውልቃ ትሰጠዋለች)

እህ! ብቻ እንዳይሆን መደለልህ ፡፡

በተረፈ - በፀባይዋ ያሻትን ያህል ብትበልጠኝ

እንዳይመስልህ 'ሚያሳስበኝ፡፡

ቻርሚዮን፡- ያቺው መጣች!

አይራ፡- አረ ጥፊ እመቤቴ የቄሣር እህት እኮ ነች!

ክሊዎፓትራ፡- ለምን የአምላክ እህት ሆና፣ አታዝባትም ህይወቴን!

ከቆምኩበት ንቅንቅ ሳልል ፣ 'ምጋፈጣት ነኝ ጣውንቴን፡፡

(ኦክታቪያና ቤንቲዩሶስ ይገባሉ፡፡ ኦክታቪያ በዝግታ ወደ ክሊዎፓትራ ትጠጋለች፡፡

በመድረኩ ግራና ቀኝ የሁለቱም አጀቦች ወደ መድረኩ ፊት ይጠጋሉ)

ኦክታቪያ፡- (በቋንቋዋ ታጉተመትማለች) ኤኮ ላ ክሊዎፓትራ! ላ ፉታሌ ላ ቪፔራ!

ቬራሜንቴ ኤሮቲካ! ማ አንኬ ዲያቦሊካ፡፡

(ወደ ክሊዎፓትራ ትቀርባለች) ክሊዎፓትራ መሆንሽን፣ ምን መጠየቅ ያስፈልጋል?

ኩሩው ጅንኑ ሁኔታሽ -

ክሊዎፓትራ፡- ንግስትነቴን ያሳያል፡፡

እኔም አንቺ ማን እንደሆንሽ፣ መጠየቅ አያስፈልገኝ፡፡

ኦክታቪያ፡- ስርዝ ድልዝ የሌለብኝ የጠራሁ ሮማዊት ነኝ፡፡

ሮማዊ ማለት ደግሞ ካወቅሺው አንዲት ንግስት

ሙሉ ስልጣን ያለው ዘር ነው፣ እንደፍቃዱ ሊያደርጋት

ሊሰራት ወይም ሊያፈርሳት፡፡

ክሊዎፓትራ፡- እኔን ከነ ሙሉ ክብሩ፣ እያገለገለኝ ያለው

ጌታሽ እኮ ሮማዊ ነው፡፡

ኦክታቪያ፡- እሱስ ነበረ መሆኑን -

ግብፅ አገር ውስጥ ባሪያ ሆኖ፣ አጣው እንጂ ያንን ስሙን፡፡

ዕድሜ ላንቺ ለመርዛሚ! - ለሰበርሺው ኃያል ቅስሙን፡፡

ጥፋቱስ የኔው ነው እንጂ፣ ይህ ባልሆነ ነበር ጥንቱን

አሁን ግን ልበጥስለት፣ ነው የመጣሁ ሰንሰለቱን!

ክሊዎፓትራ፡- የፍቅረኛዬ ባለቤት- ረጋ በይ ግድ የለሽም

አላግባብ ልትዘልፊኝ እንኳን፣ ምንም አይነት መብት የለሽም፡፡

ጥሎሽም እዚህ የመጣው

ይኸው የቤት ጭቅጭቅሽ፣ ‹‹ሚስት››ነትሽ ቢታክተው

እና የኔም የሴትነት፣ አያያዜ ቢደላው ነው፡፡

ኦክታቪያ፡- ያያዝሽ መድላትማ፣ ከቶውንም አይገርመኝም

የዘማዊነትን ጥበብ፣ እንዳንቺ የኖረችበት! ሌላ እንስት አትገኝም፡፡

የወጥመድሽ ሲሳይ ሲሆን፣ እሱ የመጀመሪያው ሰው፣ እንዳልሆነ ልብሽ ያውቃል

ሩቅ መሄድም አያሻ፣ ቁሳር ምስክር ይሆናል፡፡

ክሊዎፓትራ፡- አትሳሳች - ቁሳርን አልወደድኩትም!

ቢሆንም - ለሰጠኝ ፍቅር፣ ምላሹን አልነፈኩትም፡፡

የሆነው ሆኖ - ይህ ክስሽ እውነት እንኳን አለው ቢባል፣ ሊያስረዳልሽ የሚችለው

ከሰው ልጆች ታላቁ ሰው፣ ባሪያዬ እንደነበር ነው፡፡

ከሱ ኋላም የቀጠለው -

ግን በኔ አመለካከት፣ ከሱ እጅግ የሚሻለው

ህግ ያንቺ ነው ’ሚለውና፣ ፍቅር የኔ ያደረገው

ታላቁ ማርካ አንቶኒ ነው

ኦክታቪያ፡- (ወደ ክሊዎፓትራ ይበልጡን እየተጠጋች)

እስቲ ቀረብ ልበልና፣ ይህን ያህል ግዜ መብቴን፣ የነጠቀችኝን ፊት ልየው

የወንድ ወጥመድ የሆነው

እና ውዱ ባለቤቴን፣ ከሰው በታች ያረገውን ምትሃቷን ልመርምረው፡፡

ክሊዎፓትራ፡- መመርመሩ ነው ’ሚሻለው፡፡

ምክንያቱም - የምትሃቴን፣ ግማሹን ያህል በኖረሽ

የውዱ ባለቤቱ ልብ፣ የዚህን ያህል ባልራቀሽ፡፡

ኦክታቪያ እውነቱን ንገሪኝ ካልሺኝ - የያታችን ማፈሪያ ነሽ!

ዲያቢሎስ በገዛ አምሳያ፣ ፈጥሮ ለጥፋት የሾመሽ፡፡

በኃጢያጢያት መደሰቻ፣ ሰይጣናዊ መስተፋቅር፣ አፍዝ አደንግዝ መካንሽ

ትንሽም አያሳፍርሽ?

ክሊዎፓትራ፡- ማፈር ያለብሽስ አንቺ፣ ለኒህ ነገሮች ያልታደልሽ፡፡

ቸሩ የሰማይ ገዢና፣ የማያልቅበት ተፈጥሮ፣ ይህን “ምትሃት” ቸረውኝ

የጀግኖቹን ጀግና ፣ ልቡን በፍቅር ለመውሰድ፣ እንድችል ስልጣን ከሰጡኝ

እንዴት አልታይሽ አለ፣ ሆን ብለው እንደመረጡኝ?

ለዚህስ በመታደሌ፣ እጅግ መኩራት ሲኖርብኝ?

የወደደው እኮ እኔን ነው፡፡

ስለዚህ ለዚህ ታላቅ ሰው፣ ሳልሰስት ነፍሴን ባልሰጠው

አምላክ መልኬን ይለውጠው! - እና ያንቺን አይነት ያርገው

ይኸው ነው ልልሽ ’ምችለው፡፡

ኦክታቪያ፡- የምታወሪውን ያህል፣ እንደማትወጂው አውቃለሁ፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ማንም ሊወደው ከሚችል፣ የበለጠ እወደዋለሁ!

ደግሞም ከማንም ሴት በላይ፣ ለኔ ይገባኛል እላለሁ፡፡

ኦክታቪያ ኧረ ምን ዓይነት አፈር ነው፣ ከቶ አንቺንስ ያበቀለሽ!

ዓይኖችሽን በጨው አጥበሽ፣ ገና ይገባኛል ትያለሽ?

ለውድቀቱና ጥፋቱ፣ ምክኒያቷ እኮ አንቺ ነሽ!

ስመ በመላው ሮማ፣ እንዲረክስ ያረገ ማነው? - ክሊዎፓትራ

በቀሪውስ አለም ሁሉ፣ እንዲናቅ ያረገ ማነው? - ክሊዎፓትራ

አካቲዩም ላይ የከዳ ማነው? ክሊዎፓትራ

ልጆቹንስ የሙት ልጆች፣ እኔንስ ምስኪን የሙት ሚስት፣ እንድንሆን ያረገ ማነው?

ይቺም ደዩስ ክሊዎፓትራ፣ - የተረገመች ናቤራ!

ክሊዎፓትራ፡- ሆኖም ለሱ ባላት ፍቅር፣ ማንም የማይስተካከላት

ይቺው ርጉሚ ናዜራ፣ ደዩሷ ክሊዎ ፓትራ ናት!

አየሽ - እህት ኦክታቪያ - ማስተዋል ያለብሽ ነገር

ባልሽ ለኔ፣ እኔም ለሱ፣ ባነወጠን ስንፈጠር

ይህ ሁሉ ባልሆነ ነበር፡፡

በርግጥ - ሃዘን ስቃይሽን፣ ጉዳትሽንም ባልክደው

የኔው ካንቺ የባሰ ነው፡፡

ሚስት የሚባል የይምሰል ስም፣ የያዝሺው አንቺ ስለሆንሽ

ቅቤ አንጓንቹ አዛኝ አለም፣ ምክኒያቱን ሳይመረምር፣ አንቺን ነው የሚወግንሽ፡፡

እኔን ግን ያልታደልኩትን፣ ያጣሁትን ዝና ክብሬን

ስርወ መንግስቴን አጉድፌ፣ ስለበደልኩኝ አገሬን

መላው አለም ነው ’ሚወቅሰኝ እንዲህም ራሴን ጥዬ፣ ሳር ቅጠሉ እስኪገርመኝ

ቅምጥ ወይ ውሽማ ’ሚባል፣ ፀያፍ ስም ነው የተረፈኝ፡፡

አሁን ያንንም አጥቼ፣ ሕይወቴ ብቻ ነው የቀረኝ፡፡

እሱንም - ላፈቀርኩት ሰው፣ ዐይኔን ሳላሽ ’ምሰጠው ነኝ

ኦክታቪያ፡- እንግዲህ እንዳልሽው ይሁን

ስትፈፅሚው ማየት ያብቃን፣ አሁን በቃልሽ ያልሺውን

(ከነአጀቦቿ ትወጣለች)

ክሊዎፓትራ፡- በርግጥ ምኞቱም ይኸው ነው!

የኖርኩለት ሰው እንደሁ፣ ከዚህ ወዲያ አላገኘው፡፡ . . .

አሌክሳስ፡- በግልፅ አንቺን ሳታጠፋ፣ የማታርፈዋ ይቺን ሴት

ዘደዉው አሁን መጥቶልኛል፣ ቀድማ የምትጠፋበት፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ከንቱ አይዞሽ ባይነህ አንተ! ከፊቴ ገለል በልልኝ

ነይ እስቲ ምሪኝ ቻርሚዋን - አይራም ነይና ደግፊኝ፣ ለብቻዬስ አይሞክረኝ

ሁለታችሁንም ማስቀመጥ፣ የሚችል ከባድ ሃዘን ነው፣ በላዬ የተሳፈረኝ፡፡

ወደ አንድ ብቸኛ ክፍል፣ ውሰዱና እዚያ ተውኝ

ለብቻዬ ላስተናግደው፣ ሐዘኔን እስኪወጣልኝ፡፡

(ሁሉም እየወጡ ሳለ መብራት ይጠፋል)

ገቢር አራት

(አንቶኒ እና ዶላቤላ)

ዶላቤላ፡- ለምንድነው ይህን ነገር፣ ካንተ ወደኔ ማዞርህ?

መለያየት እንዳለባችሁ፣ አንተው ባፍህ ብትነግራት፣ ምኑ ላይ ነው 'ሚቸግርህ?

አንቶኒ፡- እንዳይመስልህ የምችለው -

የቀኝ ዓይኔ ቢወጣና፣ ግራው ባያለቅስ ያህል ነው።

ኦ ዶላቤላ..... ! "መለየት" በሚሉት ቃል ውስጥ፣ ኧረ ስንት ሞት ነው ያለው!

ዶላቤላ ፡- ታድያ እንደዛም ከሆነ ፣ ቤንቲዬሶስ 'ማትልከው?

ሻከር ስለሚል ተፈጥሮው፣ ይሄ ለሱ ነው 'ሚቀለው።

አንቶኒ፡- አአ! - የሱ ደግሞ ከልክ ያልፋል-

ከመርዶው መቆርፈድ በላይ፣ አቆርፍዶ ይነግራታል

የሱስ ይቅር ይገድላታል ።

ግድ የለህም ዶላቤላ - አንተው ብትነግራት ይሻላል።

ዶላቤላ፡- ምን ገዶኝ አንተ ካዘዝከኝ

ግን እኔም በተፈጥሮዬ፣ ቡቡነት ሚያጠቃኝ ነኝ።

ስለ አንድ አፍቃሪ ክፉ እጣ፣ ተረት እንኳ ሲነግረኝ

ሰውን እንደሆነ ሁሉ፣ እንባ ግጥም ነው 'ሚለኝ

አንቶኒ ፡- ዶላቤላ ምን ሆነሃል?

ታዲያ አንተንስ መምረጤ፣ ሌላ ለምን ይመስልሃል?

የቻልከውን ያህል ሁሉ፣ ብትለሰልስ ነው የሚሻል

ክፉውን ዜና ቀስ በቀስ፣ ለመቀበል ይረዳታል።

ልክ ፊቷ ስትቆም፣ እኔን እኔን እንደሆንክ አስበው

በምትነግራትም ጊዜ - በተቻለህ አስረዝመው

ዶላቤላ፡- የነገርከኝ አንድም ሳይቀር፣ ነፍሴን ስለተዋሃደው

እኔ መሆኔም ካልቀረ፣ እንድነግራት የምላከው

እቃኛለሁ አንደበቴን፣ ልክ ጌታዬ እንደፈለከው፡፡

አንቶኒ፡- እንግዲያውስ - ትቼህ ልሂድ፣ ካስቸጋሪው አደራ ጋር

ፈፃሚው አምላክ ነውና፣ ያቅምህን ያህል ብቻ ጣር፡፡

ይቅናህ እንግዲህ - ሄጃለሁ

ለሷም መጥታ እንድታገኝህ፣ መልዕክት ልኬባታለሁ፡፡

(ለመውጣት መውጫው ጋ ይደርስና ተመልሶ ይመጣል)

ሌላ የረሳሁት ነገር -

የኔን እርቅ ሰላም ጉዳይ፣ ከቁሳር ጋር ስደራደር

የሷንም ሰላም ከኔው ጋር፣ አብሬ እንደማስተካክል

ክብሯም ሆነ ዙፋኗን ፣ ’ማስጠብቅላት መሆኔን፣ ንገርልኝ በትክክል፡፡

ይህንን አሁን ያልኩህን

እንዳትረሳው አደራህን፡፡

ዶላቤላ፡- ስጋት አይግባህ ጌታዬ - አረሳም አንዷን ቃልህን፡

(አንቶኒ እነደገና ወደ መውጫው ይሄድና ተመልሶ ይመጣል)

አንቶኒ፡- ሌላ ደግሞ የምትነግራት -

ምን ያህል እንደተገደደድኩ፣ እንደተወጠርኩ አስረዳት

ከቶም ልወጣው ከማልችል፣ ማነቆ ባልገባ ኖሮ፣ ይህ አይሆንም ነበር በላት፡፡

ዶላቤላ ፡- ግድ የለም አልኩህ እመነኝ፣ አንድም ነገር እንደማልተው፡፡

አንቶኒ፡- እንግዲያው በቃ ይኸው ነው፡፡

(እንደመውጣት ይልምና እንደገና ለመልሶ ይመጣል)

አበዛኸው አትበልና - አንድ ሃሳብ ደግሞ መጣልኝ

ምንም እንኳ ከዚህ ወድያ፣ እኔና እሷ ባንገናኝ

ሌላ መውደዷን ብሰማ፣ ልቤ እንደሚሰበርና፣ መንፈሴን እንደሚጎዳኝ

ሳትዘነጋ ንገርልኝ፡፡. . .

አሁንስ መሄድ አለብኝ፡፡

ምክኒያቱም - በተመለስኩ ቁጥር ነፍሴ ፣ ስትገባ ይታወቀኛል

እናም ቀጣዩ መልእክቱ በቃ ቅሪ አትሂጂ፣ ሚል እንዳይሆን አስግቶኛል፡፡

ቀርታ እሷም እኔም ብንቀልጥ - ጥፋት እንጂ ምን ይገኛል?

በል እንግዲህ አምላክ ይርዳህ- በኔ በኩል ይበቃኛል፡፡

(ይወጣል)

ዶላቤላ ፡- ይገርማል! - ግን እኮ ወንዶች ስንባል

ያደገ የመነደገ፣ ሀፃን ነን ማለት ይቻላል፡፡

በቅጡ አስተውሎ ላየን

መጠን ብቻ ነው ’ሚለየን፡፡

ደግሞኮ - ይገርማል - እሱን ባረገኝ እላለሁ

ምነው እኔ በሱ ቦታ ሆኜ፣ በሷ ፍቅር ከሰው በታች፣ በሆንኩ ብዬ እመኛለሁ፡፡

(ከመድረኩ ጥግ በኩል ቤንቲዬሶስ ይገባል፡፡)

ቤንቲዬሶስ፡- እንዴ - ሰውዬው- ምን ነክቶታል?

ብቸኝነቱ ሲገርመኝ፣ ጭራሽ ከራሱ ያወራል?

ኧረ ማውራት ብቻም አይደል - ጭንቀትም ይታይበታል ,

አሃ . . .! ግምቴ ሰርቷል ማለት ነው!

ተዳፍኖ የነበር ፍቅሩ፣ ዞሮ ቢያገረሽበት ነው፣ ብቻውን ’ሚቀባጥረው፡፡

ዶላቤላ፡- ደግሞስ በምን ተዓመር ነው -

ለሱ የሞተውን ልቧን፣ ከሞት አንስቼ ዳግም፣ ለኔ እንዲሞት የማድርገው?

አይሆኑ ሆና ቢሳካስ፣ የቱጋ ነው ፋይዳው ያለው?

እኔም ከእንግዲህ እኔን አልሆን፣ ጥንስሱም ፍፃሜ አይኖረው፡፡

እንዲያው ብቻ ከንቱ እብደት ነው፡፡ . . .

ደግሞ ባንድ በኩል ሳየው -

ለፈነዳው ሁኔታ ጋር፣ ሰዓቱ እጅግ የሰጠ ነው።

እሱ አውልቆ የጣለውን፣ እኔ አንስቼ ብለብሰው

ምኑ ነው የሚያስወቅሰው?

ቤንቲዴሞስ፡- (ለራሱ) ምንም! ምንም - የሚያስወቅስ የለው!

ሃሃሃ! -ይቺን አልነበር ምመኘው '

ሰንኮፏን ካንቶኒ ልብ ውስጥ፣ አሁን ነው መንቀል 'ሚቻለው፡

(ክሊዎፓትራ ከአሌክሳስ ጋር እያወራች ትገባለች። በሌላኛው በኩል ቻርሚዎን አይራ ይገባሉ)

ዶላቤላ ፡- (ለራሱ) ያቺው እየመጣች ነው !

ጉድ እዩልኝ ብቻ ፊቷን፣ ሃዘን እንኳ ጌጥ ሲሆነው!

ቤንቲዴሞስ፡- (ለራሱ) ምነው ይህ ጃንደረባዋን፣ ይሄት ቢሄድ እንዳች መዓት!

እዩት እንደ ባዘቶ ጥጥ፣ ሲፈትላት ሲያጠነጥናት።

ይሄ ጥላቢስ ቀበሮ - የሸረበው ነገር አለ

ሲተረተር እንደሰማው፣ ወዲህ ጠጋ ቢል ምናለ!

አሌክሳስ፡- እመኚኝ እኮ ነው 'ምልሽ!

በተቻለሽ ሁሉ ጣሪ፣ በቅናት እንዲጠዝልሽ

የቅናት ነገረ ስራው -

ሰው ትንፋሹ ሲያጠራጥር፣ መኖር ሞቶቱ ፣ ከአፉ ስር እንደሚያዘው

ንፁህ መስተዋት ዓይነት ነው።

ትንሽ እንኳ ትንፋሽ ሲያገኝ፣ ይረጥብና መስታወቱ

ጉድ ሲሰራ ይታወቃል፣ ያ ሰውም አለመሞቱ።

(ዶላቤላ ወደ ቻርሚዮንና ወደ አይራ ይጠጋል። የሚያዋራቸው ይመስላል)

ክሊዎፓትራ መቅናት የመኖር ምልክት፣ መሆኑ ላይ እስማማለሁ

ግን ደካማ፣ ጥቅም የለሽ፣ መድሃኒት ሊሆን አውቃለሁ፡፡

በሽታውን በመመዘመዝ፣ አውጥቶ ቢያጋልጠውም

ማዳን 'ሚችል ኃይል የለውም፡፡

አሌክሳስ ፡- የቀረሽ መፍትሄ ይኸው ነው-

ውጤታማነቱም ቢሆን፣ እጅግ ነው 'ሚያስተማምነው፡፡

በዚህ ላይ ደግሞ - አለልሽ ይሄ - ዶላቤላ -ሚባል

እዚህ ጉዳይ ውስጥ ለመክተት፣ ማን አለ ከሱ የሚሻል?

እጅግ መልከመልካምና፣ ልበሙሉ ኩሩ ወጣት!

ተፈጥሮ የዘረጋቸው ወጥመድ እኮ ነው ሚመስል፣ ሴቶችን እንዲይዝላት፡፡

ከሁሉም በላይ ይህን ሰው፣ ይበልጥ ምቹ የሚያደርገው

ላንቺ ያለው ድብቅ ፍቅር፣ አንቶኒ መጠርጠሩ ነው፡፡

ባንዲቷ ክብሪት ፈገግታሽ፣ ወይም ጥቂት በጎ ቃላት

ልቡን ልታንበገቡጊው ፣ ጥቂት ትችያለሽ ይህን ወጣት፡፡

ከዚያማ - ከዚያማ - እንሚቃጠል ጀልባ፣ አዛኝ ዘዋሪ እንደሌለው

ቁልቁል በንፋስ መልቀቅ ነው፣ አንቶኒ እንዲከተለው

በቅናት እሳት ለኩሶ፣ ልቡን እንዲያንበለብለው፡፡

ክሊዎፓትራ፡- አይ አሌክሳስ - ይመስልሃል? ይህን ማድረግ ምችል ?

በጭራሽ አይሆንልኝም፣ ምን ይረባል ከንቱ ትግል?

እኔ ፍቅሬ የእውነት ነው!

ባለበትም - አይቻለኝ ልደብቀው - በሌለበት ማስመሰሉንም አላውቀው፡፡

ዕጣ ፈንታ ሚባል ነገር - ለአጉል ውሸምነትና፣ ቅምጥነት የዳረገኝ

ለደስታዬ የሚያሻኝን፣ ሸፍጥ ቅጥፈት የነፈገኝ

እከላከል አጠቃበት፣ ጋሻውም ጦሩም ሳይኖረኝ ሌጣዬን ነው የወረውረኝ!

የእጄን እንኳን ላለመልቀቅ፣ መሰሪነት እምቢ አለኝ፡፡

አሌክሳስ፡- እመቤቱ - እንደምንም - ማስገደድ ነው ራስሽን፡፡
ቀድሞም ሊያጣሽ የፈራውን፣ ይህን የዋህ ወዳጅሽን
ላንቺ ያለውን ፍላጎት፣ በእጥፍ እንዲያይል አርጊና
ከእጅሽ አግቢው እንደገና፡፡
አንድ ነፍሴን እሰጣለሁ፣ ይህ ዘዴያችን ቢቀር መና!

ክሊዎፓትራ፡- ለነገሩ - ምን ምርጫ አለኝ? የግድ እሞክረዋለሁ!
አቤት! አቤት! - ግን ቁጭቱን፣ እንደማልችል አውቃለሁ!
(አሌክሳስ ይወጣል፡፡ እሷ ወደ ዶላቤላ ትቀርባለች)
(ዶላቤላ) ከሴቶች ወግ ይዘሃል!
ጨዋታችሁን ብካፈል፣ ብቀላቀል ቅር ይልሃል?

ቻርሚዎን፡- ወጋችንም አንቺው ነበርሽ፡፡

ክሊዎፓትራ፡- እንዴት? ... ምን ማለት ይሆን የፈለግሽ?

አይራ፡- አቤት ያድናቂዎቹ ብዛ. . . ት፣ ስለ ረቂቁ ውበትሽ፡፡

ክሊዎፓትራ፡- የውብ ቃላት ጋጋታ ነው፣ ከልባቸው እንዳይመስልሽ፡፡
ሮማውያን ብታውቂያቸው -
በቃላት ሰው በመሸንገል፣ በዓለም ወደርም የላቸው፡፡
(ለዶላቤላ) ጋለስ፣ ቲቡለስ ሚባሉት፣ ዕውቅ የቅኔ ሊቆቻቸው
“ዴሊያ”ና ቺስሪስ ላይ ነው፣ ይህንን ያስተማሯቸው፡፡

ዶላቤላ፡- እኒህ ያልሻቸው ሮማውያን፣ እንዳልሺው ሊቆች ቢሆንም
ወደ ምድረ ግብፅ የመምጣት፣ ዕድል መቼም አላገኙም፡፡
እንጂ - ዴሊያና ቺስሪስ፣ አርዕስታቸው ባልሆኑም፣
እኔ ሁሉን ያየሁት ግን - የታደልኩ ብሆን ለማጥም
የሚወደስ ውበት ብዬ፣ እነ ዴሊያን አልመርጥም፣
ነበረኝ የምቀኝለት፣ እጅግ የላቀ ጨዋ ሰም፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ይኸውልሃ! አሁን እንኳን፣ ስትሸነግለኝ አየኸው?

ግን ችግሩ ያንተ ሳይሆን፣ የጠቅላላው የዘርህ ነው፡፡

አገራችሁ ዙሪያ ገባው

ሸንጋይ ዋሾ ነው የሞላው!

ይቅርታ አድርግልኝና - ጓደኛህም እንዳንተው ነው፡፡

አሁን ግን ወደኔ የላከህ፣ እኒህን ቃላት ልትነግረኝ

እንዳልሆነ እርገጠኛ ነኝ፡፡

ዶላቤላ፡- በጭራሽ ውዷ እመቤቴ! - እሱ የላከኝ እንኳን ,

ክሊዎፓትራ፡- እ. . .ሺ ? በርግጥ እሱ የላከህ እንኳን?

ዶላቤላ፡- ቅር የሚያሰኝ መልዕክት ነው፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ማለት . . . ማንን ነው ቅር የሚያሰኘው?

እኔኑ ነው ወይ አንተን? አልገባኝም ግልፅ አድርገው፡፡

ዶላቤላ፡- ማዳም - ሁለታችንንም፡፡

አንቺም ማዘንሽ አይቀርም

እኔም አርጂሽ በመሆኔ፣ ከመጨነቅ አላመልጥም፡፡

ክሊዎፓትራ፡- አይራና ቻርሚዎን - አንዴ፣ ይሄን መልእክት እስክሰማ

ትንሽ ራቅ በሉና፣ ጠብቁኝ እዚያ ገደማ፡፡

/ለራሷ/ መንፈሴ - እንግዲህ በርታ በል፡፡

እሺ - አሳዛኙን መልዕክትህን ፣ ዝግጁ ነኝ ለመቀበል፡፡

በል እስቲ አምጣው ንገረኝ

ለነገሩ - ምን እንደሆን፣ መገመትም አይቸግረኝ፡፡

ዶላቤላ፡- በገመትሺው ደስ ባለኝ

መሪር ዜና እንደመንገር፣ ምስጋና አልባ ምግባር የለም፡፡

ከዚህ በላይ ደግሞ እኔ - ከፆታዎችሽ በሙሉ፣ ከሚገኙት በዚህ አለም

አንቺን እመቤቴን ማስቀየም፣ ከቶ ፍቃዴ አይደለም።።

ክሊዮፓትራ፡- በጭራሽ ሃሳብ አይግባህ! -እንዳልከው ብታስቀይመኝ-

ከፆታዎችህ በሙሉ፣ ከሚገኙት በዚህ ዓለም፣ አንተን ይቅር የምልህ ነኝ።።

ቤንቲዬሞስ፡- (ለራሱ) አቤት ሴት! አቤት ሔዋን ዘር! - እዩ ስትቀርበው አድብታ

ረቂቅ - የተረገመ -ተለዋዋጭ፣ እስስት ፆታ!

ክሊዎፓትራ፡- ምናለ ታድያ -እለፈው! -ይህን ያህል መጨነቅህ፣ መጠበብህ ለምኑ ነው?

ከአንቶኒ ቀጥሎ ያለው -ልጨነቅለት ምችለው

ያው እንግዲህ ግዛቴ ነው።።

ዶላቤላ፡- የኔ እመቤት

በርግጥ ስለ ሃዘን ያለሽ፣ እጅግ የጠለቀ ስሜት

የማመዛን ቀልብሽ፣ አዛብቶብሽ እንዳይሆን ነው

አሁን በእጅጉ 'ምስጋናው።።

ክሊዎፓትራ፡- ኧረ በጭራሽ! -ምነው ያበድኩ እመስላለሁ?

ይሄ ምንም አያሳስብህ - ዕድል የሚጭንብኝን፣ ለመሸከም እችላለሁ።።

የፍቅር ሰንኮፋም ቢሆን፣ በሌላ ፍቅር ይነቀላል

እሾህም በሾህ ይወጣል - መርዝም ያው በመርዝ ረክሳል

እንጂ ፍቅሬን አጣሁ ብሎ፣ ማን ራሱን ሰቅሎ ይገላል?

ዶላቤላ ፡- እጅግ ከሚገባው በላይ፣ ተደሰትኩኝ እመቤቴ!

ሃዘንሽን እንዲህ በቀላል፣ ስትወስጂው በማየቴ ።።

በቃ ይኸው ነው መልዕክቱ፣ እንደገመትሺው ነው ሁሉም

ታድያ - ወንዶች ሁሉ እንደሱ፣ ከዳተኞች እኮ አይደሉም።።

ክሊዎፓትራ፡- ኧረ እንደሱስ አያርጋቸው!

ዶላ ቤላ ፡- አንዳንድ ወንዶች አይታጡም፣ 'ሚገኙ እንዳስቀመጧቸው።።

ክሊዎፓትራ፡- እንዳስቀመጡት መገኘት -

ሊከፈለው የሚገባ፣ ጨዋ ምግባር ነው ስለውነት!

ዶላቤላ ፡- ሊከፈለውስ አይገባም - ለጊዜው ወጉ ይቅርበት

ግን ተስፋ ያርግ ፍቀጂለት፡፡

ቤንቲዬሞስ፡- (ለራሱ) በአምላክ ስም እምላለሁ፣ የኔን ፈቅድ አግኝተሃል፡

አሁንስ ልሂድ ይበቃል

ይህ መልካም አጋጣሚ፣ ብጠቀምበት ነው ሚሻል

(ይወጣል)

ዶላቤላ ፡- ደምሽን ከገፅሽ መጥጦ፣ አሸቦ የሚያስመስልሽ

የመሰለኝ ዜና ነበር፣ የመጣሁ እዚህ ልነገርሽ፡፡

ክሊዎ ፓትራ ቆይ እስቲ አንድ ዶላቤላ - አሁን ማወቅ ምፈልገው

መልዕክቱን ይዘህ ለመምጣት፣ ጌታዬ ነው የመረጠህ፣ ወይስ አንተው ፈልገህ ነው?

ዶላቤላ ፡- ራሱ ነው የመረጠኝ -

የልብ ወዳጁ ነኝናም፣ እሱን ሆኜ እንድናገር፣ ቃላቶችን አስታጥቀኝ፡፡

ክሊዮፓትራ፡- እንግዲያውማ መልዕክቱ፣ ግሩም እንሆነ አውቃለሁ እንደዘፈን እንደሚፈስ

ለእያንዳንዱ ቃል ተጠርቦ ፣ ተልጎና ተድቦልቡሎ፣ ኩላሊት እስኪመስል ድረስ

“መለየት” የሚባለውን፣ ሻካራ ቃል ለማለስለስ

አይቀሬውን መራር ፅዋ፣ እጋተውም ዘንድ ቀስ በቀስ፡፡

ዶላቤላ ፡- ተሳስተሻል እመቤቱ - እንዳልሺው በሆነ ምነው!

እጅግ የሚጎረብጡ፣ ቃላቶችን ነው የመረጠው፡፡

በሚንቦገቦጉ ዐይኖች፣ እና በጨርማታ ግንባር

ፊቱን ጠልሰም አስመስሎ፣ ተጸናውቶት አንዳች ዛር

ምድር እንደራደች ዓይነት፣ መላ አካሉን እየናጠው

እንደ በሬ እያስጓራው፣ እና ትንፋሽ እያጠረው

የሰው ልጅ በማይመስል ድምፅ፣ ነበር የተናገረው፡፡

(ዐይኗን ለመሸሽ ፊቱን ያዞራል።)

“ከዚህ ትራቅ ለዘላለም” አልፈልግም ዐይኗን ላየው!

ጦሴን ይዛ ገደል ትግባ! በሷነው ስሜ ያደፈው!

እና የተስፋ መቅረዜ፣ ዳግም ላይበራ የወደመው!

(እሱ እኒህን ንግግሮች ሲናገር ክሊዎፓትራ እየደነገጠች እየ ደነገጠች በመጨረሻም መቆም ይሳናትና በዝግታ ዝቅ እያለች መሬት ትይዛለች።)

ትባረር -ትሰደድ -ትራቅ! ትሂድ ወደ ዓለም ዳርቻ! የወንድ ልጅ ከማይደርሰው

ከዚያም ቢሆን የሷ ሾተል፣ መሃል ድረስ ሚመርዝ ነው!” ነበር ያለው።

ክሊዎፓትራ ፡- በቃኝ! በቃኝ! - ይህ ከአቅሜ በላይ ነው!

ዶላቤላ ፡- (ዘወር ብሎ ሲያያት) ጉድ ፈላ - አቤት ጥፋት!

አቤት እርግማን! አቤት መዓት!

ኧረ ምንድነው የሰራሁት? ኧረ አምላኬ አንድ በላት!

ቻርሚዮን፡- ውይ በሞትኩት! ኧረ አይራ ድረሺልኝ! እመቤቴን ምን ላርጋት?

አይራ፡- ደግፊያት! ፍጠኝ ደግፊያት! ከአንገቷ ቀና አድርጊያት - አይዞሽ አሁን ነው ሚሻላት።

ቻርሚዮን፡- ተመስገን . . . ን! - ነፍሷን ዘራላት።

ክሊዎፓትራ፡- አምላክ ምን በድየዋለሁ - ወደዚያው እንዳያስቀረኝ

በመኖር ከማልሻበት፣ ከዚህ ዓለም ሚመልሰኝ?

አቤት ክፋት! አቤት ክፋት!

ዶላቤላ ፡- (እየተንበረከከ) በቃ እመኚኝ እመቤቴ - ኃጢያቴን ልናዘዘው!

አሁን የምናገረው፣ ራሴን የሚነቅፍ ነው።

ስለዚህ ከዚህ ቀጥሎ፣ ካፉ ሚወጣውን ሁሉ፣ ብታምኚው ነው የሚሻለው፡

ጨዋውን ባልንጀራዬን፣ ክፉኛ ነው የበደልኩት!

አሁን ያልኩሽን በሙሉ፣ በእውነት እሱ ብሎት ሳይሆን፣ ራሴው ነኝ የፈጠርኩት።

ምነው አይተሺው በሆነ፣ እየነገረኝ ባለበት

ስንቱ እንደተመላለሰ፣ በነገረኝ መልእክት ላይ፣ ደግ ቃላት ሊያክልበት

ሰግቶ የዜናውን መሻከር፣ መንፈስሽን እንዳይጎዳበት፡፡

የእሱስ ስንብት ክብደቱ

እንዲህ ነው ብሎ ለማውራት፣ ቃላት አይበቁም በውነቱ!

ታድያ እኔ

ለአደራ የማልበቃ፣ ከዳተኛ እንደመሆኔ

እናም ማርከሻ በሌለው፣ በፍቅርሽ ስለተለከፍኩ

አጋጣሚው ቀና መስሎኝ፣ እድሌን ልሞክር ነበር፣ ያንን ውሸት የለፈለፍኩት፡፡

ከህሊናዬ ሙግቱ - ክሱም ፍርዱም አይለ ቀኝም፣ መቼም በህይወት እስካለሁ!

አንቺን ግን ለመበደሌ - ይኸው ፊትሽ ተንበርክኬ! ይቅርታሽን እጠይቃለሁ፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ሆነ የተባለው ነገር፣ ሲሆን እንደምንመኘው - ማመን ምነኛ ቀላል ነው!

በቃ ተነስ ዶላቤላ - ለመርሳት ሞክር ሁሉንም፡፡

በርግጥ እንዳልከው በፊናህ፣ ጥፋተኛ ብትሆንም

እኔም ከወቀሳ አልድንም

ከመጠን ያለፈ ፍቅር፣ አሳስቶኛል እኔንም፡፡

አጋጣሚው ቀና መስሎህ፣ አንድትሞክር እድልህን

ሆነ ብዬ ቆስቁሼብህ፣ ያዳፈንከውን ፍቅርህን

በሃሳዊ ምልክቶች፣ ተስፋ ሰጥቼው ልብህን

ከጥፋት የነከርኩህን፣ እንግዲህ ከተፀፀትክበት

እኔው ራሴ ነኝ እውነት

በቅናት ቢመለስ ብዬ፣ ፍቅሬ ጥሎኝ ከሸሸበት፡፡

የትም የማይደርስ ብልጠት!

አይ እንግዲህ - ከዚያ ወዲያ፣ ልጣው እንጂ ካጣሁትም

በእንዲህ ያለ ተራ ዘዴ፣ በሱ ልብ አልጫወትም!

አማልክት ይቅር ይበሉኝ፣ እስካሁን ላደረኩትም።።

ዶላቤላ ፡- ልብሽ ዙሪያው የታጠረ፣ ሰዎች ጭራሽ የማይደርሱበት፣ መሆኑን አሁን ነው ማየው

እንደብርጭቋማ አለት፣ በውስጡ ያሳያል እንጂ በውስጡ ማለፍ ዘበት ነው።።

አዬ ውዱ ጓደኛዬ! አቤት አለመታደልህ!

ተዝቆ የማያልቅ ሃብት፣ መለኪያ የሌለው ፀጋ፣ አውጥተህ ሜዳ መጣልህ!

ክሊዎፓትራ፡- እኔ ምልህ ዶላቤላ - ጠበቅ አርገህ ብትለምነው

መልዕክት ከሷ አምጥቻለሁ፣ አንዴ አናግረኝ ብትለው

ለአንዲት ሰዓት እንኳ ቢሆን፣ ጆሮውን የሚነፍግ ነው?

ከመለያየታችን በፊት፣ የተራቡትን አይኖቼን፣ ብመግባቸው ብዬ ነው።።

ላልመለስ ስለሆነ፣ ሁሉን ትቼ የምሄደው

ጉዞዬ እጅግ ሩቅ ነው፣ ሞት ሩቅ ከሆነ ያለው።።

(ቤንቲዬዎስና ኦክታቪያ ከመድረኩ በስተጥግ ብቅ ይላሉ)

ዶላቤላ ፡- እመኚኝ አደርገዋለሁ! - ክፍያዬም ይሁንና ስጪኝ ልሳመው እጅሽን

ይህ ብቻ ነው ልመናዬ፣ አትከልክይኝ አደራሽን።።

(እጇን ለመሳም ይይዛል)

ቤንቲዬዎስ፡- (ለኦክታቪያ) ማየት ትችያለሽ ከዚህ -

ኧ. .ረ ? ታደርገው ይሆን ከልብህ? - ለስላሳውም እጇም አማረህ

ቆይ ቆይ ወደኛ እያዩ ናቸው።።

ኦክታቪያ፡- የሌባ አይኖች ፍጥነታቸው!

ቤንቴዲዎስ፡- ልብ ያላልናቸው በመምሰል፣ እስቲ ነይ እንጠጋቸው።።

(ሁለቱም ወደ መድረኩ መሃል ብቅ ይላሉ)

ዶላቤላ ፡- ቤንቴዲዎስ - ንጉሱን አላየኸውም?

ቤንቲዬዎስ፡- እንደውም ።።

እኔም ስፈልገው ነበር -

ግን ሰማሁ አንደማይቀበል፣ ለጊዜው አንዳችም ነገር

ዶላቤላ ፡- ጉዳዬ ምን እንደሆነስ፣ ይኖር ይሆን የምታውቀው?

ቤንቱዲዎስ፡- ለውድ ወንደሙ ለቄሳር፣ ደብዳቤ እየላክ ነው፡፡

ዶላቤላ፡- ነው? መልካም እፈልጋለው ላገኘው

(ዶላቤላና ክሊዎፓትራ ይወጣሉ)

አክታቪያ፡- መቼም አይን አያየው የለው!

ቤንቲዴዎስ፡- በጣም እኮ ነው የሚገርመው!

እኔማ እንደማስበው አኳኋን ሁሉ ላየው

“አክታቪያ ለስካሁኑ፣ በጣም አመሰግናለሁ

ሽማግሌሽን ውሰጂው፣ የተሸለ አግኝቻለሁ፡፡” የምትል ነው የሚመስለው፡፡

እኔ ምልሽ - ከዚህ ምስጢር፣ አሁን ባይናቸውን ካየነው

ምንጠቀመው ምንድነው?

አክታቪያ፡- ምንም መጠቀም አያሻን - እንዳላየን እንቁጠረው፡፡

ቤንታዴዎስ ለየዋለሁ ዶላቤላ፣ አዝን ይሆናል ምን አልባት -

እሷ ግን አደገኛ ናት!

የዐይጂ ሃይል ምትሃቱ፣ ከቱሳልያኖች ይበልጣል!

ጨረቃን ከጥቁር ሰማይ፣ ጎትቶ ማውረድ ይችላል

የአንደበቷ ማርነት- ምን ተብሎ ይነገራል?

እኔ ቤንቲዴዎስ እንኳን- ይህን ያህል የምጠላት -

ጥላቻ በሞላው ሃሴት፣ ነው ውበቷን ማደንቅላት!

የሷስ ውበት እንቆቅልሽ፣ ለዝንተ አለም ይገርመኛል -

በአንደኛው ጎኔ ስረግመው፣ በሌላው ጎኔ ያምረኛል

አየሽ ውዲ አክታቪያ - አሁን እያሰጋኝ ነው

ይኸው የአንቶኒ ነገር ነው፡፡

ከዚች ሴት መርዝ ፍቅር፣ በደንብ የተገላገለ፣ መስሎ ለሱ ቢታየውም

አሁንም ውስጡ የቀረ፣ እርሾ ቢጤ አያጣውም።

ሰንኮፉ ካልተመዘዘ፣ ፍቅሩ ደግሞ ማገርሸቱ፣ ምንም ጥርጥር የለውም።

በነፍሴ እወራረዳለሁ - አሁን በዚች ሰዓት እንኳን

ከቁሳር ጋር 'ሚፃፃፈው፣ አውቃለሁ ስለሷ እንደሆነ፣ ለማውረድ እርቅ ሰላሟን።

አክታቪያ፡- እንዳላየን እንድንቆጥረው፣ አልነበር የፈለኩት?

አሁን ግን ሃሳቤን ቀየርኩ - ያንተን ሃሳብ ተቀበልኩት።

ስለዚህም - ያየነውን

በግልፅ እንነጋገረዋለን! (መሄድ ትጀምራለች)

ለኔም ጥሩ አጋጣሚ ነው - ቅሌቷን እየነገርነው

አጠነዋለሁ ስሜቱን፣ እንዴት እንደሚያጣጥመው

ጉድ! - ለአንዲት ጋለሞታ ሰላም፣ ናላውን እየዞረ ነው ?

አቅለሸለሸኝ ሳስበው!

ይህን የማይመስል ነገር፣ ይሻለዋል ባይሞክረው!

ቤንቲዬሞስ፡- እየመጣ ነው መሰለኝ - አጃቢዎቹ ይታዩኛል-

እኔ ልጀምረውና፣ አንቺ ብትቀጥይ ይሻላል።

(አንቶኒ ይገባል)

አንቶኒ ፡- አክታቪያ - የኔ ፍቅር - ስፈልግሽ እኮ ነበር

ደብዳቤዎችሽ የታሉ? ተጽፎ ተዘጋጅተዋል?

የኔዎቹ መመሪያዎች፣ አንድ ሳይቀር ተላልፈዋል።

አክታቪያ፡- የኔዎቹም - ጌታዬ - ተዘጋጅቶ ተቀምጧል።

አንቶኒ፡- ቤንቲዬሞስ -

ቤንቲዬሞስ፡- አቤት ጌታዬ - ፈለክኝ?

አንቶኒ፡- አዎ አንዳፍታ ለብቻህ ፣ የማናግርህ ነበረኝ።

(ትከሻውን ያዝ አድርጎ ወደ ጎን እየወሰደው) መቼ አየሁ ዶላቤላን?

ቤንቲዴሞስ፡- አሁኑን ነዋ ጌታዬ - አምስት ደቂቃም አልሞላን፡፡

ክሊዎፓትራም አብራው ነበር

ወደኋ እንደሆነ ባላውቅም፣ ወጡ በዚያ በላያኛው በር፡፡

አንቶኒ፡- ድምፅ ቀንስ ስትናገር፡፡ - የስንብት ቃሌን ይዞ

ከሷ ዘንድ እንዲያደርስልኝ፣ ነው የሄደው በኔ ታዞ፡፡

ቤንቲዴሞስ፡- (ድምፁን ሳይቀንስ) እንዴታ! በርግጥ ይመስላል!

የአንተኑ የስንብት ቃል፡፡

አንቶኒ ፡- አረ ቀስ በል - ምን ሆነሃል?

“የአንተን የስንብት ቃል” ? - ምን ለማለት ፈልገህ ነው ?

ምን አልባት - ይህ አባባልህ፣ ምስጢራዊ ትርጉም አለው ?

ከሷ ጋር የተገናኘው፣ በራሴ ትዕዛዝ እኮ ነው!

ቤንቲዴሞስ፡- **(ድምፁን ሳይቀንስ)** እንግዲያውስ ትዛዝህን፣ በደንብ ፈፅሞታል ባይ ነኝ!

ፍቅር በተሞላው መንገድ፣ መልክትህን እንዲነገራት፣ ነበር ያዘዝከው መሰለኝ፡፡

አንቶኒ፡- ይቺ ምስኪን - ያልታደለች!

ክፉውን መርዶ ስትሰማ- አይሆን ያላቸው ሲሆን - ምነኛ ይሆን ያዘነች!

ቤንቲዴሞስ፡- ልክ እንደሚጠብቃት፣ በፀጋ ተቀበለችው!

ያኔ ካንተ በፊት ቄሳር፣ ሲለያት እንዳረገችው፡፡

ወደ ፊትም ካፈቀረች -

የዛንም እንደምትችለው፣ ነው ያንተን መለየትና መራቅህንም የቻለች፡፡

እንጂ እንዳይመስልህ ጌታዬ፣ ደንግጣ ራሷን የሳተች

ወይ ራሷን ልገድል ያለች፡፡

አንቶኒ ፡- (መንሾካሸኩን ይተውና ጮክ ብሎ) ተራ ባለጌ ሰው አርገህ

ስሚን እያጠፋኸው ነህ!

ይህን ያህል ለመጥመድስ፣ ምንም በቂ ምክንያት የለህ!

ቤንቲዴሞስ፡-	እንዲህ ተከፍለህ ብዬስ፣ ፍፁም አላሰብኩም ነበር

ባልነግርህስ ኑሮ ቢቀር፡፡

ኦክታቪያ፡-	(ወደ ነሱ እየቀረበች) ጌታዬ ምን ሁናችኋል? - ጭቅጭቅ ነው ወይስ ምክር?

የተረበሽ ትመስላለህ፣ አጋጠመህ እንዴ ችግር?

አንቶኒ ፡-	አይ- እንደው ትንሽ ነገር ነው፣ እንዲህም አያነጋግር

ሂጂ ግቢ የኔ ፍቅር

ቤንቲዴሞስ፡-	እንዲህም አርጎ “ትንሽ” የለህ፡፡

በራሱ ትዛዝ-

አንቶኒ፡-	(በኃይለ ቃል) በቃህ አሁን - አፍህን ያዝ!

ነግሬሃለሁ ተጠንቀቅ - አልታዘዝም ብትለኝ

በህይወትህ ነው ምትከፍለኝ!

ኦክታቪያ፡-	ይህን ያህል የሚያስቆጣህን፣ ነገር ነው “ትንሽ” ምትለኝ?

ቤንቲዴሞስ፡-	(ለኦክቶቪያ) “ትንሽ” አለው፣ “ትልቅ” አለው

አንቺም በአይንሽ ያየሽው ነው - ምንም ምስጢርነት የለው፡፡

አንቶኒ ፡-	በዐይኗ ያየችው ነገር ነው? - ድብብቅ ይበቃል?

ቤንቲዴሞስ አዎ - ሁሉንም አይታለች - ወጣቱ ዶላቤላ -

አንቶኒ ፡-	(በምፀት) ሃ ሃ ሃ! “ወጣቱ ዶላቤላ”! —

ቤንቲዴሞስ፡-	ወጣት አይደለም ብላ

እኔ መቼም - በኔው ግምት፣ ወጣት ብዬ ነው ማስበው

መልከ ቀናነቱም ቢሆን፣ ይቺን ታክል እንከን የለው

ደግሞም የኔ ብቻ ሳይሆን፣ የሁሉም ግምት ይሆናል፡፡

አንቶኒ	ነ . . .ው ?

ቤንቲዴሞስ፡-	ለነገሩ - ፉንጋ ሆነ መልከ ቀና

ምን ዋጋ አለው? የቀረባት፣ በራስህ ትዛዝ ነውና።

በርግጥም ይመስል ነበር፣ የምስራች የላክህላት

የደስታ ፊት ስለነበር፣ ያሳየች ዜናው ሲደርሳት።

ፈገግ ነበር ያለችው

ወዲያው እጇን በእጆቹ፣ የመንካት ፍቃድ ሰጠችው።

እጇን አሻሻው- ጨመቀው

በተራቡ ከንፈሮቹ፣ እየሳመ ቢያስጨንቀው

እንደማፈር አለችና- በረጅሙ ተነፈሰች

ከዚያም- ፈገግታ አሳይታ፣ መልሳ ተሸኮረመመች

በመጨረሻም- አንዳች ነገር በለሆሳስ፣ ምትነግረው እየመሰለች

ጉንጯን ወደ ሱ ጠጋ አርጋ፣ ከጉንጩ ላይ አስደገፈች

ይሄን ግዜ ዞር አለና - አራስ ልጅ ያገኘ አይነት ጉንጯን በጉጉት ቢስመው

ጮክ ብላ ተናገረች፣ እንዳስቀመጡት መገኘት፣ ዋጋው እንደሚከፍለው።

አክታቪያ፡- ይህን በዓይኔ አይቻለሁ

በጆሮዬም ሰምቻለሁ።

አንቶኒ ፡- የቷ ሴት ትሆን በሞቴ፣ ያያችሁ የሰማችሁት፣ እኒህን ቃላት ስታወራ?

ከገዛ ጓደኛዬ ጋር፣ እንደልባ ስትዳራ !

መቼም አትሆን ክሊዎፓትራ?

ቤንቲዬሞስ፡- ጌታዬ እሷኑ ነዋ!

አንቶኒ ፡- ክሊዎፓትራ የኔዋ?

ቤንቲዬሞስ፡- አዎ ያንተ ክሊዎፓትራ! የዶላቤላ ክለዎፓትራ! - የሁሉ ወንድ ክሊዎፓትራ!

አንቶኒ ፡- ውሸት! - ሊሆን አይችልም በፍፁም!

ቤንቲዬሞስ፡- ጌታዬ እመነኝ ባክህ፣ አንድም ነገር አልዋሸሁም።

ምንስ ያጠራጥርሃል?

ቅምጦች ችላ ሲባሉ፣ ወንድን በወንድ እንዲተኩ፣ ለአንተስ ቢሆን ይጠፋሃል?

አንቶኒ፡- በዚህ ጉዳይ ላይ ከእንግዲህ፣ ማሰብም አያስፈልገኝ!

ውሸት ነው! - እርግጠኛ ነኝ!

ደባው የናንተ መሆኑ ቁልጭ ብሎ ነው የታየኝ፡፡

ኦክታቭያ - ልግለፅልሽ አንድ ነገር -

በእንዲህ አይነት አጉል መንገድ፣ መሄድ አይገባሽም ነበር፡፡

ያየሁትንም አይቼ፣ ምሬሻለሁ ተይው ይቅር

ከዚህ በላይ ግን አትግፊኝ፣ አደራሽን የኔ ፍቅር፡፡

ኦክታቭያ፡- የሷ በቅሌት መገኘት፣ አንተን ይመለከትሃል?

ምን እንዲህ ያስጨንቅሃል?

አንቶኒ ፡- እንዴት አያስጨንቀኝም?

ምንም ከእንግዲህ ከሷ ጋር፣ እህል ውሃ ባይኖረኝም

አለም የቀድሞ ምርጫዬን፣ ቢያንኳስሰው አይጥመኝም

የማትራብ ወዶ ነበር፣ መባልም ደግ አይመስለኝም፡፡

የሆነው ሆኖ- ግድ የለም፣ በበኩሌ ትቼዋለሁ

አንቺንም ጓደኛዬንም፣ ከልቤ ምሬያችኋለሁ፡፡

ቤንቲዴሞስ፡- ይህን የአዛውንት እድሜዬን፣ እንዴት ብታጣጥለው ነው

እንደ ዋሾ ማላፋቴ፣ ባሰተኛ አሉባልታ፣ ጆሮህን እንደማጓድፈው

አድርገህ የምታስበው?

እሷን እውነተኛ ነች ካልክ

መንግስተ-ሰማይ ነው የካድክ!

አንቶኒ ፡- መንግስተ - ሰማይም ሆነ፣ ምድሪቱ ቢመሰክሩ

በሷ ላይ ያለኝን እምነት፣ ከቶ አይችሉም ሊቀይ!

ቤንቲዴሞስ እንግዲያውስ ላምጣልህ፣ የገሃነሙን ምስክር

ስለዚች ሴት ማንነት፣ የሚያስረዳህን በዝርዝር -

(አሌክሳስ ልክ ይገባና ወደ ኋላው እንደመመለስ ሲያቅተው ቤንቲዬሞስ ያየዋል)

እኮ ወዬት? ነው ምትመለሰው?

ና ወዲህ ትፈለጋለህ፣ መቆየትህም ግድ ነው

አሌክሳስ፡- ጌታው - ፈልገኸኝ ነበር?

ቤንቲዬሞስ እንድትሰራ ላደርግህ ነው፣ እጅግ የምትጠላውን ነገር - እውነትን በግልፅ መናገር፡፡

የመቤትህ የክሊዎፓትራ፣ የጓዳ አማካሪዋ

እናው ምስጢሬ ባለችው፣ አድራጊ ና ፈጣሪዋ

መሆንህ ማንም ያውቃል፣ እና እንዳትክደኝ ተጠንቀቅ

አሌክሳስ፡- የተከበርከው ጌታዬ-

ቤንቲዬሞስ፡- በሽፍት ሰብቅ የተካንከው፣ አቃጣሪ ደላላዬ!

መርፌና ክር አገናኙ፣ እግር ያዥ ጃንደረባዬ!

ንግግርህ ለማራቀቅ - ለአንደበትህ ጣም ለመስጠት - ወይም ውብ ድርሰት ልትፈጥር

እና ማወቅ ከምንሻው፣ ፍሬ ነገር ልታርቀን፣ በምንም አይነት አትሞክር፡፡

አሁን ከአንተ የሚፈለገው

ብርዝ ክልስ የሌለበት፣ ንጹህ የቤት ፈትል እውነት፣ እንድታወራ ብቻ ነው፡፡

ንግስትህ ከዶላቤላ፣ በፍቅር ፈረስ ስትጋልብ፣ እኔ ራሴ ባይኔ አይቻለሁ፡፡

ምን ምን ተጨማሪ ጉዳይ፣በሚስጥር እንደሚፍፀም ካንተ አፍ መስማት እፈልጋለው፡፡

ምን ያህል ነው ያቀረቡህ አንተንስ በምን ግብራቸው ?

ሰአቱ መቼ መቼ ነው ፣አላማቸውን መቅጫቸው ?

አንቶኒ፡- አልክሳስ እውነት የመናገር መብትህ እንዳልተነፈገ እወቅ

ለቤንቲዲዎስ ቢጥመው -ወይ ባይጥመው አትጨነቅ ::

የተጎዳች ንግስትህን፣ ሃቀኝነት አስረዳና

ይህን ከንቱ ጥላቻዋን አስቀርባት መና

አክታቪያ፡- (ጉምጉምታ) ጉድ እዩልኝ ! እንዴት አድርጎ የልብ የልብ ይሰጠዋል !

ሃሳዊነቷን ለማወቅ ፣ሃቁን እንዴት ይፈራዋል

ለካ አይኖቹነም የጨፈነው

እውነቱን ከማየት ይልቅ፣ መሳሳቱን ቢመርጥ ነው

አይ ወንድ አይ ወንድ- እንዴው አምላክ ለምን ይሆን፣ እንዲህ ጅል አድርጎ የፈጠረው

አሌክሳስ፡- ያፍቃሪዋ የጌታዬን ማንነቱ፣ ጨዋነቱ ፣ብስለቱ ፣ታላቅነቱ

ፍቅሩም ግብሩም ከሰው መሃል፣ እኩያ ወደር ማጣቱ

እንድትወደው ቢያስገድዳት

ሴት ልጅ ልቧ ስስ ነውና ፣ ጥንቱንም አምላክ ሲፈጥራት

ጥፋቷ መራር አይደለም፣ ያን ያህል ’ሚያስኮንናት

ለዚህ -ፍቅር ራሱ ነው ፣ጠበቃዋ ’ሚሆናት

እና እስካሁንም ለሆነው ቅዱስቱን አክታቪያን፣ ለጥ ብየ ’ምለምንነው

ንግስቱ በውዱ ጌታሽ ፣የፍቅር መረብ መውደቋን፣ ይቅር እንድትይልኝ ነው።

የጀግናው ቤንቲዬሶስ -ልቡን አምላክ ያራራላት

ያለፉ ትን ድርጊቶቿን ፣ አመዛዝኖ ይቅር ቢላቸው።

አንቶኒ ፡- ድንቅ በሆነ ሁኔታ ፣ ሀቁን ነው የተናገረው

ቤቱሊዮስ ልብ ቢለው !

አሌክሳስ፡- (ለአንቶኒ) ታላቁ ጨዋ ንጉስ ሆይ አንተን ግን በሚመለከት

ለድሪጊቷ ያበቃትን ፣በቂ ምክንያት ለመስጠት

እንጂ አይደለም ላስቸግርህ ፣አንተም ይቅርታ እንድትላት ፣ይቅር መባል በሌለበት

የውበቷ ምትሃት ብቻ -ዘውድ ዙፋኗ ሳይጨመር ንጉሶችን የሳበ ነው ፣ ከኢትዮጵያ ምድር ሳይቅር።

የአለም በትረ መንግስቶች፣ ከእግሯ ስር ተኮልኩለው ፣ ክምርም ሰርተው ከፊቷ

ከመሃላቸው እንትመረጥ ፣ያሻችው ሊሆን ግዛቷ

ልምምጣቸው ቢያይልም፣ስጦታቸው ቢደረደር

ይመጥነኛል ያለችው ፣ሮማዊ ብቻ ነበር፡፡

ደግሞም ከሮማንውያኖቹ

ታላቁ ማርካቶኒ እንጂ፡፡ልባባይገቡ ሌሎቹ

በወግ በማእረግ እጇን፣ የለመኑን ሁሉ ናቀች

ከሚስት ባነሰም መጠሪያ፣ ያነተ መሆኑን መረጠች፡፡

አንቶኒ ፡- እየተናገርከው ያለው አንድም ሳይቀር ትክክል ነው!

አሌክሳስ፡- የሆነው ሆኖ ጌታዬ- ምንም እንኳን ሃያል ፍቅር፣ አደብ ሚዛኗን አስቶ

ህሊናዋን በመተብተብ፣ ይሉንታዋን አሳጥቶ

አሸቀንጥሮ ቢያሶጣትም ፣ከክብር ጎራ ጎትቶ

አሁን በስተመጨረሻ ፣አምላክ አይኗ ሲገልፅላት

የተቀደሰ አልገዋን ያለ አግባቡ በመቀማት

ጨዋዋን ሴት ኦክሽታቪያን ፣ክፉኛ እንደበደለቻት

ሃጢያቷ ግልፅ ሲሆንላት

የፍቅር ሃያል ሰንኮፍ፣ ከልቧ ነቅሎ መጣሉ፣ ቀላል ሆኖ አልታይ ቢላት

ከዚህ የሚያሳዝን እና ፣አጉል ውሳኔ ላይ ጣላት

ቤንቴዲዮስ፡- አሃ! -ዞረህ ዞረህ አመጣኸው

ልብ በሉልኝ ሰውየውን ፣ ነገሩን ሲያስተካክለው

ፍሬ ቢጤ ያለው ነገር ፣ማውራት እየጀመረ ነው

አትፍራ እነጂ ጃንደረባው ቀላል ጥሩ ጀምረሃል

ንጉሱ እንዲሁ እንደልብህ ፣ትናገር ዘንድ ፈቅዶልሃል

አሌክሳስ፡- ባይፈቀድልኛማ ኖሮ- እንደመጨረሻ አማራጭ ንግስቱ የወሰደችውን

ልነግርው ባልደፈርኩ ነበር፣ ለጆሮ የማይጥመውን፡፡

ሆኖም -የልቧን አቅጣጫ ፣ለመቀየር ብትጥርም

ስሜቷ ሙሉ በሙሉ ተለውጧል ልል አልደፍርም።።

አንቶኒ፡- ባትደፍር ነው የሚሻልህ!

እንደዚህ አይነት የሞት ቃል፣ ይወጣና ከዚህ ካፍህ

ይህን ተብታቢ አናክን ፣ሰንጥቄ ነው የማሳርፍህ።።

ኦክሽታቪያ (ጉምጉምታ)ይህን መቻል ያለብኝ እኔ ነኝ ?

አምላኬ ፅናቱን ስጠኝ

ቤንቲዬሞስ፡- ሽጋው ጃንደረባ- ቀጥል !

ቀጥል አንተ የወንድ ግማሽ፣ ለምንድነው ዝም የምትል

አሌክሳስ፡- እንደውነቱ-ዶላቤላንም ካየነው

ባይኑ ካያት ግዜ አንስቶ ፣በልቡ አፍቃሪዋ ነው ።።

ከጌታየ መቆየቱን ፣ የእድል ጉዳይ ካዛባባት

እና የሃዘኗ መፅናኛ ፣ የግዷን መሻት ካለባት

እንግዲህ ማን አለ ሌላ፣ ከዶላቤላ 'ሚቀርባት

ጌታየም ከተዋት ወዲህ

አንቶኒ፡- ጥፋኮ ነው የምልህ ከዚህ!

አሁን ትግስቱ ተሟጧል ፣ አልሻም በአይኔ ላይህ!

(አሌክሳስ በአንቶኒ ተባሮ ይወጣል) በለ አሁን ከአጠገቤ ራቅ አንገትህ ሳልበጥስልህ !

ኦክታቪያ፡- አግባብም አይደል ጌታዬ- ስለአውነት አግባብ አይደለም

ባለቤትህ ፊትህ ቆሜ ፣ከሌለው ምቆጠርበት፣ ምንም አይነት ምክንያት የለም።።

ጨዋ ሴት በሆነችና ፣በተቆጨህ ባማረብህ!

ላንዲት ከሃዲ መለኮን ፣ነው እንደህ መነገብገቤ

አንቶኒ ፡- ኦክሽታቪያ- ከፊቴ ሂጂ፣ክፉኛ ተረብሻለው

ኦክሽታቪያ፡- እንዬ-ጌታዬ ምነው ?

አንቶኒ ፡-	ዞር በይኮ ነው የምለው !

ቤንቲዬሞስ፡-	ግድየለም ማዳም ታዘኸው-ለግዜው ቁጣው እስቂለቀው

ገለል ማለት ነው የሚሻለው፡፡

አክታቪያ፡-	ምን ባጠፋሁ ነው ጌታየ፣ ዞርበይ ከፊቴ 'ምትለኝ ?

ሀፍረተ ቢስ ከሃዲዋን ፣ኪሎ ፓትራን አደረከኝ ?

አዎ - እሷንማ ብሆን ኖሮ፣ እምነት ሃይማኖተወ የሌለኝ

እንኳስ ኃይለ ቃል ወጥቶህ፣ ከፊቴ ሂጅ ልትለኝ

አንገቴ ላይ ተንጠልጥለህ፣ ቃሌን ሁሉ እንደ አምላክ ቃል፣ ነበር የምትቀበለኝ፡፡

ጭራሹኑ አንተው ነበርክ፣ አስነዋሪ ስራዎችን፣ ልትሸፍንልኝ ምትገኝ

አንቶኒ፡-	ኦክታቪያ- አይታይሽም?-የተሳፈረኝ ሰቆቃ፣ምን ያህል እንደበዛብኝ ?

ምናለ ታዲያ በዚህ ላይ፣ አንቺ ባትመጪብኝ-

ውቃቢ አምላኪ ቢቀርብኝ፣ ልማከረው ምችለው

እስኪ ለብቻዬ ሆኜ፣ ይሄን ነገር ላሰላስለው

እና- ባክሽ ኦክታቪያ፣ ያሁኗን ብቻ ታገ- ሌላ ምንም የለኝ/ምለ

ኦክታቪያ፡-	እንግዲያው ልንገር አይደ- ብቸኝነት የፈለግከው

ፍቅረኛ ስለከዳችህ፣ ለማዘን እንዲመችህ ነው፡፡

ቀድሞም በሲሶው ልብህ ነው፣ ወደኔ የተመለስከው !

እንጂ የቀረውንማ፣ እዚያው ለሷ ነው የተውከው፡፡

ለወንድሜም መልክት ስትልክ

የሷን ጉዳይ እንዳካተትክ- አንዳንድ ወሬ ሰምቻለሁ

እናም በጣም አመሰግናለው!

ለኔ ያለህን ታላቅ ፍቅር፤ በደንብ አረጋግጫለሁ!

አንቶኒ፡-	አረ ባክህ ቢንቴዬሞስ- ባልንጀራዬም አልነበርክ?

ወይስ አንተም ተለወጥክ፣ ሌላኛው ዶላቤላ ሆንክ?

እያየህ ዝም የምትለኝ

ግዴለም ለጊዜው ዞር በይ፣ ፣ ምክር መቀበል አይጎዳም፡፡

አክታቪያ፡- እሺ- መሄድ እሄዳለው

ተመልሼ እንደማልመጣ፣ ግን እንድታውቅ እፈልጋለው፡፡

የረጅም ጊዜ ጭካኔ፣ እና ንቀት ሲበዛበት

ፍቅርም አቅሙ ይሳሳና፣ ችሎ ፀንቶ ከቆየበት- ይገነደሳል በድንገት፡፡

ስለዚህ- አይዞክ ጌታዬ ፣ ይቺ ጋኒን ብለህ ያልካት

ከንግዲህ በህይወትህ ውስጥ፣ እንደማትኖር አውቀህ እርሳት፡፡

ከኔ ያዳላህላት፣ ተመለስና ውሰዳት!

እጠጠበቀችህ ነው ያለች፣ አውቃ እነምደምትጠራት፡፡

አይ መጃጃል! አይ መሳሳት

እኔም ይብቃኝ- በበደል ላይ፣ በደል አይደራረብብኝ-

ምንም እንኳን ህሊናዬ፣ ካንተ እንድቆይ ባይፈቅድልኝ

ላድርግልህ ሚገባኝን፣ ውለታ ሁሉ የማደርግ ሃላፊነት ስላለብኝ

ወንድሜን በሚመለከት፣ቃል የገባሁት ነገር ፣ እንዳልተውኩት እወቅልኝ፡፡

አብረን ላሳለፍናቸውም፣ ደግ የትዳር ጊዜዬት ሁሉ

ርህራሄና ሃሳቤ፣ ያንተው ሆነው ይቆያሉ፡፡

ከንግዲህ አንተን ሙሉሀን፣ የማግኘት ተስፋ የለኝም!

ስለዚህ በቃኝ ጌታዬ- ደህና ሁን አንገናኝም፡፡

(ትወጣለች)

ቤንቲዴሞስ፡- ግዴለም እናንተ አማልክት!

አሳር ፍዳዬን ቆጥሬ፣ ያስተካከልኩትን ሁሉ፣አገባችሁት ከትቢያ?

ምነው ወደዚህ ወርዳቹ፣ በገጠማችሁት ፍልሚያ!

አንቶኒ፡- እ..... ሺ ዶላቤላ- መልክቴን በደንብ አደረስክ?

ዶላቤላ፡- አድርሻለሁ ጌታዬ- ልቤሳይፈቅደው ቢሆንም፡፡

አንቶኒ፡- ልቤ ሳይፈቅደው ቢሆንም

ምኑን ነው ልብ ማይፈቅደው? የኔና እሷ መለያት፣ አስጨንቆሃል አንተንም?

ደስ ሊልህ በተገባ፣ ነበርእንጂ ይልቁንም።።

ዶላቤላ፡- ለምንድነው ደስ የሚለኝ?

አንቶኒ፡- **(በምፀት)** ከልብህ ስለምትወደኝ! ሃሃሃ!

ከገባሁበት ክፉ ወጥመድ፣ ብወጣ ስለምትመኝ! ሃሃሃ!

መሆኑንስ እንዴት ነበር? - መልክቱን ስትወስድላት-

ለይምሰል ለወጉ ሳይሆን፣ ካንጀቴ ያዘንኩ መሆኔን፣ ደህና አድርገህ ገለፅክላት

ዶላቤላ፡- በእጅጉ ነው ምታፈቅርህ - አንተን ካጣች መላም የላት፣ ከሁኔታዋ እንዳየኋት።።

አንቶኒ፡- እ.....! እሱን እኔስ መች አጣሁት?

የኔው ኪሎፓትራ ፣ ምን ያህል እንደምታፈቅረኝ

አንተ አይደለህም ምትነግረኝ።።

ታዲያ- ይቺን ፍፁምና፣ ዕፁብ ድንቅ ፍጡር ነው

ትቼ መሄድ የምችለው

ዶላቤላ፡- አልዋሽህም- እኔም ባንተ ቦታብሆን ፣ አይመስለኝም የማደርገው።።

አንቶኒ፡- ምነው? - ትተሃትካልሄድክ እያልክ ታስጨንቀኝ አልነበር?

አሁን ምን ምክንያት አገኘህ፣ ሃሳብህን ለመቀየር?

ዶላቤላ፡- ቀድሞስ ነገፍሬህ አልነበር፣ ደንዳና አንጀት እንደሌለኝ?

ሲቃ ድምጹአን መስማትና፣ እንባዋን ማየት አቃተኝ

ልቋቋመው የማልችለው፣ ሃዘኔታ ልቤን ፈታኝ።።

እና ያንተም ልብ እንደነው፣ ቢረታ እጅግ እመኛለው

ለመጨረሻ ስንብቷ ፣ አንዴ እንደምታገኝህ፣ ቃል ገብቼላታለሁ።።

እንዲያውም መጣች መሰለ

ቃል በገባሁት መሰረት፣ እንድሁን እርግጠኛ ነኝ።።

(ኪሎዋፓትራ ትገባለች)

አንቶኒ፡- እስቲ ትክ ብለህ እየኝ

ዶላቤላ፡- እ?- ጌታዬ ምን አልከኝ?

አንቶኒ፡- ዶላቤላ-መሰሪ ነህ!

ዶላቤላ፡- መሰሪ? ምኑ ነው እንዲህ ያሰኘህ?

ጌታዬ- መሰሪ ማነው?

አንቶኒ፡- አታስመስል ያልሰማኸው!

መሰሪ ብዬ የጠራሁ፣ አንተኑ ዶላቤላ ነው።።

ኪሎፓትራም ሆነች አንተ፣ ፈሪዛ አምላክ የሌላችሁ

ሁለት መሰሪዎች ናችሁ!

ዶላቤላ፡- ጌታዬ እኔን እንዲ አልከኝ?

ይሄ ነው ለኔ የሚገባኝ?

ኪሊዎፓትራ፡- አረ ምኑን ነው ሚያሰማኝ?

የጫነብኝ ስቃይ አንሶኝ፣አምላክ ሌላምአዘጋጅቷል?

ከመለያየታችንም፣ የባሰ የርግማን ፍርጃ እጣዬ ላ ተመዘግቧል

አንቶኒ፡- አዎ አምላክ ሚዛን ካልጎደለው

አንቺን ገነማ ሚጠብቅሽ፣ ከዚህ ሺህ እጅ የከፋ ነው! አረ የናንተስ ጉዳችሁ፣ አይገኝለት

ምነው በገደለኝ ኖሮ፣ ከናንተ ያገኛኘኝ ለት!

እኔን? እኔን እንዲህ ጉድ ትሰሩኝ? -እኮ እኔን

እምኘየ ለሰጠኂቹ፣ ሙሉ ልቤንና ነፍሰን

ከናንተ ሌላ ፍላጎት፣ ደስታ ላልነበረኝ

ይሄ ነው ሚከፈለኝ?

ምነው ዶላቤላ! -ምነው ኪሊዎፓትራ!

ነፍሳቹ ጡርም አትፈራ?

ዶላቤላ፡- በድላህ ከሆነ በእውነት

ፍትህ ያማልክት ነውና፣ የእጂንይስጣት ያለምህረት!

አንቶኒ፡- በድላኝ ከሆነ ነእውነት!

ሃሃሃ! ውድ ወዳጄ- እንደው በዝች ሰአት እንኳን፣ፌዝ ቢቀር ምናልባት?

አንተ ነፃ መሆንህ ነው? እጅህ ከምኑም የለበት?

ግን እስኪ ቆይ ዶላ ቤላ-መቼም አትክደው ጉድ የለህ-

ፍቅሯ በልቤ የለም ብለህ

አሁን ፊቴ ትመጣለህ?

ዶላቤላ፡- እውነቱን ንገረኝ ካልከኝ-አንተን ምወድህን ያህል

ልወዳትም ብጥር አልችል፡፡

አንቶኒ፡- አይደለ.....ም?

ጓደኝነት ሚፈቅድልህ፣ አንድም ፀያፊ ነገር የለም!

እልም ያልከው ቀጣፊ ነህ

አለማፍቀርህን እንኳን፣ ለመማል ስላልተቻለህ

ያንተን ያህል- የሷን ያህል - እያልክ ታደናግራለህ፡፡

ደግሞ ከካሃዲነት፣ ግብዝነት ይብሳል

አልወዳትም ብትል - አሷን እወዳታለው ብትል እኔን፣ ማስቀየሙ አስግቶሃል፡፡

አይ የኛ አደናጋሪ!- አደናግረህ ልብህ ወልቋል!

ምንም ልትክደኝ አትሞክር፣ ቤንቲዬዎስ ሁሉን ሰምቷል

ኦክታቪያም ዐይኗ አይቷል፡፡

ኪሊዎፓትራ፡- የጠላት ምስክር የለም!

አንቶኒ፡- የአሌክሳንስ ምን ትይው? አሌክሳስ ጠላት አይደለም!

ከሱም በላይ ሚያውቀው የለ፣ እሱም ሁሉን ተናዝዞታል

ደባችሁ ከሀ እስከ ፐ፣ ከፊቲ አዝረክርኮታል፡፡

(ለዶላቤላ) ለነገሩ ካንተ በላይ፣ ምን ምስክር አስፈለገኝ?

ለስንብቴ ብልክህ ፣ ዋስ ጠበቃ አማላጂ፣ ሆነህ አይደል የጠበቅከኝ?

ዶላቤላ፡- እንግዲህ ምን መናገር እችላለሁ?

መውደድ ኃጥያት ከሆነ... ኃጥያተኛ ነኝ አምናለሁ

ግን.....በርግጥ ፀፀት ኃጥያትን፣ አጥቦ ሚያነፃ ከሆነ እመነኝ ተፀፅቻለሁ፡፡

መድረግ የማትሻውን አርግ፣ቢያንስ እሳትህ ቀዝቀዝ ይላ፣ መጨረሻውባይረባህም፡፡

እሷ ግን ንጹና ናትና፣ ታስጨንቃትአይገባህም፡፡

ኪሊዎፓትራ፡- መቼስ ያፈቀረች ሴት ምናለ የማታደርገው !

ለዛ ለውድ ልብ ስትል ፣ የደስታዋ ምንጭ ለሆነው

ምን መላ በአለም ይኖራል ፣ አልቀበል የምትለው?

እና ባልንጀራህም ፣ እኔው ነኝ የገፋፋሁት

ነፍሱን የተጣጣለውን የፍቅር እሳት የለኮስኩት

ምናልባት ቅናት ቢይዘው፣ እናም መረብ ወጥመድ ሆኖኝ

ልመልስህ እችል መስሎኝ፡፡

የማስመለስን ጥበብግን፣ ቀድሞውኑ ስላልታደልኩ

በከንቱ ነበር የደከምኩ

አወይ የእጣ ፈንታ ሰወልጣን፣ መሆኑ ቀርቶ ያሰብኩት

ባንዲት ደቂቃ ማስመሰል፣ የህይወቴ ሙሉ እውነት፣ ፀጋ አመድ ሲሆን አየሁት፣

አንቶኒ፡- ከሸረሪት ድር ሚሰራ

ውትፍትፍ የክህደት ሴራ!

ታዳኙ ወይ ሌላ ካየው

ማጥመዱ ድሮም ዘበት ነው፡፡

ዶላቤላ፡- ይቅር በላት ጓደኛህን

ኪሊዎፓትራ፡- ይቅር በለው

አንቶኒ፡- አንቺኛዋም ራስሽን፣ አንተኛውም ራስህን

ጥፋት እንደሌለባችሁ፣ በደንብ ስላመናችሁ

አንደኛችሁ ላንደኛችሁ፣ ጥብቅና ትቆማላችሁ፡፡

የየራሳችሁን ወንጀል፣ እንዳልተፈጠረ አርጋችሁ!

ለመሆኑ- እኔን ከማስቀናትበላይ፣ ተንኮል እንዳልወጠናቹ

ምንድነው ምስክራችሁ?

ክሊዎፓትራ፡- እኛው እራሳችንና፣ አምላክ እንጂ ሌላስ የለም፡፡

አንቶኒ፡- አጥፊ ለጠፊ መመሳከር፣ ወትሮም አዲስ አይደለም፡፡

አዲዮስ- ከዚህ በኋላ ፍቅር እና ጓደኝነት

በሰው ልጆች ልቦና ውስጥ ቦታም የላቸው ስለውነት!

እኚህ ሁለት ዲያቢሎሶች፣ ነቅለው አባርረዋችኋል፣ ከተሴማችሁበት፡፡

ጥፊልኝ አሁን ከደጇ

ዶላቤላ፡- ፈጣሪ ለጥፋታችሁ፣ መቀጣጫ ይሁን ብሎ

አስቀድሞ ፈጥሮናል፣ ፀፀት ከምሬት ቀላቅሎ፡፡

እንዲያም ሆኖ ግን ዘወትር፣ ግብሩን ባንክሮ ካየነው

ኋጥአን በመማረሩ ነው፣ ግርማ ሞገሱ ሚያይለው

ለምህረቱ -መጀመሪያ መጨረሻም ገደብ የለው፡፡

ታዲያ ይህንን ቢያጤነው- ሰውን ሰውን ይቅር በለው፡፡

አንቶኒ፡- ገለል በሉልኝ አልክኮ! ይበቃኛል ከዚህ ወዲያ፣ የምሰማው ነገር የለም

አልሻም ዳግም ላያችሁ! ጥፉልኝ እስከዘላለም

ክሊዎፓትራ፡- እስከዘላለም? - እስከዘላለም ነው ያልከው?

ላንዲት አፍታ መለየቱን እንደማልጭል ልቤ ሲያውቀው

እንዴት ብዬ ነው ጌታዬ ፣ ዘላለም ካንተ ምርቀው?

ምን..... አነኝና የታባቴ ነው ምሄደው?

ወደራሴ ግዛት አልዞር- ላንተ ስል አጥቼዋለው

ወደሮማንያኔ አልሄድ- ባንተው ዳፋ ዐይኗን ላፈር፣ እንዳሉኝ በደንብ አውቃለሁ

ወይስ ስደተኛ ሄኜ፣ ያለረዳት አለሁልሽ ባይ፣ ዙሪያው ገደል እንደሆነብኝ

ሰፊውን አለም ብቻዬን፣ ልንከራተት ፈረድክብኝ?

አንተን አፈቀረች ብሎ፣ አለም አባሮኝ እያየህ

ዘላለም ከፊቱ፣ ራቂ ፣ ትላለህ በኔ ጨክነህ?

አንቶኒ፡- ባልሰማሽ ነው የሚሻለኝ

በውስጤ አንድ ጅል አለ፣ እመናት እመናት እሚለኝ፡፡

የክብር አምላክ እውነት ካለ ፣ እንግዲህ እሱ ይሁነኝ!

ክሊዎፓትራ፡- ርህራሄም አምላክ አለው፣ ስማኝ እባክህ!

ማንቋሸሽህን- ንቀትህን- ሁሉን ችሎ አጎብድዶ፣ የተከተለ ባሪያህን

ካገር ታባርረዋለህ፣ዘላለም ላያይ አይንህን

ትንሽ እናኳን አይራራ እኮ!- ሰው እንደዚህ ይጨክናል?

በቃ ሄደች እንኳ ቢባል

አንዲት ዘለላ እንባ ወይም ፣ አንዲት ደግ የስንብት ቃል

እንዳይወጣ ያስታውቃል

አረ ምን ድንጋይልቡ ነው!

ጭራሽ ወዶኝ ያውቅስ እንደሁ ፣ እንዴት ብዬ ነው የማምነው?

ብቻ ይር- እኔና- አንተን - ማርክ አንቶኒ- እኔና አንተን

አማልክት ዳኛ ይሁነን!

አንቶኒ፡- በቃበቃ! - ምን ያሻል አንካስላንቲያ?

ሚስጥረኛሽ ከሚባለው፣ ከገዛሽ አሌክሳስሽ ወዲያ?

ክሊዎፓትራ፡- ኤዲያ!

ዶላቤላ፡- እሱ ብሎ ምስክር -ይህ ቀጣፊእርያ

አንቶኒ፡- (**ለኪሎዎፓትራ**) ያንቺው አሌክሳስ እኮ ነው ! ምን ማለት ነው አዲያ ማለት?

ኪሊዎፓትራ፡- የራሱ መላቢስ ውጥን፣ ነበር እሱማ ቢልለት

ፍቅርን ይዞ ለማስቀረት

አስሮ ባቅናት ሰንሰለት፡፡

ምነው ጆሮዬን በዘጋው ፣ የሱን ምክር የሰማው ዕለት

ይህው እዚህ በቀምኩበት፣ ይጠራና ይስጥ ቃሉን

ማወቅ ካሻህትክክሉን.....

ግዴለም አስልክበት ይምጣና ይንገር ሁሉን

አንቶኒ፡- ነግሮኛል አልኩሽ - ነግሮኛል! አንድም ሳያስቀር ዝርዝሩን፡፡

ክሊዎፓትራ፡- መጥቶ የሚናገረው ቃል፣ እኔን ነፃ ካላወጣኝ-

አንቶኒ፡- እኮ! ውሻሽ መሆኑ መች ጠፋኝ!

ገፅሽን ብቻ በማየት

ለማለት ወይ ላለማለት

መመስከር መካድ መሸምጠጥ፣ የማይሳነው ቀጣፊ!

በዝች ፍንክች የማልል ነኝ፣ እንዲያው በከንቱ አትልፊ።።

ክሊዎፓትራ፡- የመለያየቱ ነገር፣ አልቀረልኝ ማለቱ ነው?

የፍርኃ ነገር ከሆነ፣ ይሁና እንግዲ ልቻለው

መቼስ የሰው ልጅ እድሉን፣ ከላዩ ቆርጦ ዕይጥለው።።

ልበ ደንዳናው ጌታዬን፣ ደህና ሁንልኝ እንግዲህ

ያላግባብ የጠፍ ስሜን፣ እንደያዝኩ እርቅሃለው፣ አይታየኝም ከዚህ ወዲያ።።

አንቶኒ፡- የፈጣሪ ያለህ! ወግ ነው ሲባል እሰማለው ፣ ሊለያዩ ሲሉ ማልቀስ

ይኖርብኝ ይሆን እንዴ ፣ እኔምነ ለወጉ እምባ ማፍሰስ?....

ካነባሁላቸውማ፣ ክሴ ሃሰት ሊመስል ነው

ወግቶ መላሱን፣ ፈርዶ ማልቀስ፣ ሁለቱም ትርጉም አይኖረው

ይቅር ማለቱ እንደማልችል፣ ባንድ በኩል ሲታሰበኝ

እንባዬን ማቀብ አቃተኝ።።

መሞታችሁን አልሻም! ስለዚህ ቆዩ በህይወት

ኑሯቹ ግን አሜኬላ ቆንጥር ጋሬጣ ይብዛበ!

ብርሃኔን እንዳጠፋችሁ

ለዝንትአለም ላይነጋ፣ ቀኑ ይጨልምባችሁ!

አርስ በእርስ ላትተያዩ፣ ተዋጡ በቀን ጨለማ፣

ተገናኙ የሚባል ወሬ፣ ፍፁም ጆሮዬ እንዳይሰማ!

በሁለታችሁ መሃከል

መለያያችሁ እንዲሆን፣ የብሱም ባህሩም ይወከል

ከዚች ካንዲ ፀሓይና፣ ከጥቁርሰማይ በስተቀር

በጋራ ማየት ትችሉት ፣ አይኑር ሌላ ምንም ነገር.....

በሉ አሁን በየፊናችሁ፣ መንገዳችሁን ጀምሩ

የየራሳቹን ክፉ ዕጣ፣ እድሜ ልክ አንጎራጉሩ።።

እናንተ ከድታችሁኛል

ሰው የሚባል እርጉም አውሬ፣ ከዚህ ወዲያ ይበቃኛል!

(ሁሉም በተለያየ አቅጣጫ ይወጣሉ)

ገቢር 5

(ክሊዎፓትራ፣ ቻርሚዎን አደራ)

ቻርሚዎን፡- ምናል የመንግስተ ሰማይ

ፍርዱ ሲገማደል ባናይ!

የዚህ ሁሉ ቀና ምግባር፣ ይህ ቅጣት ከሆነ ቤዛው

እድል ብቻ እንደሁነ፣ ይችን ዓለም የሚገዛው

ሰውም በራሱ እጅ እንደው፣ እጣዎቹን የሚዘግነው

ለማመን ልንገደድ ነው።።

ክሊዎፓትራ፡- ማርከው ያመጡትን ልቡን፣ ማቆየት ካልተቻላቸው

ዐይኖቼስ ምን ዋጋ አላቸው?

ምንቅል አድርጌ አውጥቼ፣ ምነው ሜዳ በጣልኳቸው!

አቤት የመውደድ እርግማን

እንኳንስ ለሰው ልጅና ይበዛበታል ለሰይጣን።።

እንግዲህ እናንት አማልክት- ኃያል እዝነ ልቦናችሁ፣ ቋሚ ምስክር ይሁነኝ!

አዳምጣችሁትም የለ ፣ ጥፊልኝ ከፊቴ ሲለኝ?

ታዲያ ይሄን ችዬ መኖር፣ እንዴት አርጎ ነው እሚቻለኝ?

መሞቱ እንጂ የሚሻለኝ! --በቃኝ በቃኝ--

(ራሷን ለመውጋት ጊሌዋን ትመዛለች። ቀልጠፍ ብለው ይይዟታል)

እጅንስ እሺ ያዛችሁ

እስትንፋሴን ባቅበውስ፣ ምን ማድረግ ትችላላችሁ?

መተንፈሴን አቆምና፣ ወደ ውስጥ መሞት እችላለሁ

ይህ የተረገመ ፍቅር፣ ውስጤ አንቂ እገድለዋለሁ!

(አሌክሳስ ይገባል)

አይራ፡- አረ አሌክስ እባክህ እርዳን ?

ንግስቲቱ ብሶባታል፣ ምናደርገው እኮ ጠፋን።።

ክሊዎፓትራ፡- ልቀቁኝ እባካቹ አንዴ!

ደግሞ ፊቴ ትቆማለህ፣ አንተ እርኩስ መሰሪ ዳንዴ!

ምናለ ብትለቁኝ ብይዘው፣ እናንተም ያውናቹ እንዴ?

ልቀቁኝ እኮ ነው ምለው! - አንገቱን ልበጥስለት፣ እና ተንፈስ ይበል ሆዴ!

አሌክሳስ፡- ይገባኛል እንደውነቱ

ቃሌም ምግባሬም ነውና፣ ያለ ጊዜው ያለ ወቅቱ፡፡

ግን እስቲበ እናውራ ስለዕውነቱ

አንዴ መውደቅ የጀመረ፤ ታላቅነት ግርማዊነት

በኔ አይነቱደካማ ሰው፣ተደግፎ ነው ባለበት መቆምስ የነበረበት?

ይሄ ግዙፍ እንከናቹ፣ በላዬ እንዲናድብኝ

ላልጠቅመው ስሩ ገብቼ፣ አመድ መሆን ነበረብኝ?

ምነው ንግስት ምን ሆንሽብኝ?.....

የገዛ ታላቅነቱን፣ በገዛ እጁ እጥፍ እጥፍ የሚል አባዜ ካደለው

የኔ አይነቱ ታዛኝ ሉሌ፣ ከመውደቅ ላድንህ ቢለው

እንደው ከንቱ ድካምእንጂ፣ በጭራሽ በጅም አይለው፡፡

እና ንግስት ሆይ እባክሽ፣ ባትፈርጂብኝ ነው ሚሻለው

የሉሌም እኮ ጡር አለው፡፡

ክሊዎፓትራ፡- አሃ.....! ጭራሽ ከደሙ ንፁኅ ነኝ፣ የማለት ድፍረቱም አለህ?

እንዴት አይነቱን ህለና፣ ይሆን አንተስ ያደለህ፤

ግልፅና ቀፅተኛውን፣ ተንኮል አልባውን ንፁኅ ፍቅሬን፣ ሁሉን ለኔ ተይው ብለህ

ወደ ተጠማዘዘ፣ ጠማማ የቅናት መንገድ፣ የመራህ አንተም አይደለህ?

አየኸው መጨረሻውን? ያንተን ዕቅድ ያንተን ስራ?

ኦክታቪያም ብትገለል፣ ምን አገኘች ክሊዎፓትራ?

ካገር ተባረረች እንጂ፣ ዳግም ላታይ አይኑን ዞራ

አሌክሳስ፡- ጀልባውን ማዕበል አንክቶት፣ዳር የወጣ የባህር ሰው

የባህሩን ጠረፍ ቋጥኝ፣ ሷጥጦ ወደላይ ለመውጣት፣ ጉልበቱም ትንፈፍሹም ቢያጥረው

እና አንድ በጎ አድራጊ፣ ለራሱ ህይወት ሳይሰጋ

ሊጎትትና ሊያወጣው፣ ካፋፍ እጁን ቢዘረጋ

ልታድነኝ ሞከርክ ብሎ፣ ሊረግምና ሊኮንነው

ያንቺንም እኮ እንደዚያው ነው።

አንዲት እርምጃ ሲቀርሽ፣ ባይበላሽ ኖሮ ነገር

ከአፋፍ እኮ ደርሰሽ ነበር።

ክሊዎፓትራ፡- እኔን ከአፋፍ ያርገኝ እቴ-

ሂድ ነውኮ ምልህ ከፊቴ!

አሌክሳስ፡- ስሚኝ ባክሽ እመቤቴ -

የኦክታቪያን መሄድና ፣ የደላብላን መባረር ፣ ልብ ብለን ካስተዋልነው

ግዴለም እመኚኝ ማዳም ፣ አሁንም ቢሆን አንቶኒ ፣ ያንቺው መሆኑ ግልፅ ነው።

ልቡም የራቀሽ ሚመስለው

የፍቅር ማፈግፈጊያ ፣ መደበቂያ ዱር ከሆነው

ከቅናት አምባ መሸጎ ፣ ለጊዜው ተጠልሎ ነው።

እመቤቴ- ይህን ጉዳይ ፣ እንኳን እኔና ማንም ሰው

የውጥኔን መስመር ይዞ ፣ ከታሰበው ግብ ሊያደርሰው

እንዳይመስልሽ የሚያቅጠው።

ያለቀ ነገር እኮ ነው!

የመጨረሻ ዕድል ስጪኝ - እና እኔው ልፈጽመው።

ክሊዎፓትራ፡- ፍቅሬን ገደል እንደከተትክ

ገደል ገብተህ ማውጣት ከቻልክ

አንዴ ሞክር ምን ቸገረኝ

ፍቅሬ ጠፍቶ ከቀረ ግን - አንድ አምላክ አይለመነኝ ነ

ፍስህን የምወስድ ነኝ!

አሌክሳስ፡- ያልኩትን ማድረግ ካቃተኝ - ለቅጣትሽ ዝግጁ ነኝ።

ይልቅስ አምላክ ላንቶኒ ፣ ሃያል ድጋፉን በሰጠው።

የቂስርን ጦር መርከቦች ፣ ለመፋለም ተዘጋጅተው

ያሉ መርከቦቻችንን ፣ ከፋሮ ማማ ላይ ቆሞ ፣ በመቃኘት ላይ ነው ያለው።

ከዚህ ወዲያ የሚሆነው

መሞት ወይም ማሸነፍ ነው።

ፍርጃችን ያው ሞት ከሆነ - የዕጣፈንታ ውል ነውና ፣ ቃሌም ቃልነቱን ይቅር

ድሉ የኛ ከሆነ ግን ፣ ባለድሉ ሰው ያንቺው ነው፣ እመኚኝ ያለጥርጥር።

(ከርቀት ጫጫታ ይሰማል)

ቻርሚዎን፡- ግዴለሽም ማዳም አይዞሽ ፣ አልቀርም መሰል ሳይቀናሽ

ጫጫታውም ነገር አይሰማሽ ?

(እንደገና ቀረብ ጠሚል ጫጫታ)

አይራ፡- ይኸው አሁንም አድምጡት

ሁካታውን አቀለጡት!

አሌክሳስ፡- ከወደ ወደቡ ይመስላል

ከድምፁ ጉላት ቅርበቱን ፣ ግምት ለመውሰድ ይቻላል።

ተመስገን! አስደሳች ዜና ፣ አምላክ ሊያሰማን ይሆናል ።

ክሊዎፓትራ፡- ቅዱስ ኡሳይረስ አደራ!

አውጣኝ ከዚህ ከመከራ!

ሴራጲዮን፡- ንግስቲቱ? ንግስቲቱ የት ናት ?

አሌክስ፡- ይሄ ቤከን ቶርቷራ ቁስ ፣ ምን አገኘው ? የምን መዓት?

ትዛዙን የሰማ ይመስላል ፣ መድረሱን የፍርድ ሰዓት።

ሴራጲዮን፡- እግዚኦ ቁጣ ! እግዚኦ መዓት !

የፈራነው ሁሉ ሆነ ! እምዩ ግብጽ አለቀላት!

የዓለም ስልጣንኬ ንግስት፣ ግብጽ ሞታ ተቀብራለች

ዝንተ ዓለም አትነሳም ፣ ስሟ ከእንግዲ አይጠራም ፣ በቃ እንጦሮጦስ ወርዳለች።

ግዜ እንደ ጥልቅ መጫኛ ፣ ተተርትሮ አለቀባት

የግብጽ አልፋ ኦሜጋዋ ፣መዝገቧን ደመደመባት!

እግዚኦ ምጽዓት!

ክሊዎፓትራ፡- ምንድነው ምትቀባጥረው ?

ወደ ቀጥተኛው መልዕክት ፣ ነገርህን አሳጥረው !

ኬት ነው አሁን የመጣኸው !

ለነገሩ- ፊትህ ላይ ፣ በግልጽ እንደ ሚነበበው

ይዘህ የመጣኸው ወሬ ፣ የጤና እንዳይሆን ግልጽ ነው።

ሴራፂዮን፡- ከፋሮ ነው የምመጣው

አይ ዘንድሮ የኛስ ጣጣ!

ከፋሮ አፋፍ ላይ ቁልቁል ፣ ውጊያውን ላይ ሄጀ ነበር

ምን ዋጋ አለው - አይቼ መጣው ፣ ፍጹም ያልጠበቁት ነገር።

የመጨረሻ ተስፋችን ፣ ከባሕር አይልሽ አልነበር ፣ ሙሉ በሙሉ ያረፈው?

ክሊዎፓትራ፡- እና ምነው?- ተሸነፈ ?

ሴራፂዮን፡- ኧረ በፍጹም !

የባሕር ወታደሮች፣ ከናካቴው አልተዋጉም።

ክሊዎፓትራ፡- ታዲያ ሸሹ ልትለኝ ነው?

ሴራፂዮን፡- እንደየሱስ በሆነ ምነው !

አይቼ የመጣውት ነገር ፣ አይደለም ጆሮሽ የሚያምነው ።

ከፋሮ ጫፍ ከማማው ላይ

ከአንቶኒ ጋር ቆመን ሳለን ፣ ሚሆነውን ሁሉ ልናይ

የባህር ኃይልሽ መመኪያ ፣ የሆነው ትላቁ መርከብ

እየከዘፈ ተስቦ ፣ ነቅቆ ከቆመበት ወደብ

ጠላት ወደሰፈረበት ፣ አቅጣጫውን እንዳቀና

ዋናው አዛዦ ብቅ ብሎ ፣ አንዳች ነገር ላይ ወጣና

እጆቹን ከፍ በማድረግ ፣ ሶስት ጊዜ አወዛውዞ፣ ምልክቱን ቢያሳያቸው

ወታደሮችሽ በስሜት ፣ ሶስቴ ጮኸው መለሱለት፣ ባለ በሌለ ድምጻቸው።

ወዲያውኑ መርከቦችሽ፣ ከየቆሙበት ዳርቻ ፣ በአዛዦ እየተመሩ

ወደ ጠላት ጦር አቅጣጫ ፣ እንቅስቃሴ ጀመሩ።።

ጥቂትም እንደቀዘፉ ፣ ለመገናኘት ከጠላት

እየቀረበ ሲመጣ ፣ ያ አስፈሪ የጣዕር ሰዓት

ድንገት እዚያው ዕሁን ሆነ ፣ ለግብጽ የቀረደው መዓት።።

ጦርነት መሆኑ ቀርቶ ፣ መተራረድ መገዳደል

እንግዳ ሥርዓት ታየ ፣ የወዳጅ ዘመድ አቀባበል ።።

ንገሪኝ ካልሽ ባጭሩ-

የኛም የነሱም ጦረኞች ፣ መለዩላቸውን አውልቀው ፣ ሽቅብ ማሽቀንጠር ጀመሩ

ወዲያውም የኛ መርከቦች ፣ በነሱ ጦር መሐል አልፈው

ከሮማውያን ጀርባ ቆሙ ፣ በሥርዓት ተሰልፈው ።።

አሁን ታዲያ - ሁለቱም ጦር፣ ተቀላቅለው አንድ ሆነው

ወደዚህ እየመጡ ነው።።

ክሊዎፓትራ፡- ሴራጲዮን - ይበቃል

ምጽዓቴን ነግረኸኛል።።

ጌታዬ አሁን የት ነው ያለው?

ይህንስ ዱብዳ መብረቅ ፣ በምን መልኩ ተቀበለው?

ሴራጲዮን፡- ቁጣው ፣ እልሁ ፣ እብደቱ ፣ አይደለም መግለጽ የሚቻል

ሚሠራውን አያውቀውም ፣ አካሉ ትንታግ ይረጫል!

ካንድም ሁለት ሶስት ጊዜ ፣ ከማማው ቁልቁል ለመዝለል

እና ከጠላት መርከብ ላይ ፣ ወርዶ ባናቱ ሊተከል

ባለ ጉልበቱ ሲታገል

የኛ ሰዎች ቢያስቀሩትም ፣ እጅ እግሩን ግጥም አድርገው

አፉ ባረፉ ተሞልቶ ፣ አንቺን እየረገመ ነው

ያንቺ ተንኮል ነው የመሰለው

እና አሁን ከመጣና ፣ ካገኘሽ እንዲህ ቆመሽ ሳል

አልክሳስ፡- ብትደበቂ ይሻላል - ሴጣኑ እስኪያልፍ ዘወር ብትይ

ንጽእናሽን በቅጡ ፣ ማስመስከር እስከምትችይ።።

ክሊዎፓትራ፡- ይምጣ ያግኘኝ - አልሸሽም!

አሌክሳስ፡- እንደሱማ ተይ አይሆንም ።።

ይልቅ ፍጠኚና ሄደሽ ፣ ሐውልትሽ ውስጥ ተደበቂ

ቁስር ዘንድ ሄጂ እስክመጣ፣ እዚያ ሁኚና ጠብቂ።።

ክሊዎፓትራ፡- ‹‹ ቁሳር ››? - ከቁሳር ጉዳይ የለኝም!

አሌክሳስ፡- ለምን እሺ አትይኝም ?

ይህን እብድ እንዲያጠፋልሽ - እና አንቺንም እንዲያምርሽ

በሚገባ ላሳምነው ፣ የሚያቅተኝ እንዳይመስልሽ።።

ክሊዎፓትራ፡- አንተ ውሻ ልክስክስ ፍጡር ! በቁም የበከትክ ወራዳ !

አንተም ሰው ሆነህ ቀን አይተህ ፣ ጀግናው ጌታዬን ትከዳ ?

አሁን ሌላ ሳይከተልህ ፣ ድራሽህ ይጥፋ ከፊቴ !

ድምጽህን መስማት አልሻም ፣ ተሟጦ አልቋል ትዕግስቴ።።

አንተው በተበተብከው ነው

ለዚህ ሁሉ የበቃነው።።

ሴራጲዮን እባክህን - አንተ መቼም ታማኝ ሰው ነህ

እስቲ ምክርህን ስጠኝ ፣ ምን አድርዲ ትለኛለህ ?

ፈጠን በልና ንገረኝ የማሰቢያ ጊዜም የለኝ።።

ሴራጲዮን፡- ገለል ብትይ ነው የሚሻል

አሁን ለጊዜው አንቶኒ ፣ ባያገኝሽ ይበጅሻል።።

ይህን ተንኮል ከበፊቱ ፣ ሀ ብሎ እንደጀመረው

የመጣውንም አደጋ ፣ እሱ ራሱ ይሞክረው።።

ለተፈጠረው ሁኔታ ፣ አንቺም እንግዳ መሆንሽን

እዚሁ ይጠብቅና ፣ ያስረዳው ንጽሕናሽን ።።

በምላሱ ተማምኖ አይደል ፣ ከቁሳር ቅጣት ነፍስሽን ፣ ማዳን እችላለሁ ያለ ?

ታዲያ ይህን ችሎታውን ያንቶኒን እስት ለማብረድ፣ ይጠቀመዋ ምናለ።።

አሌክሳስ፡- ኧረ የፈጣሪ ያለህ ! ይሄንንስ እኔ አልደፍርም

በዚማ መሞቴ አይቀርም !

ክሊዎፓትራ፡- ላንተ ሞት አይበዛብህም !

ይገድለኛል ብዬ አይደለም ፣ ከጌታዬ ምደበቀው

የጨዋ ጣሪያ መሆኑን ፣ ጥሩ አድርጌ ነው የማውቀው፡፡

የጠረጠረኝ ጊዜ እንኳን ፣ እኔን ካገር ያባረረው

የሴት ልጅ ነፍስ በእጁ ማጥፋት፣ ውርደት መስሎ ቢታየው ነው፡፡

እና አሁንም ቢመጣ፣ እንደማይገድለኝ አውቃለሁ

ቢሆንም ንፁህ መሆኔን፣ ከኔው ባይሰማ እመርጣለሁ፡፡

ስለዚህ - ጠብቀው እና፣ በምታውቀው ቋንቋ ሁሉ፣ እንዳልከዳሁት ንገረው

እንጂ ከዚያ በኋላማ፣ አብሬው ነው የምሞተው፡፡

አሌክሳስ፡- እባክሽ እዘኚልኝ

የዛሬን እለፊኝና፣ ልከተልሽ ፍቀጅልኝ

ክሊዎፓትራ፡- ከዚች ቦታ ንቅንቅ ብትል

ሬሳህን ነው ማስከትል!

ይልቅ ዘርዝረህ አስረዳው፣ የሆነውን በትክክል

ለኔ እንኳ ግድ ባይኖርህ - ምድር ለምድር እየተሳብክ፣ አፈር እየላስክ እንድትል

እስከዛሬ ላቆየሃት፣ ለዚች ኮሾ ነፍስ ስትል፡፡

ሁን ያለውን መቼም አይቀር፣ እና ሚሆነው እስኪሆን

ና እስቲ እንውጣ ሴራጲዮን፡፡

(ክሊዎፓትራ፣ ሴራጲዮን፣ ቻርሚዮን እና አይራ ይወጣሉ)

አሌክሳስ፡- በእውነትም እጅግ ይገርማል!

ይህን ኑሮ ኑሮ ብዬ፣ እንዳላጣው ይህን ያህል፣ መጨነቄ ምን ይባላል?

የኔ ኑሮ - የኔ ህይወት -

ልጆች የሚያድጦለቡሉት፣ ልክ የበረዶ ኳስ አይነት

በኒህ ሰፍሳፋ እጆቼ፣ አጥብቄ በያዝኩት ቁጥር

ለምን ይሆን የሞት ሞቴ፣ ይገፍ ላቆየው የምጥር?

አይ አይምሮ ብሎ ነገር!

ጥንቱም ከሰው ጋር ሲፈጠር

ክፉና ደጉን መለያ፣ ማመዘኛም አልነበር?

ለምንድነው አንድአንድ ግዜ፣ እንደከፋ ባልንጀራ፣ አደጋ ጥሎ ሚበር?

እኒህ ፍቅረኛሞች እንኳ፣ ሁለቱም በየፊናቸው

ከጠፈር በታች ያለውን፣ ሁሉን ማስገበር የሚችል፣ ግዙፍ አይምሮ እያላቸው

የማይቀር መሆኑን ሲያውቁት ደርሶ መለያየታቸው

ለምን ይሆን መጨነቁ፣ እንዲህ ነፍስና ስጋቸው? . . .

ይልቅ አሁን ላስብ እስቲ - ምን ማለት ይሆን የምችል

ይቺን ነፍሴን ለማዳን ስል?

ካሁኑ ሞት አፍ ለማምለጥ፣ ምችልበት መላ ባገኝ

የክሊዎፓትራ መጨረሻ፣ እምብዛም አያስጨንቀኝ።

አንቶኒ፡- **(ከውስጥ)** የትኛው ነው መንገዳችን? በዚህ ነው በዚህ ምንሄደው?

ቢንቲዬሞስ፡- **(ከውስጥ)** እንደሚመስለኝ - ይሄኛው፣ ወደ ሃውልቱ ነው ሚወስደኝ።

አሌክሳስ፡- ጉድ ፈላ! - የሱ ድምፅ ነው ሚሰማኝ

ሳልዘጋጅ መያዜ ነው፣ ምን ይሻላል? ግራ ገባኝ።

የቆርጣ መቀጠል ጥበብ፣ እንደልጂስ አሳድጌው፣ ምነው በዚች ሰአት ከዳኝ?

ቆሜ መጠበቅ አልደፍርም-

ከዚህ መራቅ ባልችል እንኳ፣ ብደበቅ ሳይሻል አይቀርም።**(ይወጣል)**

(አንቶኒ እና ቤንቲዬሞስ ይገባሉ)

ቤንቲዬሞስ፡- እየው ይሄንን ሾተላይ!

ተመልከታት ክሊዎፓትራን፣ ታትማበት ግንባሩ ላይ!

እግዚኦ ፊቴን ምነኛ፣ ለቅጥፈት አዘጋጅቶታል!

አፍ አውጥቶ ሊዘረግፍ፣ ካረገዘ ውስጥ አንድም ቃል!

(ሰይፍን እየመዘዘ) መጀመሪያ እሱ ይሙት፣ የሌሎች ይቀጥላል።

አሌክሳስ፡- አዬ ጉዴ - ባክህ ተወኝ፣ እባክህ ጌታዬ ተወኝ!

አንቶኒ፡- ተወው እስቲ ቆይ ግድ የለም!

ይህንን ልክስክስ ብትገል፣ ለራስህ ክብር ደግ አደለም፡፡

(ለአሌክሳስ) ተጠንቀቅ ግን አንተ ቆሻሻ!

የዚያች ንግስትህን ጉድ፣ እሸፋፍናለሁ ብለህ

አንዲት ቃል ካፍህ ብትወጣ፣ ሰይጣኔን ታመጣዋለህ!

አሌክሳስ፡- ጌታዬ እሷስ የለችም - ሄዳለች ከዚህ እርቃ

ከእንግዲህ አንተም ሆንክ ፍቅር፣ በንትርክ በጭቅጭቅ፣ አታቃጥሏትም በቃ

አንቶኒ፡- ዶላቤላ ዋጋ ነዋ፣ የሸሸችው መች አጣኋት!

አልገድልህም ብዬ ነበር፣ አሁን ቃሌን አነሳሁት

አንተ ቀጣፊ! በቃ ሙት!

(ሊገድለው ይጠጋል)

አሌክሳስ፡- ኧረ እስቲ ቆይ አንድ ግዜ - እሷ ወዴትም አልሸሸች፡፡

አንቶኒ፡- ሸሽታለች! - ሸሽታለች፡፡

በግልጽ ይታየኝ ጀምሯል፣ አታላይ እንደነበረች፡፡

የሸንገላ ዝማሬዋን፣ ጠዋት ጠዋት ለኔ እንዳልዘመረች

አሁን ክረምቱ ሲገባ፣ ክንፏን ዘርግታ በረረች

በሃምሌ ጭለማ ጥላኝ፣ ወደ ቄሳር ፀደይ ሄደች፡፡

ሰው አይደለችም! አውሬ ነች!

አሌክሳስ፡- እንደሱ አታስብ ባክህ ተው

በሁሉም ነገር እድሏ፣ የተቆራኘ ነው ካንተው፡፡

አስከድታ ቢሆንማ፣ የባህር ሃይሏን ወደ ሮም፣ አንተ እንደጠረጠርካት

በርግጥ ወደቄሳር መሄድ፣ እንዴት ቀላል በሆነላት

ይህን ጉቦ ቢያገኝ ቄሳር፣ ምነኛ በተቀበላት!

ቤንቲዴዎስ፡- የአቀባበሏ ስርዓት፣ እንዲደምቅላት በማለት

ነው ጦሯን ያስቀደመችው፣ በገፀ- በረከትነት፡፡

አንቶኒ፡- ያማ ምን ያጠራጥራል!

ከደሙ ንፁህ ነኝ ካለች ኖራ በማስረዳት ፈንታ፣ መሰወሯ ምን ይባላል?

አሌክሳስ፡- ኖራ ባስረዳችህ እንጂ፣ ማስረዳቷማ መች ቀረ

ካፏ አንኳን ቃላት ባይወጡም፣ ዐይኗ ላይ ያለውን እውነት፣ አንተው ታይላት ነበረ፡፡

ግን ጥርጣሬህን ሰምታ፣ ከዳችኝ ብለህ ማለትህን

ማፈራረስህን ስታውቀው፣ አይፍረስ ያለችው እምነትህን

የተለወጠ ነፍስህን፣ ፊት ለፊት ማየት ቢያስፈራት

ከእስከሁኑ ምፅት ሁሉ፣ ያሁኑ ካቅሟ በላይ፣ ሆኖ መሸከም ቢሳናት

ከገዛ ሃውልቷ ገብታ፣ ገለለችና ራሷን

በሃዘን መናጥ ጀመረች፣ እንደጥንቅሽ ደፍታ አንገቷን፡፡

ፊቷ ቅጭም እንኳ ሳይል፣ ቁልቁል መሬት መሬት ስታይ

እንባዎቿ በሷ ሳይሆን፣ በራሳቸው ፍቃድ ወተው፣ ሲወርዱ በጉንጮቿ ላይ

በድኑ ሃውልቷ መስላ ፈዝዛ ቆየችና ጥቂት

ወዲያው አይኖቿን ቀና አርጋ፣ አንች ነገር ውል እንዳለው፣ ተከለቻቸው ፊት ለፊት፡፡

ከዚያም - ድንገት ሳናስበው -

አንቶኒ፡- ቆይ እስቲ አንዴ አንተ ሰው - ነገርህ ወዴት ወዴት ነው?

አቅጣጫህ አላማረኝም ፣ ልቤን ቅፍፍ ቅፍፍ አለው፡፡

ቤንቲዴሞስ፡- መሆን ያለበትን ነገር፣ አደረገችው ነው ምትል?

መጨረሻውስ? በል ቀጥል!

አሌክሳስ፡- ብቻ ድንገት ሳናስበው፣ ባንችልበት ለማስጣል

ጊሌዋን በቅፅበት መዛ፣ ሰካችው ጡቶቿ መሃል፡፡

ከዚያ ዞራ እያየች -

"አሁኑኑ ፈጥነህ ሄደህ፣ የመለያ ስንብቴን፣ ለጌታዬ አድርስልኝ

አሁንም ታማኝነቴን፣ ይጠራጠር እንደሆነም፣ አደራህን ጠይቅልኝ"

ብላ ነገረችኝና - ሌላም ምትለው ነበራት-

ግን ሞት በመሃል ገባና፣ ሳትጨርሰው አቋረጣት፡፡

በመጨረሻም እስትንፋሷም ፣ ስምህን እንዴት ለመጥራት፣ በብርቱ ጥራ ነበረ

የስምህን ግማሽ ብቻ፣ ጠራችና ግማሹን ግን፣ ውስጧ ተቀብሮ ነው የቀረ፡፡

ቤንቲዴሞስ፡- ተመስገ . . .ን - የልቤ ሞላ

አንቶኒ፡- የኔ ምስኪን - የኔፍቅር - ፍፁም ኖረሻላ?

ንፁህ ሆነሽ ሞተሻላ?

እኔሳ ምንድነኝ?

ንፅህናን ከወነጀልኩ፣ እውነትን ከገደልኩ ወዲያ !

ቤንቲዴሞስ፡- መጨረሻዋን አሳየን

አንቶኒ፡- **(ለአሌክሳስ)** እኮ እዚህ ምን ገተረህ ?

የነፍሴን ውስጥ መረራ ስቃይ ቆመህ ምትሰልል አንተ ነህ?

መርዶህን ነገርክ ምንቀረህ

ሂድ አልኩህ እኮ! አይሰማህም?

ሮማዊው ንጉስ አሁን፣ የሚያደርገውን ቆመህ ማየት፣ ሚገባህ ሰው አይደለህም፡፡

አሌክሳስ፡- **(እየወጣ ጉምጉምታ)** ጎሽ አሁንም ይወዳታል!

ከሃኑ ከቁጭቱ፣ በግልፅ ያስታውቅበታል

ጥ. . . ሩ ነው!

ሞታለች ብሎ አምኖ ሳል፣ በህይወት መኖሯን ሲያውቀው

በደስታ ዚቅ ሲፈነጥዝ፣ እርቁ ያኔ ነው የሚያልቀው

እን . . . ዲያ ነው! - የራሴን ነፍስ ብቻ ሳይሆን የሷንም እኮ አዳንኩት!

ግን ከነዚህ ሮማውያን ሰይፍ፣ ለጥቂት ነው ያመለጥኩት

(ይወጣል)

ቤንቴዴሞስ፡- ምነው ትንሽ ቀደም ብላ፣ አክታቪያ ሳትሄድ በፊት፣ ሞት ቢሆን ሞታ ላይቀር!

መደራረደር ቢያሻህ እንኳን፣ ሁኔታው ያመች ነበር፡፡

አሁን ብልጠት ስለሚመስል፣ የባጣ ቆያኘረ ዘዴ አይነት

በቁሳር በኩል በሆን፣ አይኖረው ተቀባይነት፡፡

ስለዚህ ነቃ በልና፣ ያቅማችንን ያህል ታግለን

ጎን ለጎን እንሞታለን፡፡

አንቶኒ፡- ምታገለውም ነገር የለኝ፡፡

ምን የቀረኝ ነገር አለ፣ ከእንግዲ የሚያታግለኝ?

እልህ፣ ንዴት፣ ብስጭት ውስጥ፣ ምገባበትስ ምን አለኝ?

ቢኒቴዶዎስ በቃ ተወኝ!

ቤኒቲዶዎስ፡- ቁሳር በር ላይ ነው ያለው፡፡

አንቶኒ፡- ችግር የለም- ግባ በለው!

ከንግዲህ እግዳዬ ነው፡፡

ቢቴዶዎስ፡- ምነው መራራ ሃሞትህ

አሁን በአሁኑ ፈሰሰብህ?

አንቶኒ፡- ይህ ህይወት- ይህን መኖር- በቃ ናኩት-ተጠየፍኩት!

ከዚ አለም ኑሮ ትብታብ፣ መላቀቅ ነው የፈለኩት፡፡

ቤኒቴዲዎስ፡- እኮ በጀግና ወግ አርገው!

ባለፈው ያጠቁን ግዜ ካጨዱብን የተረፈን

ሶስት ጋንታ የሚሆን ጦር እዚህ ከተማ ውስጥ አለን

ውሳኔህ መሞት ከሆነ፣ እኔም በዚች ጠባብ ሰአት ሌላ ምኞት ስለሌለኝ

በጠላት ሬሳ ክምር ዙሪያችንን ለማሸብረቅ ሶስት ጋንታ አያንስም ባይ ነኝ፡፡

አንቶኒ፡- ልዋጋለት የሚገባኝ፣ ምንቀርቶኛል በዚች አለም?- ኪሎዎፓትራ ሞታ የለም?

ዝናዬም ክብሬም ሞገሴም፣ሁሉም የጣልኩለተ ነገር

ለሷ ፍቅር ስል አልነበር?

ቤንቲዶዎስ፡- እኮ ይሄ ሰው ይምጣና፣ ይያዘኝ ነው የምትለኝ?

አንቶኒ፡- አዎ ይምጣና ይያዘኝ!

ታዲያ- እንደሮማዊነቴ፣ቢይይዝ በድኔን ነው እነጂ፣ በቁሜ እንደሁ አያገኘኝ፡፡

ቤንቲዶዎስ፡- ማን ያውቃል

ሁሉን ጥሰናቸው አልፈን ያንተው ዕዝ ከሚገኝበት መድረስ ይቻለን ይሆናል፡፡

አንቶኒ፡- እኔ በቃ ሰልችቶኛል፣ መቅረዜ ችቦዬ ወድሟል፣ ብቻውን ይፈንጭ በላይዋ፡፡

ከፊት ለፊቴ የሚታየኝ፣ ድቅድቅ ጨለማ የዋጠው፣ በረሃ አለም በመሆኑ

ራሴን ላጋድመውና፣ በዚህ ይብቃኝ መባዘኑ።።

ቤንቲዴሞስ፡- ምንድነው የሆንከው አንተ ሰው?!

ያሁሉ ድካም ትግላችን፣ የታጋች ሞት ለመሞት ነው?

ኪሊዎፓትራ እንኳን አውቃበት፣ ከነክብሯ እኮ ነው የሞተች

ነው ወይስ ህሊናህንም፣አደንብሻው ነው የሄደች?...

አረ ባክህን ጌታዬ- አረ ለወሬም አይመች!

አንቶኒ፡- ቤኒቲዴሞስ..... ግዴለህም..... በማትለውጠው ጉዳይ ላይ፣ ጊዜ ማጥፋት አይረባህም

ቤንቲዴሞስ፡- እባክህ ተለመነኝ፣ ሌላው ቢቀር ለኔ ስትል

አንቶኒ፡- ምን ግዜም ምክንያት አለኝ፣ ስመዝም ሆነ ስገድል

ቤንቲዴሞስ፡- "ምክንያት"? . . .

ከነተግታግ ወላፈን፣ ለገለባው ሰደድ ሆነህ

ታሪክኛው ሰይፍህን፣ በጠላትህ ደም አስጊጠህ

ማደሪያውን አፎት ሳይሆን፣ ከመዳፍ መሃል አርገህ

ይቺን አለም መሰናበት፣ "ምክንያት" ይሆንም ባይ ነኝ?

እንቶኒ፡- ቤንቲዴሞስ አልገባህም . . .

ወትሮም ለመኖር እንጂ ለመሞት ገድዬ አላውቅም

ቤንቲዴሞስ፡- ይገርማል . . . ሰው እንዴት መቅኔው ከአጥነቱ፣ እንዲህ ድንገት ሙጥጥ ይላል?

አንቶኒ፡- ይላል ይላል . . . ሙጥጥ ጥፍፍ ጥፍፍ ይላል።።

ቤንቲዴሞስ፡- ኧረ ከየት አመጣኸው በል ፣ እንዲህ ያለውን መታከት

አንቶኒ፡- ውዱ መይሳው ወዳጄ፣ ብትረዳኝ ምን አለበት

ሰው ልቡ ከሞተ ዎዲያ፣ ምን ትርጉም አለው? . . .

ይልቅ ከንቱ አያዋዛህ፣ ከነ ህይወቱ እንዳታሲዘኝ

ግዜ የለም ቀልጠፍ ብለህ፣ አፈላፀሙን አግዘኝ

አይ ካልክም በራሴ፣ ልከውነው የምችል ነኝ።።

ቤንቲዴሞስ፡- አብሬ መሞቴ በጀኝ

እንጂ ሞተህ ምኖር ቢሆን፣ሃዘን ምነኛ በፈጀኝ

ግን ከመሞታችን በፊት በመረብ እንደተያዙ፣ ሁለት የጫካ አንበሶች

ብናተራምሳቸውስ፣ የከበቡንን አዳኞች?

አንቶኒ፡- ቤንቲዴሞስ - የኔን ሃሳብ ተቀበለኝ - አንተ መሞት የለብህም።

ቤንቲዴሞስ፡- ጌታዬ ይሄንን አልቀበልም

አንቶኒ፡- ስለኔ በጎ ለማውራት - ለኔ ስትል አትኖርም?

ከዘናዬ ጎን ዘብ ቆማ፣ ከሰዎች የሃሜት ጥቃት፣ ልታድነኝ አትፈልግም?

ቤንቲዴሞስ፡- ካንተ ጎላ ከኖርኩማ፣ እኔም ከሃሜት አልድንም

አንቶኒ፡- ትእዛዝ ነው! - እሺ በለኝ።

ቤንቲዴሞስ፡- ጌታዬ - አሚሚታችን ካማረ፣ በራሱ በቂ ነው ባይ ነኝ

ስለዚህ ሌላ ምስክር፣ ከቶ የሚሻ አይመስለኝም

አንቶኒ፡- አብረን ስንኖር ከልብህ፣ እንዳፈቀርከኝ አውቃለሁ

ለዚህ ፍቅርህ ውለታህን፣ ልከፍል እፈልጋለሁ።

መሞቴ እንዲሁ ስለማይቀር

በሰይፍ ግደለኝና፣ ጠላቴ የሆንክ በመምሰል፣ ከቁሳር ሰላምህን ፍጠር።

ቤንቲዴሞስ፡- ሃ ሃ ሃ! ሃ ሃ ሃ! - በጣም አመሰግናለሁ!

አፈቀርከኝ ባልክበት አፍ፣ ዞረህ ክዳኝ ትለኛለህ? - ጌታዬ እጅግ አዝናለሁ!

እኔ ነኝ አንተን ከድቼ

ምታረቅ ከጠላቶቼ?

እንዲህ ወራዳ ሰው አድርገህ፣ ነበር እንዴ የምትገምተኝ?

በመጨረሻ ደቂቃ፣ አዝኜብህ እንድሞት ነው፣ ይህን ነገር የነገርከኝ?

ጌታዬ - ውዴ ሰዓት ላይ፣ ምነው እንዲህ ጉድ አረከኝ፣

አንቶኒ፡- ይቅርታ! - አትዘንብኝ ፣ ሮማዊው አንበሳዬ

ከክሊዎፓትራ ሞት ወዲህ፣ ስለተነጣጠሉብኝ፣ ምላስና አይምሮዬ

ምናገረውን አላውቅም፣ ቀልቤ ተገፏል ከላዬ።

የተሻለ ሃሳብ አለኝ

አደራህን ይህን ደግሞ፣ አልቀበልም እንዳተል፡፡

ቤንቲዴሞስ፡- ምንም ይሁን - ታዛዥሀ ነኝ፡፡

ብቻ አንተ ከሞትክ ወዲህ፣ እንድኖር አትጠይቀኝ!

አንቶኒ፡- ምን መሰለህ - መጀመሪያ እኔን ገድለህ

ከዚያ ራስህ ትሞታለህ

ለወዳጅህ ቅድሚያ መስጠት ፣ አግባብ እንደሆነ ታውቃለህ፡፡

ቤኒቲዴሞስ፡- ድህና- ቀኝ እጅህን ስጠኝ፡፡

እዚያው እንገናኛለን፣ ምንም ያህል አትቅደመኝ፡፡

እስከዚያውም ድረስ ቢሆን፣ ንጉስ ሆይበ ተሰናበተኝ

‹ **(ይተቃቀፋሉ)**

ንጉስ ሆይ ነው ያልኩህ እንዴ

በመለያያችን ሰአት፣ይህንን አይነት የባዳ አጠራር፣ ደስም አላለኝ

ሞት አፈራፍ ላይ ስርአት የለም፣ በል ደህና ሁንልኝ ጓዴ!

(እንደገና ይተቃቀፋሉ)

እንግዲህ ጨረስን መሰለኝ

መሆኑ ማይቀር ነገር ላይ፣ አላዋዛም ቆፍጣና ነኝ፡፡

ሆኖም አይንህን እያየሁ፣ ልወጋህ ስለማይቻለኝ

ዙርና ጀርባህን ስጠኝ፡፡

አንቶኒ፡- እሆናለሁ እንዳዘዝከኝ፡፡

(ፊቱን አዙሮ ጀርባውን ይሰጠዋል)

ታዲያ ተጠንቅቀህ ሰንዝር፣ አረጋግጠህ ብልት

አደራህን እንዳትስት!

ቤኒቲዴሞስ፡- ግዴለም ስጋት አይግባህ

በሚቻለኝ ሃይል ሰንዝሬ፣ ድህና አድርጌ ነው ምወጋህ!

(የአንቶኒን ትከሻ የሚወጋ አስመስሎ ይቆይና እራሱን በራሱ ይወጋል)

አንቶኒ፡- አአ!- ተሳሳትክ ታወቀኝ!

ቃል ገብተህም አልነበር፣ እሱን ሞት ለኔ ልትሰጠኝ?

ምነዋ ሞቴን ነጠከኝ?

ቤኒቲዬሞስ- አታለልከኝ!

ቤኒቲዬሞስ፡- **(በወደቀበት)** አታልዬሃለሁ በእውነቱ

ግን- ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ነውና ያሳደልኩት እምነት

በዚች ባንዲቷ ጥፋቴ፣ የቱን ያህል ባሳዝንህ

ይቅርታህን እንዳትነፍገኝ- ከልቤ ነው ምለምንህ፡፡

(ይሞታል)

አንቶኒ፡- በል እንግዲህ- ድህና ሁና!

ሞት ላይ እንኳን ከፊቴ ነህ፣ የኔ መሪ- የኔ ጀግና!

አንተንና የኔዋን ንግስት- ከኔ ጋር ይቆይ ክብራችሁ

ክብሬን ይዛቹ ሄዳቹ

ከምኔው ተሰናበተ?- በቃ ሞት ማለት ይኸው ነው?

ለነገሩ- ከዚህ ወዲያ- ምንድነው እኔን የሚያስጨንቀኝ?

መሞት ማለት ማሰብ ማቆም፣ እንደሆነ እየታወቀኝ

እንደ.... ዚህ! ማድረግ ሲቻለኝ!

(እራሱን ይወጋል፡፡ በዝግታ ይወድቃል)

አይ ክፉ እድል፣ ልቤን ሳትኩት!

በዚህ በማይረባ እጅ ነው፣ ሳር ቅጠሉን ያስገብርኩት?

እጅ የማክዳ እንኳ ቢሆን፣ ምነው በዚህ ሰአት ከዳኝ?

ወይም- ሞትም ከድሌ ጋር፣ አድሞ ፊት ሊነሳኝ ነው፣ በሩ ላይ ደጅ የሚያስጠናኝ?

(ከውስጥ የሰዎች ዱካና ግርግር ይሰማል)

ቄሳር ደረሰ መሰለኝ

አሁን እንዲህ ባለሁበት፣ ከነሂወቴ ያገኘኝ

አውቃለሁ ምን እንደሚለኝ፡፡

ደርሶ ሳይዚኝ ቀድሜ፣ ያበላሽሁትን ስራ፣ ባስተካክል ነው ሚሻለኝ፡፡

(ቀና ብሎ በርከክ ለማለት ሲጣጣር ክሊዎፓርራ፣ ቻርሚዎንና አይራ ይገባሉ)

ክሊዎፓትራ፡- አልቀረማ የፈራሁት!

ምነው ቀድሜ ብነሳ?- ምነው ቀድሜ ብነሳ?

ሰራልኝ ያ እርጉም አሌክሳስ!

(ወደ አንቶኒ በመሮጥ ትጠገዋለች)

አንቶኒ፡- አሃ- እንዴት እንዴት ነው

በህይወት አለሽ ማለት ነው?

ወይስ- ሳይታወቀኝ ሞቼ፣ መንፈሴ ሰማይ ቤት መጥቶ፣ መንፈስሽን ይሆን የማየው?

ክሊዎፓትራ፡- **(ለነቻርሚዎን)** ኑ አስቲ እርዱኝ! ቀና እናርገው

ፍጠኑ! እርዳታ ጥሩልኝ!

አረ ምንድነው ሚሻለው?- እስቲ ጎኑን ደግፍልኝ!

(ደጋግፈው በማንሳት መከዳ ላይ ያስቀምጡታል)

አንቶኒ፡- ሁለታችንም አልሞትንም- አሥ- አሁን- ግልፅ የሆነልኝ

ነይ እስቲ- ክሊዎፓትራዬ- አጠገቤ- ቁጭ በይልኝ፡፡

በህይወት- የምቆይባት-ግዜ እንዳለቀች አውቃለሁ

ግን- ከሞት ጋር ተናንቄ- ላፍታ እንኳን ቢሆን- ካንቺ ጋር- ለመቆየት እጥራለሁ

ክሊዎፓትራ፡- ጌታዬ ምንድነው ጉዱ?

ሚግተለተልብን ቁጣ፣ ተደራርቦ አንዱ ባንዱ?

አንቶኒ፡- ሚኮበልል ሰው- ታቀወቂ የለ

ጓዙን ጠቅልሎ- በፍጥነት፣ ይችን አለም- ጥሎ ሲበር፣ ፋታ ያጣ የቸኮለ?

ነገር ግን ውል ሲልበት፣ መንገዱ፣ ጀምሮ ሳለ

እጅግ የሚያሻው- ውድ እቃ፣ ትቶት የወጣው እንዳለ

እደሚመለሰው ሁሉ፣ለመፈለግ- ያንን እቃ

ላንቺ ነበር የተመለስኩ፣ ለመጓዝ አልቻል ቢላት ነፍሴ ከነፍስሽ እርቃ፡፡

ክሊዎፓትራ፡- እናንተ አማልክት አድምጡኝ!

እስካሁኑም ጭካኔያቹ፣ ካቅሜ በላይ ነበር እና፣ ይበቃል አትቀጥቅጡኝ!

እባካቹ ማሩኝ እና፣ ነፍሱን መልሳቹ ስጡኝ!

አንቶኒ፡- በቃ ፍቅሬ- የኔማ ነፍስ፣ ከእግዲህ አትመለስ

በትግል- በሃይል ይገፍ ነው፣ ያቆየኋት እስካሁንም፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ንፁ አፍቃሪ ነበርኩኝ፣ ብዬ ለማስረዳት አሁን፣ ጊዜም የለን እንተወው

የፍቅሬን ልክ ለማሳየት፣ የቀረኝ አንድ መንገድ ነው

የምለቅህ እንዳይመስልህ፣አብሬ ነው የምሞተው፡፡.....

አንቶኒ፡- የ -ዶላቤላ- ሽስ- ነገር

ክሊዎፓትራ፡- ምንም ነገር አልነበረም - ከናንተ ውንጀላ በቀር፡፡

አንቶኒ፡- እፎ . . .ይ! ይበቃኛል፡፡

ከዚህ በላይ - ለመቆየት፣ አይቻለኝም -ይበቃኛል፡፡

"ተከትዬህ - እመጣለሁ" - ብለሽ የለ? - አምንሻለሁ

ምክንያቱም - በዚች ሰዓት ምትይኝን ከልብ እቀበልሻለሁ

በንፁህ - የፍቅር መንፈስ - እንድንለያይ እሻለሁ፡፡

ክሊዎፓትራ፡- አትጠራጠር መምጣቴን፣ እዚህ ምናለ ለቀረኝ?

ፈጥኜ ምከተልህ ነኝ፡፡

ያንተ በሆነ ነገር ላይ፣ ቁሳር ምንም ድል አያገኝ፡፡

አንቶኒ፡- ታድያ እስክትመጪም ሲሆን - ባለፉቱ -ጥቂት ቀናት - እያሰብሽ የበደልኩሽን

በጭራሽ - ሐዘን በልብሽ - እንድይገባ አደራሽን፡፡

ከገነት ቀናት የፈካች - አንዲት - ወርቃማ ቅዱስ ቀን

እንዳሳለፍን - ቁጠሪው - በፍቅር ጉም - እየዋኘን፡፡

አቤ . . .ት! አሥር የፍቅር አመታት!

ሳናባክን - አንዲት ሰዓት

ክሊዎፓትራዬ - የኔ እናት - እኔና አንቺ - ፍቅርን ኖርናት፡፡

ክሊቆፓትራ፡- ያንደበትህ ዜማው ጣዕሙ፣ ልክ የሚሞት ወፍ ዜማ ዓይነት

ምነው አንዲት ሰዓት እንኳ ብትቆይልኝ ምናለበት !

አንቶኒ፡- አይመስለኝም - አንድ ደቂቃም የለኝም፡፡

(ትስመዋለች)

ይሄ አሁን - አንዴ የሳምሺኝ - ብቻውን - ለኔ በቂ ነው

ለቁሳር - ከተውኩት ዓለም - የበለጠ ዋጋ አለው!

(ይሞታል)

ክሊዎፓትራ፡- ይህንን አሁን ያልከኝን፣ ደግመህልኝ ባዳመጥኩህ -

እና ሺ ግዜ በሳምኩህ!

ጌታዬ - ትሰማኛለህ?

እባክህን አነጋግረኝ፣ አሁንም ከኔ ጋር ካለ፡፡

እባክህን በርታ ጌታዬ፣ መናገርም ካልተቻለህ

አንድ ምልክት አሳየኝ፣ ልወቅ በህይወት እንዳለህ፡፡

ባክህ እንደምንም ብለህ -

ጌታዬ - ትሰማኛለህ? - አንቶኒ! ትሰማኛለህ?

አይራ፡- አሁን እሱ እዚህ የለም

ሊሰማሽ ከማይችልበት፣ ርቆ ሄዷል ከዚህ አለም፡፡

አሁን እዚህ የምናየው

ነፍሱ ትታው የሄደችው በድን ሸክላ ቀፎዋ ነው

ቻርሚዎን፡- ማዳም አንዳትዘነጊ!

እንዳታዝኚ ገዝቶልሻል! የሙት ቃል ነው ልብ አድርጊ!

ክሊዎፓትራ፡- በደንብ ነው ማሚላለት፣ ፍላጎቱን የጌታዬን

አይራ፡- እንደሚባለው ከሆነ - ቁሳር መሐሪ መሰለኝ፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ቢሆን ባይሆን ምን ችገረኝ!

ምሕረቱን የሚሸቱን፣ ይሂድና ይማር እንጂ፣ እሱ ነው እኔን ሚምረኝ?

እንዲህ አይነቱን መልከስከስ፣ ጌታዬ መች አስተማረኝ!

የራሴን ነፍስ ከቁሳር ላይ፣ በራሴ ክብር ምገዛ ነኝ? . . .

ቻርሚዎኔ - ፈጠን ብለሽ -

ውዶቹን ጌጣጌጦቹን፣ እና ዘውዴን ታመኚያለሽ -

ባለፈው ለድሉ ክብሩ፣ የጎነጎንኩለትም፣ የአበባ ጉንጉን ጨምረሽ፡፡

አንም ደግሞ - የኔ አይራ -

ሂጂ መድሃኒቱን አምጪው፣ ምንገላገልበትን፣ ከዚህ ዓለም ጉድ መከራ፡፡

አይራ፡- ማለት - እባቦችን ማዳም?

ክሊዎፓትራ፡- ሁለቱ ላዝሽ አይገባም!

(ቻርሚዎንና አይራ ይወጣሉ)

በግድ ሊያስኖሩን ሲጥሩ፣ መሞት ምነኛ ይጥማል!

ከገዛ ጭለማ ቤቱ፣ ድረስ ሄዶ ሞትን ማነቅ፣ ልዩ ደስታ ይሰጣል፡፡

እንደጌታዬ ከሆነ ፣ አሁን ፊቴ እንደማየው

ሞት የሚሉት ጥቁር አውሬ፣ የሚያስፈራም ነገር የለው፡፡ . .

(ወደ አንቶኒ በድን ትጠጋለች)

እሺ የኔው ማርካንቶኒ ለጊዜው ብቻችንን ነን -

አንድም ፍጡር እዚህ የለም፣ የሚሰማን ወይ የሚያየን፡፡

እስቲ የቀዘቀዘውን፣ ከንፈሩ አንዴ ልሳመው፣ እስክሄድ ስንቅ ቢሆነኝ

ኦክታቪያ እንደሁ አታየኝ!

(ትስመዋለች)

አቤ . . ት ግን እንዴት ይገርማል!

ክንዶቿ መሓል ከማየው፣ አስር እጅ እንዲህ ይሻላል!

(ቻርሚዎንና አይራ ተመልሰው ይገባሉ)

አሃ! መጥታችኋ? በጣም ጥሩ

ቻርሚዎን፡- እንዴት እንዴት ነው ነገሩ? - ምንድነው አሁን ሚደረግ

ክሊዎፓትራ፡- ሥርዐት ቢጤ አይከፋም፣ ብዙም ሳይሆን እንዲያው ለወግ

ለጌታዬ ክብር ማዕረግ፡፡

በመጀመሪያ - ይህ አክሊል፣ በጀግናዬ ራስ ይጫናል

ለዚህ አቢይ ግዳዩ ክበር፣ የምሸልመው ይሆናል፡፡

(አክሊሉን ትጭንለታለች)

ካንቶኒ ሰይፍ ተማዞ አንቶኒን መርታት የቻለ

ራሱ ማርካቶኒ እንጂ፣ ጫፉ የደረሰ ማን አለ?

ስንቱን ጀግና አስገብሮ፣ ድሉ ድል አልመስልህ ቢለው

አንተስ ከማን ትበልጥ ብሎ፣ የገዛ ልቡን ገደለው፡፡

(ጌጦቿን ማድረግ ትጀምራለች)

ቻርሚዎን፡- እንዲህ ማጌጥ መንቆጥቆጥሽ፣ ታድያ ለምን ይጠቅምሻል?

ደነዝ ነሽ ልበል ቻርሚዋን እያየሽ የማደርገውን

ይህን ታላቅ ሮማዊ አላፊቀርኩትም ሳላውቅ የሚስት ግዴታዬን

ቻርሚዋኔ አልኩ እኮ፣ ሰምተሽኛል?

እስከዛሬ የዋተትኩት ለዚህ ማዕረግ ክብር ነበር፣ አሁን እውን ሆኖልኛል

ሞቱን ሞቼ አገባውና ሚስቱ መሆን ይቻለኛል፡፡

ቻርሚዎን፡- ይኸው ማዳም ጨርሰናል፡፡

ክሊዎፓትራ፡- ጎሽ አንግዲህ ገለል በሉ የቀረው የኔ ስራ ነው፣ ወዲህ ድርሽ እንዳትሉ . . .

እኮ ፍጠኑ ምንድነው -

የምን መፍዘዝ መደንዘዝ ነው ?

/ሁለቱ እያመነቱ በዝግታ ይወጣሉ /

እንግዲህ ከጌታዬ ጎን፣ መቀመጥ ብቻ ቀርቶኛል፡፡

(አገልግሉን ይዛ ከጎኑ ትቀመጣለች)

አዎ ይሄ ቦታ ይገባኛል!

እኔም እነደሱ ቁሣርን፣ ድል መንሳት ይኖርብኛል፡፡

በል እንግዲህ - ሰላም ላንተ! ውድ የሕያው ፍቅሬ ቅሪት፡፡

አማልክት አደራ ስሙኝ፣ ትቼው ከመሄዴ በፊት!

ምድረ ግብጽ ለህይወቱ ፣ የነሳችው ሰላሙን

ከእንግዲህ ወዲያ ለሞቱ፣ እንደማትነፍገው ይሁን! . . .

ሴራጲዮን፡- **(ከውስጡ)** ንግሥቲቱ ወዴት ትሆን? ሙሉ ከተማው ተይሏል!

ቁሳርም እየመጣ ነው - ከዋናው መግቢያ በር ደርሷል!

ክሊዎፓትራ፡- ሞትን ደርሶ ሊያስጥል ነበር?

ዘግይቷል! ሊያምረው ነው ሚቀር፡፡

አገልግሉን ውስጥ እንዳለች እባቡን ለማበሳጨት ትሞክራለች

(ፊቷን ወደ ጎን አዙራ እጇን አገልግሉ ውስጥ ትጨምራለች፡፡ ወዲያው ክንዷ ላይ ደም ይታያል)

ጎሽ ስራው ሰርቷል

ሴራጲዮን፡- **(ከውስጥ)** ይበቃል እንግዲህ! በሩን፣ በሃይል ሰብራችሁ ክፈቱት!

ያንን ከይሲ ርጉም ሰው ግን፣ ባይነ ቁራኛ ጠብቁት!

ክሊዎፓትራ፡- ሞት ቀልጣፋው! - አይ አጅሬ!

ምኔው ምኔው ቀናህ፣ ተሰራጨህ በደም ስሬ?

ከጌታዬ ዘንድ ለመድረስ፣ አቤት እንዴት ቸኩያለሁ!

አሁን ግን - ባጭር ጊዜ ውስጥ፣ እንደማገኘው አውቃለሁ፡፡

ከባድ የመደንዘዝ ስሜት፣ ዘልቆ በሰራ አካላቴ

ይኸው ደረሰ ከአናቴ . .

ሽፋሽፍቶቼ ከበዱኝ - ዐይኖቼ ተከደኑብኝ -አይታየኝም ጨለመብኝ -

ውዱ ፍቅሬ - ድቅድቅ ጉም ውስጥ ገባና ተሰወረብኝ -

የት ላግኘው? - የት ሄደብኝ?

(ከጎኑ ትሆናለች)

ቁሳር ጉድህ! - ናና እየን!

አሁንነ - ከቻልክ - አለያየን!

(ትሞታለች፡፡ ሴራጲዮን፣ ሁለት ቄሶች አሌክሳስ የፊጥኝ ታስሮ፣ እና ሌሎችም ግብፃውያን ብለው ይገባሉ) ቻርሚዋንና አይራ ይገባሉ

አንደኛ ቄስ፡- ሴራጲዮን - ጉድ እይ ብቻ!

ሞት ያደረሰውን ጥፋት፣ ሊያደርገኝ መዘባበቻ!

ሴራጲዮን፡- የፈራሁት ይህን ነበር፡፡

ቻርሚዎን - ደግ ስራ ነው ይህ ነገር?

ቻርሚዎን፡- አዎ ደግ ሞት ነው የሞተች - አምላክ በወግ ይቀበላት

ሴራጲዮን፡- ሁሉም ነገር መጨረሻው፣ እንዲህ ሆነና አረፈው?

ለነገሩማ - ሁን ያለው ፣ ወትሮውም መሆኑ ማይቀርም ነው፡፡

እንዲህ ቢሆን - እንዲያ ባይሆን - እያልን የምንጨነቀው

እንዲያው ልፋ ቢለን እንጂ - እንዳች የለም ምንፈይደው፡፡ . .

እየዋቸው ፍቅርኛሞቹን - ጎን ለጎን ተቀምጠው ሳሉ

ለጠቅላላው የሰው ልጅ ዘር፣ መለኮታዊ አመራር፣ የሚሰጡ ይመስላሉ !

የፈገግታዋ እንኳ ስሜት፣ ታትሞ የቀረው ከፊቷ

እንዳላስደታት ያሳያል፣ ለወደደችው መሞቷ

እዚያም ደስታን ልትሰጠው፣ ከገባበት ሌላ አለም፣ ተከትላው በመግባቷ፡፡ . .

በሉ እንግዲህ - ቁሳርም እየገባ ነው፣ አሁን ላዘን ጊዜም የለን

ያን መሰሪ እርጉም ፍጡር፣ ለተራበው የቄሣር ሰይፍ፣ ማስታገሻ አስረከበን

ከወደፊቱ ገጢያችን፣ እርቀሰላም እንፈጥራለን፡፡ . .

(ወደ ክሊዎፓትራና አንቶኒ በመዞር)

ረጅሙን እንቅልፍ ተኙት፣ እናንት የፍቅር ሃውልቶች፣ አማልክት የባረኳችሁ

እጣፈንታ ማዕበላት፣ ከሰው ልጅ ዕድል ፈተና ለዝንት ዓለም ርቃችሁ፡፡

ዝናችሁ ከትውልድ ትውልድ፣ ያስተጋባልኝ ለዘላለም

በፍቅረኛሞች ታሪክ ውስጥ፣ እንደናንተ የኖረና፣ ሞቱም እንዲህ ያማረ የለም፡፡

ተፈፀመ